**<u>አዋጅ ቁጥር----/፪ሺ፲፬</u>**

# <u>የድሬዳዋ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ</u>

የአስተዳደሩን አስፈፃሚ እና ማዘጋጃ ቤታዊ አካላት ለነዋሪው ህዝብ ፍትሀዊ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ አገልግሎት መስጠት በሚችሉበት ሁኔታ እንደገና ማደራጀት በማስፈለጉ፤ በሀገራችን ብሎም በአስተዳደራችን እየተካሄደ ያለውን ለውጥ ውጤታማና ዘላቂ ለማድረግ ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮ አንቀፅ (፲፪) ንዑስ አንቀፅ (፩) ፊደል ‹‹ሀ›› ላይ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከዚህ የሚከተለውን አውጇል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

### ፩ <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ ‹‹የድሬዳዋ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም እና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር _____/፪ሺ፲፬ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪ <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩ ‹‹**አስተዳደር**›› ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ነው፤

፪ ‹‹**ቻርተር**›› ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮ነው፤

፫ ‹‹**ካቢኔ**›› ማለት በቻርተሩ አንቀጽ ፲(፪) (ሐ) የተመለከተውና በቻርተሩ አንቀጽ ፴፪ ላይ የተደነገጉት ሥልጣንና ተግባሮች ያሉት የአስተዳደሩ የሥልጣን አካል ነው፤

፬ ‹‹**ከንቲባ**›› ማለት አስተዳደሩን በበላይነት የሚመራ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ነው፤

፭ ‹‹**ምክትልከንቲባ**›› ማለት አስተዳደሩን የሚመራ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ነው፤

፮ ‹‹**ቢሮ**›› ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ መሠረት የተቋቋመ የአስተዳደሩ ቢሮ ነው፤

፯ ‹‹ሥራ **አስኪያጅ**›› ማለት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች አስፈፃሚ ነው፤

፳ ‹‹**የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት**›› ማለት የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያወጣው ህግ መሰረት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ተብሎ የሚወሰን ማናቸውም አገልግሎት ነው፤

፱ በዚህ አዋጅ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ስለካቢኔ አባላትና ስለሌሎች አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት

## ፫ የካቢኔ አባላት

፩ የአስተዳደሩ ካቢኔ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ.ከንቲባ፣

ለ.ምክትል ከንቲባ፣

ሐ.በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭መሠረት የተቋቋሙትን ቢሮዎች የሚመሩ ኃላፊዎች፣

መ.የከተማው ሥራ አስኪያጅ፤እና

ሠ.ከንቲባው በአባልነት እንዲሳተፉ የሚመርጣቸው የአስተዳደሩ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሐ) የተመለከተው ማንኛውም የቢሮ ኃላፊ በካቢኔ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ወይም ውክልና የተሰጠው ሰው በካቢኔ ስብሰባ በምትክ አባልነት ይሳተፋል፡፡

## ፬ የአስተዳደሩ ካቢኔ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

የአስተዳደሩ ካቢኔ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፭ የቢሮዎች መቋቋምና ተጠሪነት

የሚከተሉት ለከንቲባው ተጠሪ የሆኑ ቢሮዎችህጋዊ ሰውነት በማግኘት ተቋቁመዋል፡፡

፩ የንግድና፣ ኢንዱስትሪ ቢሮ፣

፪ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣

፫ የሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ፣

፬ የግብርና፣ ውሃ፣ ማዕድንና አነርጂ ቢሮ፣

፭ የጤና ቢሮ፣

፮ የትምህርት ቢሮ፣

፯ የሴቶች፣ህፃናትናማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣

፰ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ፣

፱ የመንግሥት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ፣

፲ የመሬት ልማት እና ማናጅመንት ቢሮ፣

፲፩ የከተማ ልማትናኮንስትራክሽን ቢሮ፤

፲፪ የሥራ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ፤

፲፫ የወጣቶች፣ ስፖርት፣ ባህልና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ማስተባበሪያ ቢሮ፡፡

## ፮ <u>ስለ ምክትል ቢሮ ኃላፊዎች ፣ ተጠሪነትና ኃላፊነት</u>

፩ እያንዳንዱ ቢሮ እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ሊኖረው ይችላል፤

፪ እያንዳንዱ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለቢሮ ኃላፊው ሆኖ በቢሮው ተቋማዊ አደረጃጀት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፤

፫ የቢሮው ኃላፊው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡

## ፯ <u>ስለ አስፈፃሚ አካላት መቋቋም</u>

የሚከተሉት ሌሎች አስፈፃሚ አካላት ህጋዊ ሰውነት በማግኘት ተቋቁመዋል፡-

፩ የከንቲባውናእና የካቢኔ ጉዳዮች ጽህፈት ቤት፤

፪ የልማት ተነሺዎች ካሳ ክፍያና መልሶ ማቋቋም ኤጀንሲ፤

፫ የውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ጽህፈት ቤት፣

፬ የመንግስት ግንባታና የውል አስተዳደር ኤጀንሲ፤

፭ የአጠቃላይ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራት ማረጋገጫ ባለሥልጣን፤

፮ የመልካም አስተዳደር፣ የህዝብ አቤቱታና ቅሬታ አፈታት ጽህፈት ቤት፤

፯ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኤጀንሲ፤

፰ የአደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን፤

፱ የግብርና እና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽህፈት ቤት፤

፲የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፤

፲፩የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ኮሚሽን፤

፲፪የገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ፤

፲፫የኢንቨስትመንት እና ዲያስፖራ ኮሚሽን፤

፲፬የንግድ ጽህፈት ቤት፤

፲፭የስፖርት ኮሚሽን፤

፲፮የባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፤

፲፯የመሬት ልማት እና ከተማ ማደስ ጽህፈት ቤት፤

፲፰የአካባቢ ልማትና የህብረተሰብ ተሳትፎ ኤጀንሲ፤

፲፱የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጽህፈት ቤት፤

፳ የህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ማስፋፊያ፣ የግብዓት እና ግብይት ኤጀንሲ፡፡

፳፩የእንሰሳት ሀብት ልማትና ጤና ኤጀንሲ፤

፳፪የምግብ፣ መድሀኒትና ጤና ነክ ቁጥጥር ባለሥልጣን፤

፳፫የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲቲዩት፤

፳፬ የደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት፤

፳፭ የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፤

፳፮የፍትህ ጽህፈት ቤት፤

፳፯ የሚሊሻ ጽህፈት ቤት፤

፳፰ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ኤጀንሲ፡፡

## ፰ <u>የአስፈፃሚአካላትተጠሪነት</u>

፩ የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነታቸው ለከንቲባው ይሆናል፡-

ሀ. የከንቲባውና የካቢኔ ጉዳዬች ጽህፈት ቤት፤

ለ. የፍትህ ጽህፈት ቤት፤

ሐ. የአደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን፤

መ. የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፤

ሠ. የልማት ተነሺዎች ካሳ ክፍያና መልሶ ማቋቋም ኤጀንሲ፤

ረ. የአጠቃላይ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራት ማረጋገጫ ባለስልጣን፤

ሸ. የመልካም አስተዳደር፣ የህዝብ አቤቱታና ቅሬታ አፈታት ጽህፈት ቤት፤

ቀ. የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን፤

፪ የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ. የንግድ ጽህፈት ቤት ፤

ለ. የኢንቨስትመንት እና ዲያሰፖራ ኮሚሽን ፤

ሐ. የአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንድስትሪ ልማት ኤጀንሲ፡፡

፫ የሚከተሉትአስፈፃሚአካላትተጠሪነት ለግብርና፣ ውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ. የውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ጽህፈት ቤት ፤

ለ. የግብርና እና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽህፈት ቤት፤

ሐ. የገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ፤

መ. የእንሰሳት ሀብት ልማትና ጤና ኤጀንሲ፤

ሠ. የህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ፣ማስፋፊያ፣ የግብዓት እና ግብይት ኤጀንሲ፡፡

፬ የሚከተሉት አስፋፃሚ አካላት ተጠሪነት ለጤና ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ. የምግብ መድሃኒት እና ጤና ነክ ቁጥጥር ባለሥልጣን ፤

ለ. የድሬዳዋ አስተዳደር የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲቲዩት፡፡

፭ የመሬት ልማት እና ከተማ ማደስ ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለመሬት ልማት እና ማናጅመንት ቢሮ ይሆናል፡፡

፮ የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ. የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ኮሚሽን፤

ለ.የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ ጽህፈት ቤት፡፡

፯ የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ. የመንግስት ግንባታና የውል አስተዳደር ኤጀንሲ፤

ለ የመንግስት ህንፃዎችና ቤቶች አስተዳደር ኤጀንሲ፡፡

፰ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለወጣቶች፣ስፖርት፣ ባህልና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ. የባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፤

ለ. ስፖርት ኮሚሽን፡፡

፱የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ኤጀንሲ ተጠሪነት ለሥራ፣ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡

፲ የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ. የደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት፤

ለ. የሚሊሻ ጽህፈት ቤት፡፡

## ፱ በሌሎች ህጎች ስለተቋቋሙ አስፈፃሚ አካላት

የአስተዳደሩ ሌሎች አስፈፃሚ አካላት በተቋቋሙባቸው ህጎች በተደነገገው መሠረት ሥራቸውን የሚቀጥሉ ሲሆን ተጠሪነታቸውም እንደሚከተለው ይሆናሉ፡-

፩ የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለከንቲባው ይሆናል፡-

ሀ. የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ፤

ለ. የግንባታ ፍቃድ ቁጥጥር ባለስልጣን፡፡

፪ የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ. የመንግስት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን፤

ለ. የገቢዎች ባለስልጣን፡፡

፫ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የነዋሪዎችእና መረጃ ኤጀንሲ ተጠሪነት ለሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ይሆናል፡፡

፬ የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለመሬት ልማትና ማናጅመንት ቢሮ ይሆናል፡፡

፭ የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለሥራ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ. የቴክኒክ ሙያና ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ፤

ለ. የልህቀት ማዕከል፡፡

፮ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮሮፖሬሽን ተጠሪነት ለንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ይሆናል፡፡

፯ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኢጀንሲ ይሆናል፡፡

፰የድሬዳዋ አስተዳደር የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ተጠሪነት ለትምህርት ቢሮ ይሆናል፡፡

፱የሚከተሉት ኮሌጆች ተጠሪነታቸው ለቴክኒክ ሙያና ትምህርት ሥልጠና ኤጀንሲ ይሆናል፡፡

ሀ. የኢትዮ-ጣሊያን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፤

ለ. የድሬዳዋ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ፡፡

## ፲ የቢሮዎችና የሌሎች የአስፈፃሚ አካላት ኃላፊዎች ተጠሪነትና ኃላፊነት

፩ እያንዳንዱ የቢሮ ኃላፊ የሚመራውን ቢሮ የሚመለከቱ ሥራዎችን፣ ፕሮግራሞች እና የህጎችን አፈፃፀም በተመለከተ ተጠሪነቱ ለከንቲባው ሆኖ፣

ሀ. ኃላፊ ለሆነበት አስፈፃሚ አካል የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ. ኃላፊ ለሆነበት አስፈፃሚ አካል በተፈቀደው በጀት እና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤

ሐ. ኃላፊ የሆነበትን አስፈፃሚ አካል ይመራል፣ ይወክላል፡፡

፪ እያንዳንዱ ሌላ አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነታቸው በዚህ  አዋጅ አንቀጽ ፯እና ፰ ለተመለከተው አካል ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሀ-ሐ/የተመለከቱት ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡፡

## ፲፲ ስለ ሠራተኞችና ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶች

፩ እያንዳንዱ አስፈፃሚ አካል ኃላፊ እንዲሁም ሌሎች አግባብ ያላቸው የሥራ ክፍሎች እና ለሥራው የሚያስፈልጉ ሠራተኞች የሚኖረው ሆኖ ይደራጃል፡፡

፪ ቢሮዎች ከሚያስተባብሯቸው አስፈፃሚ አካላት ወይም ከሌሎች አስፈፃሚ አካላት ጋር የድጋፍ ሰጭ አገልግሎቶችን በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያፀድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት በህግ ይወሰናል፡፡

# ክፍል ሦስት

# የቢሮዎችና የሌሎች አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር

## ፲፩ የወል ሥልጣንና ተግባር፤

እያንዳንዱ ቢሮና ሌሎች አስፈፃሚ አካላት በሥራቸው መስክ፤

፩ ከፌዴራል መንግሥት ፖሊሲና ህግ ጋር የሚጣጣም የአስተዳደሩን ፖሊሲና ህግ ያመነጫል፣ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

፪ በፌዴራል መንግሥትና በአስተዳደሩ የወጡ ፖሊሲዎችና ህጎችን በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣ መመሪያዎችን ያወጣል፤

፫ ምርምርና ጥናት ያከናውናል፣ ስታትስቲካል መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ያሰራጫል፤

፬ ሠራተኞቹን አግባብ ባለው ህግ መሠረት ያስተዳድራል፤

፭ በጀትና ንብረት በህግ መሠረት ያስተዳድራል፤

፮ በህግ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

፯ የለውጥ ሥራዎችንና የአሠራር ማሻሻያ ፕሮግራምን ተግባራዊ ያደርጋል፤

፰ አግባብ ካላቸው አካላትና የአስተዳደሩ ነዋሪዎች ጋር በአጋርነት ለመስራት የሚያስችሉ ስልቶችን በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፱ የሚያዘጋጃቸው የልማት ዕቅድ የሴቶች ፣ የህፃናት የወጣቶች ጉዳይ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃን ተግባር እንዲካተቱ መደረጋቸውን ያረጋግ ጣል፤

፲ የአካል ጉዳተኞችና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጠቂዎች በሃላፊነቱ ክልል የእኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፩ ስለ ሥራው አፈፃፀም በየወቅቱ ተጠሪ ለሆነለት እና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፤

፲፪ በዚህ አዋጅና በሌሎች ህጎች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፡፡

## ፲፪ የከንቲባው እና የካቢኔ ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር፤

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ በአስተዳደሩ ካቢኔና በከንቲባውየሚካሄዱ ስብሰባዎችን ቃለ ጉባኤ ይይዛል፣ ለካቢኔ ስብሰባ የሚቀርቡ አጀንዳዎችን አስፈላጊነት አይቶ ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ የካቢኔ ውሣኔዎችን ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፤

፪ የካቢኔ ውሣኔዎች እና ሰነዶችን ያደራጃል፣ በአግባቡ ይይዛል፣ የመረጃ አገልግሎቱን በዘመናዊ ዘዴ ያደራጃል፤

፫ የከንቲባውን የዕለት ተዕለት መርሀ ግብሮችን ይከታተላል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬ ከንቲባው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የካቢኔውን የስብሰባ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፣ ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር በአባሪነት ለሚመለከታቸው አባላት ይልካል፣ ስብሰባዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

፭ ጽህፈት ቤቱ ከህዝቡ ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖረው ከህዝብ መገናኛ ዘዴዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር የጽህፈት ቤቱን ዓላማና ተግባር ያስተዋውቃል፤

፮ የአስተዳደሩን የስራ እንቅስቃሴ የሚመለከቱ መረጃዎችን በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በማሰራጨት የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ያረጋግጣል፤ የተለያዩ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን በማዘጋጀት የአስተዳደሩን መልካም ገጽታ ይገነባል፤

፯ በጽህፈት ቤቱ በኩል አስተዳደሩን ለመጎብኘትና ለሥራ ጉዳይ ለሚመጡ የፌዴራል እና የክልል ከፍተኛ ባለስልጣናት እንዲሁም የውጪ አገር እንግዶችን ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ፕሮግራም አዘጋጅቶ ያስጎበኛል፣ ተገቢ መረጃዎችን እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፰ በከንቲባውየሚሰጡ የፕሬስ መግለጫ፣ መልዕክቶች፣ ጽሁፎችና ንግግሮች እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

፱ ከአስተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ከፌዴራልና ከክልሎች ጋር ያለውን የሥራ ግንኙነት ይከታተላል፤

፲ ለጽህፈት ቤቱ የሚቀርቡትን ወይም የካቢኔውን ውሣኔ የሚጠይቁ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በማጥናት የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

፲፩ በአስተዳደሩ ካቢኔ የሚወጡ ደንቦችናመመሪያዎችን በድሬ ነጋሪት ጋዜጣ እንዲታተሙና እንዲሰራጩ ያደርጋል፤

፲፪ አስተዳደሩ ከእህት እና ከሌሎች ከተሞች ጋር ለሚያደርገው ግንኙነት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣ ምቹ ሁኔታም ይፈጥራል፤

፲፫ ከሌሎች የውጭ ሀገር ከተሞች፤ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ ጉዳዮች የውጭ ግንኙነት ሥራዎችን ያስተባብራል፤

፲፬ በመልካም አስተዳደር መጓደል ምክንያት የአስተዳደሩን የመጨረሻ ውሳኔ ለማግኘት ወደ ጽህፈት ቤቱ የሚመጣ ማንኛውም ባለጉዳይ በአግባቡ የሚስተናገድበትን ስርዓት ይዘረጋል፣ በስራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤

፲፭ ከተለያዩ አካላት የሚቀርቡ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ጥያቄዎችን በመቀበል መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

፲፮ ለአስተዳደሩ ባለስልጣናት የፕሮቶኮል አገልግሎት ይሰጣል፣ የውጭ ሀገር ጉዞ ያመቻቻል፤

፲፯ የአስተዳደሩ አስፈፃሚ አካላትና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን እቅድ እና የእቅድ አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፣ ወቅታዊ መረጃ ለከንቲባው ያቀርባል፤

፲፰ ለከንቲባው ተጠሪ የሆኑ የአስተዳደሩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶችን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ ወቅታዊ መረጃ ለከንቲባው ያቀርባል፤

፲፱ ለከንቲባው በተለያዩ ዘርፎች የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤

፳ አስተዳደሩ ከአጎራባችክልሎች የሚዋሰንበትን ድንበርና በአስተዳደሩ የሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች የሚዋሰኑበትን ድንበር በተመለከተ የሚነሱ አለመግባባቶችን በመፈተሽ ለአስተዳደሩ ምክር ቤት ቀርቦ ውሣኔ የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፳፩የካቢኔ ጉዳዮችን ስራ ያከናውናል፤

፳፪ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፲፫ <u>የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባር</u>

ባለሥልጣኑየሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ በፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሚወጡ ደረጃዎችን በመከተል የአስተዳደሩን የአካባቢ ደረጃዎች ያዘጋጃል፣ አካበቢ እንዳይበከል የመከላከያ ስልት ይቀይሳል፣ አግባብ ያላቸውን አካላት ያስተባብራል፤

፪ የአካባቢ ጥበቃና የተፈጥሮ ሀብት የዘለቄታ አጠቃቀም እንዲኖርና እንዳይባክን ተገቢ ቅስቀሳ ያደርጋል፣ ስለአካበቢ ጥበቃ በመገናኛ ብዙሃን ትምህርት ይሰጣል፤

፫ የኢንዱስትሪ ዝቃጭ፣ ተረፈ ምርትና ቆሻሻ በህግ መሠረት መወገዱን ይከታተላል፤

፬ በአስተዳደሩ በሚገኙ በማናቸውም ኢንዱስትሪ፣ የማምረቻ እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ የአካባቢ ኦዲት ያካሂዳል፤

፭ የአካባቢ ጥበቃ ህጎችን መሠረት በማድረግ የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፮ በከርሰ ምድርና ገፀ-ምድር ሀብቶች ላይ ፍቃድ በሚሰጡ አካላት ላይ የቁጥጥር ስራ ያካሂዳል፤

፯ ከአካባቢ ጋር በተያያዘ ከሚሰሩ ከመንግሥታዊ፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ጋር ተባብሮ ይሰራል፤

፰ የአካባቢ ላብራቶሪ ያቋቁማል፣ ሌሎች የክትትል ጣቢያዎችን ይመሰርታል፤

፱ በአስተዳደሩ የውሃ፣ የአየር፣ የጨረርና የድምጽ ብክለት የሚቃለልባቸውን ስልቶች ጥናትና ምርምር በማድረግ፣ ህጎችን በማዘጋጀት እንዲፀድቁና ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፲ አካባቢን ለመጠበቅና የተጎዳ አካባቢን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ አግባብ ካላቸው መስሪያ ቤቶች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣ እንደአስፈላጊነቱም የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፩ በመንግስትም ሆነ በግል ፕሮጀክቶች፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስልቶች፣ ህጎችና መርሐ ግብሮች ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲፪ አደገኛ ነገሮችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ አስተዳደሩ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን እንዲሁም ህያዋንን በዘረመል ምህንድስና መለወጥን፣ ልውጥ ወይም ባዕድ ህያዋንን ወደ አስተዳደሩ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን የሚመለከቱ የአካባቢ ደህንነት ህጎችንና መመሪያዎችን አግባብ ካላቸው መስሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፣ ሲፈቀዱም በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፲፫ በልማት እቅዶችና በኢንቨስትመንት መርሀ ግብሮች ውስጥ የሚካተቱ የአካባቢ የአዋጭነት ማስሊያ ቀመሮችንና የስሌት ሥርዓትን አግባብ ካላቸው መስሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፣ ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ እንደሁኔታውም በጥቅም የመዋላቸውን ሂደት ይከታተላል፤

፲፬ አግባብ ካላቸው መስሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓትን ይዘረጋል፤

፲፭ የአካባቢ ጥበቃ ምርምሮችን ያስተባብራል፣ ያበረታታል እንደአስፈላጊነቱም ራሱ ያካሂዳል፤

፲፮ አግባብ ባላቸው የህግ ድንጋጌዎች መሠረት የአካባቢ ጥበቃ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በአስተዳደሩ ስልጣን ስር ወደሚገኝ ማንኛውም መሬት፣ ቅጥር ግቢ ወይም ሌላ ቦታ ይገባል፣ ኃላፊነቱን ለመወጣት ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ማንኛውንም ነገር በህግ መሰረት ይፈትሻል፣ ናሙናዎችን ይወስዳል፤

፲፯ የአስተዳደሩን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ በየወቅቱ እያዘጋጀ አግባብ ላላቸው መንግስታዊ ፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት እንዲደርስ ያደርጋል፤

፲፰ የአካባቢ ጥበቃ የድርጊት እቅዶችንና ፕሮጀክቶችን ዝግጅት ያበረታታል ወይም ያግዛል፣ ለድርጊት እቅዶቹና ፕሮጀክቶቹ ማስፈፀሚያ የሚውሉ እገዛዎችን ያፈላልጋል፤

፲፱ አግባብ ያላቸው መስሪያ ቤቶች በአስተዳደሩ አካባቢ ጥበቃን በሚመለከቱ ህጎች የተጣሉባቸውን ኃላፊነቶች በሚወጡበት ሁኔታላይ ምክር ይሰጣል፣ እንደአስፈላጊነቱም እርምት ሊወሰድባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ የውሳኔ ሀሳብ ለአስተዳደሩ ያቀርባል፤

፳.በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ድንገተኛ ሁኔታዎችን ለመቋቋም ስለሚወሰዱ አስፈላጊ እርምጃዎች አስተዳደሩን ያማክራል፤

፳፩ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በተያያዙ በወጡ ህጎች እና መስፈርቶች መሰረት የተደነገገውን ተላልፈው በተገኙ ማናቸውም ወገኖች ላይ አግባብ ባላቸው የፍትህና አስተዳደራዊ የዳኝነት ሰጪ አካላት ፊት በማቅረብ ተገቢ ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፳፪.አግባብነት ባላቸው የህግ ድንጋጌዎች መሠረት የአካባቢ ጥበቃ ግዴታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

፳፫. የአስተዳደሩን የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ለመቋቋም የሚያግዙ ስልቶችን ይቀይሳል፤ በልማት እቅድ ውስጥ ተፅዕኖ ማቋቋሚያ ስልቶች እንዲተገበሩ ስልት ይነድፋል አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ግብረ መልስም ይሰጣል፤

፳፬. የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ ለአስተዳደሩ ያቀርባል፣ ተፅዕኖውን ለመቋቋም በየደረጃው ለሚወሰድ መፍትሄ አቅጣጫ ይቀይሳል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

፳፭.አየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ እንዲተገበር ያደርጋል አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፤

፳፮.የአስተዳደሩን የሙቀት አማቂ ጋዞች መረጃ ይሰበስባል፣ በሚተገበረው የስልት እርምጃ ልቀት ደረጃውን በየወቅቱ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

፳፯.ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፲፬ <u>የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን</u>

ባለስልጣኑ በድሬዳዋ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር፴፫/፪ሺ፯የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፲፭ <u>የልማት ተነሺዎች ካሳ ክፍያና መልሶ ማቋቋም ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

፩ የዘርፉን ሥራ የሚያቀላጥፉ ደንቦች፣መመሪያዎችና የአሰራር ማሻሻያ ማኑዋሎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ያፀድቃል፣አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፪ ከባለድርሻ አካላት ጋር የጠበቀ የስራ ግንኙነት እንዲኖር የበኩሉን የስራ ድርሻ ይወጣል፤ሌሎችም እንዲወጡ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፤

፫ ለልዩ ልዩ ልማት ስራዎች አገልግሎት የሚውሉ ቦታዎችን እና በቦታው ላይ ስለሚኖሩ ተነሺዎች ዝርዝር መረጃ ቦታውን ለማልማት የሚፈልጉ ተቋማት ለይተው እንዲያሳውቁ፣ የፍላጎት መግለጫ ጥያቄ እንዲያቀርቡ ያደርጋል፣

፬ በቀረበው ፍላጎት መነሻነት ስትራቴጂክ እቅድ በመንደፍ የአስተደደሩ ካቢኔ እንዲያፀድቀው በማድረግ አስፈላጊው ግብአት እንዲመደብ ያደርጋል፣

፭ የዘርፉን ስራ ለማከናወን አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ተቋማትና ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ይሰራል፤

፮ ለልማት ሲባል ከቀያቸው የሚነሱ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰፍሩበት ቦታ፣ የመኖሪያ ቤት መዘጋጀቱንና በአካባቢው አስፈላጊ የሆኑ የመሰረተ ልማት አቅርቦቶች ተሟልተው መገኘታቸውን ያረጋግጣል፣

፯ የልማት ተነሺዎች ነባራዊውን ሁኔታ ግንዛቤ እንዲጨብጡ እና ከነባር ይዞታቸው በፍላጎት መልቀቅ እንዲችሉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የግንዛቤ ማጎልበቻ ስራዎችን ይሰራል፣ ስልጠና ይሰጣል፣

፰ የተለያዩ የመረጃ ማሰራጫ ዘዴዎችን በመጠቀም የመንግስትን የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ለአስተዳደሩ ማህበረሰብ በማስተዋወቅ ለልማት ሲባል ከነባር ይዞታ መነሳትን በተመለከተ በቂ ግንዛቤ እንዲኖር እና የጋራ መግባባትም እንዲፈጠር ይሰራል፣

፱ የልማት ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበት የአሰራር ስርዓት እንዲዘረጋ እና ወጥ ስታንዳርድእንዲዘጋጅ ያደርጋል፣

፲ የልማት ተነሺዎች የካሳ ክፍያ፣መልሶ ማቋቋምና ቅሬታ አፈታት ስራን የሚያፋጥኑ ቴክኖሎጂዎች በሥራ ላይ የሚውሉበትን ስልት እንዲቀየስና ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፲፩ በመልሶ ማቋቋም ሂደት ለተነሺዎች የተፈጸመው ክፍያ ሳይባክን ውጤት በሚያስገኝ ስራ ላይ እንዲውል እገዛ ያደርጋል፣

፲፪ ለመልሶ ተቋቋሚዎች የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ አዋጪ ፕሮጀክቶች እንዲዘጋጁ በማድረግና ለሚመለከተው አካል አቅርቦ በማፀደቅ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣

፲፫ የልማት ተነሺዎች በህግ ማግኘት የሚገባቸውን መብቶች መከበራቸውን ያረጋግጣል አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፲፬ የልማት ተነሺዎች በተሰማሩባቸው የልማት ዘርፎች የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡ ዘንድ የፕሮጀክቶቹን እንቅስቃሴ አግባብ ያለው ክትትልና ድጋፍ እንዲደረግላቸው ያደርጋል፣

፲፭ መልሶ ተቋቋሚዎችን በአካል በመጎብኘት ቴክኒካዊና ሞራላዊ ድጋፍ በመስጠት የተሻለ አፈፃፀም ላስመዘገቡት የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣል፣

፲፮ በንብረት ግመታ ሂደትም ሆነ በክፍያ አፈጻጸም ያልረኩ ዜጎች ቅሬታቸውን ለኮሚሽኑ ሲያቀርቡ ጥያቄያቸውን በመቀበል ፍትሀዊ ምላሽ በወቅቱ እንዲሰጥበት ያደርጋል፣

፲፯ ከህበረተሰቡ እና ከልማት ተነሺዎች በጥቆማ፣በቅሬታና በአቤቱታ መልክ የቀረቡ ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ የውሳኔ ሃሳቦችን አጣርቶ ያጸድቃል፣

፲፰ የአስተዳደሩ የበላይ አመራር አካላት ለተነሺዎች ጥያቄዎችና አስተያየቶች ምላሽ የሚሰጡበትን የጋራ መድረክ ይፈጥራል፣

፲፱ ቅሬታን ከምንጩ ለመቀነስ የሚረዱ ልዩ ልዩ ጥናቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣በጥናቱ ግኝቶች ላይ ለሚመለከታቸው አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ እንዲፈጠር ያደርጋል፣

፳ ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፲፮ <u>የአጠቃላይ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራት ማረጋገጫ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር</u>

ባለስልጣኑየሚከተሉትሥልጣንናተግባራትይኖሩታል፡-

፩ በአጠቃላይትምህርትእናበቴክኒክናሙያተቋማትየሚሠጥትምህርትናስልጠናከሀገሪቱናከአስተዳደሩየኢኮኖሚናየማህበራዊፍላጎትናአግባብነትካላቸውሥርዓተትምህርት፣ፖሊሲዎችናስትራቴጂዎችጋርመገናዘባቸውንያረጋግጣል፣ይቆጣጠራልአስፈላጊእርምጃዎችንይወስዳል፤

፪ በአጠቃላይትምህርትናበቴክኒክናሙያትምህርትናስልጠናተቋማትበህግየተቀመጠውንየትምህርትናስልጠናስታንዳርድ፣የትምህርትናስልጠናአገልግሎትአሰጣጥመስፈርትማሟላታቸውን፤አግባብነቱናጥራቱደረጃውንጠብቆስለመፈፀሙይከታተላል፤ይቆጣጠራል፤

፫ የአጠቃላይትምህርትእናስልጠናተቋማትየሙያብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትይሰጣል፣ያድሳል፣ያግዳል፣ይሰርዛል፤

፬ የመምህራን፣ርእስመምህራንናሱፐርቫይዘሮችእናየዲኖችናአሰልጣኝመምህራንየሙያብቃትደረጃያረጋግጣል፣ፍቃድይሰጣል፣ያድሳል፣ይሰርዛል፤

፭ የአጠቃላይትምህርትእናስልጠናተቋማትንየሙያብቃትንመረጃያደራጃል፤ያሰራጫል፤

፮ የአጠቃላይየትምህርትእናስልጠናተቋማትብቃትእናምዘናመከታተያናመገምገሚያስርዓትዘርግቶተግባራዊያደርጋል፤

፯ ፍቃድያላቸውየትምህርትእናስልጠናተቋማትጥራታቸውከስታንዳርድበታችበሆኑተቋማትላይየሙያብቃትማረጋገጫውንእስከመሰረዝናእስከማሸግየሚደርስእርምጃይወስዳል፤

፰ በሕገወጥመንገድየሙያብቃትማረጋገጫፍቃድያገኙየትምህርትናስልጠናተቋማትላይየሙያፈቃዳቸውንይሰርዛል፣ተቋሙንምያሽጋል፤አግባብባለውየወንጀልሕግእንዲጠየቁስልጣንላለውአካልያሳውቃል፤

፱ የሙያብቃትፍቃድእያላቸውህግበሚጥሱአካላትላይአስተዳደራዊእርምጃይወስዳል፤እንዲወሰድያደርጋል፤

፲የሙያብቃትፍቃድሳያገኙወይምበሌሎችተቋማትየሙያብቃትፈቃድየሚሰሩየትምህርትእናስልጠናተቋማትንያሽጋል፤አግባብባለውየወንጀልሕግእንዲጠየቁሥልጣንላለውአካልያሳውቃል፤

፲፩ለትምህርትእናስልጠናተቋማትዕውቅናይሰጣል፣እውቅናአግኝተውየሚሠሩትምህርትቤቶችበሀገርአቀፍምሆነበአስተዳደርደረጃበሚወጡህጎችየተቀመጡየትምህርትአግባብነትናጥራትደረጃዎችንማሟላታቸውንያረጋግጣል፤

፲፪በትምህርትተቋማትየህብረተሰቡንተሳትፎሊያረጋግጡየሚችሉአደረጃጀቶች፣የወላጅ፣የተማሪ፣የመምህራንፎረም፣የተማሪክበባትስለመኖራቸውያረጋግጣል፤እንዲሁምየትምህርትአገልግሎትክፍያዎችየወላጆችንየመክፈልአቅምያገናዘበእንዲሆንከተቋማቱጋርይመክራል፤

፲፫ከባለስልጣኑባለሙያዎችበመረጃአያያዝናአደረጃጀትዙሪያየሚቀርቡትንየጥናትኘሮጀክቶች፣ ኘሮፖዛሎችንናሪፖርቶችንበመገምገምተግባራዊያደርጋል፤

፲፬ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፲፯ <u>የመልካም አስተዳደር፣ የህዝብ አቤቱታና ቅሬታ አፈታት ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ በአስተዳደሩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከህዝቡ የሚቀርቡ የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች፣ ቅሬታዎች እና አቤቱታዎችን በመመርመርና በማጣራት ውሳኔ ይሰጣል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤ ይገመግማል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፣

፪ በመልካም አስተዳደር መጓደል ምክንያት መፍትሄ ለማግኘት ወደ ጽህፈት ቤቱ የሚመጣ ማንኛውም ባለጉዳይ በአግባቡ የሚስተናገድበትን ስርዓት ይዘረጋል፣ በስራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤

፫ አስተዳደሩ ካወጣው አዋጅ ደንብና መመሪያ ውጪ በተሰጠ የአገልግሎት አሰጣጥ ምክንያት በመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ በኃላፊ እና በሠራተኛ ላይ የሚቀርብለትን ጥቆማ፣ አቤቱታና ቅሬታ ይቀበላል፤ ያጣራል፤ ውሳኔ ይሰጣል፤ ውሣኔውን ለአቤት ባይ በጽሑፍ ያሣውቃል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፬ በውሣኔው መሠረት እንዲፈፀም ውሣኔውን በሸኚ ደብዳቤ ለሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ይልካል፣ በውሣኔው መሠረት መፈፀሙን ይከታተላል፤

፭ የቀረበለትን አቤቱታ ወይም በከንቲባውየተመራለትን ጉዳይ ለማጣራት አስፈላጊ ሆኖሲያገኘው ማንኛውንም ሰነድ ወይም መረጃን ያስቀርባል፤ ያጣራል፤ የሚመለከተው ባለሥልጣን ወይም ሌላ ግለሰብ ጠርቶ በቃል ወይም በጽሑፍ እንዲያስረዳ ያደርጋል፤

፮ ከከንቲባው የሚመራ ጉዳይን በማጣራት የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

፯ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ ያልወጣለትና ግልፅነት የጎደለውን ጉዳይ፣ ከነዋሪው ህብረተሰብና ከሌላ አካል የሚቀርቡ አቤቱታ እና ቅሬታን ተቀብሎና አጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሲወሰን እንዲፈጸም ያደርጋል፤

፰ ጽህፈት ቤቱ በመንግስት መስሪያ ቤት ላይ ወይም የመስሪያ ቤት ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ላይ የቀረበውን ቅሬታና አቤቱታ በዝርዝር ካጣራ በኋላ ለችግሩ አግባብነት ያለው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ በሚከተለው አግባብ እንዲተገበር ያደርጋል፡-

ሀ. በአስተዳደሩ ምክር ቤት ወይም በታችኛው የአስተዳደር እርከን በተሾሙ፣ በከንቲባው በተሾመ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ኃላፊ ላይ ከሆነ አቤቱታውን አጣርቶ ለሾመው አካል የውሣኔ ሃሣብ ያቀርባል፤

ለ.ጥፋቱን የፈጠረው የመንግስት ሰራተኛ ከሆነ ለሚመለከተው መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ አግባብ ባለው ህግ መሰረት በዲሲፐሊን እንዲጠየቅና ወሳኔ እንዲሰጥበትየተጣራውን ማስረጃ አያይዞ ያቀርባል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

ሐ.ጥፋቱ በወንጀል ወይም በፍትሀ ብሔር ህግ የሚያስጠይቅ ከሆነ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ በየደረጃው ለሚመለከተው ፍትህ አካላት ይልካል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

መ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፰ (ሀ) እና (ለ) መሰረት በህግ አግባብ አስተዳደራዊእርምጃ የማይወስድ እና ውሳኔው የማይፈፀምለት ከሆነ ጽህፈት ቤቱ ውሳኔውን ለመፈፀም ፍቃደኛ ያልሆነውን ኃላፊ ወይም ሠራተኛ አግባነት ባለው ህግ እንዲጠየቅ ያደርጋል፤

፱ በመስሪያ ቤት ላይ የሚታይ የቅሬታና አቤቱታ መንስኤ ሳይንሳዊ በሆነ ጥናት እየለየ ለችግሩተገቢውን የመፍትሄ ሃሳብ ለከንቲባው በማቅረብ ቅሬታው ከምንጩ የሚቀንስበትን ተግባር ያከናውናል

፲ የጥቆማ፣ ቅሬታና አቤቱታ ማስተናገጃ ስርዓቱን ለመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ለኃላፊዎቻቸው፣ ለሠራተኞችና ለከተማው ነዋሪዎች በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም ግንዛቤ እና ስልጠና ይሰጣል፤ ሥርዓቱን ይዘረጋል፣

፲፩ የጥቆማ፣ ቅሬታና አቤቱታ አቀራረብና አወሳሰን ስርዓቱን ቀልጣፋና ዘመናዊ ያደርጋል፤ መረጃን ይይዛል፤

፲፪ በእያንዳንዱ ተቋምበታችኛው የአስተዳደር እርከንየተዘረጋውን የቅሬታና አቤቱታ መቀበያ ስርዓት በተቀመጠለት አሰራር መሰረት እየሰራ መሆኑና ተገልጋዩን በአግባቡ እያገለገለ መሆኑን በቅርብ ይከታተላል፤ ውጤታማ እንዲሆን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፲፫ በአስተዳደሩ የመንግስት ተቋማት ደረጃ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በዳሰሳ በመለየት እንዲፈቱ ያደርጋል፤ ችግሮቹን ከምንጩ ለማድረቅ ስትራቴጂዎችን በመቀየስ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

፲፬ ዓላማውንከግብለማድረስየሚረዱሌሎችተግባራትንያከናውናል፡

## ፲፰ <u>የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ</u>

ኤጀንሲው በድሬዳዋ አስተዳደር የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፱/፪ሺ፮የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፳<u>የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር</u>

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ በአስተዳደሩ የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ ችግር ሲደርስ አስቸኳይ እርዳታ የሚደርስበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፪ አደጋ ከመድረሱ በፊት ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችል አቅም እንዲጎለብት ያደርጋል፤

፫ ከእርዳታ እና አደጋ ስጋት ቅነሳ ጋር የተያያዙ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና ጥሪዎች በሙሉ ለአደጋ የሚያጋልጡ መሰረታዊ ምክንያቶችን በማስወገድ እንዲያተኩሩ ያደርጋል፤

፬ የሚሰጠው እርዳታ ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚ እድገትና ልማት አስተዋጽኦ ሊኖረው በሚቻልበት ሁኔታ መሆኑን ይከታተላል ያረጋግጣል፤

፭ በአስተዳደር ደረጃ የአደጋ ሥጋት አመራር ፖሊሲ በሁሉም የአስተዳደሩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በአግባቡና ውጤታማ በሆነ መልኩ መተግበሩን ያረጋግጣል፤

፮ የአደጋ ስጋት አመራር ፖሊሲውንና የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችን አፈፃፀም ይከታተላል ፣ ይገመግማል፤

፯ የአደጋ መንስኤዎችን በጥናት እየለየ አግባብ ባላቸው አካላት ተገቢው የዝግጅትና የመፍትሄ አማራጮች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፰ በአስተዳደሩ በሚገኙ የአደጋ ሥጋት አመራር የስራ መዋቅሮች ወይም መሪና ተጠሪ አካላት የተዘጋጁ እቅዶችና የተከናወኑ ተግባራትን ያጠናቅራል፣ ይከታተላል፤

፱ ማንኛውምየልማትእንቅስቃሴናጥረትበአደጋስጋትቅነሳ ላይ ትኩረት ማድረጉን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

፲ የአደጋ ክስተትን ለመተንበይና ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት በአስተዳደር፣ በታችኛው የአስተዳደር እርከንና በማህበረሰብ አቀፍ ደረጃ ዘመናዊና ሳይንሳዊ መሰረት ያለው የመረጃና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርአት ይዘረጋል፣

፲፩ ለአደጋ ተጋላጭየሆኑየህብረተሰብክፍሎችአቅማቸውየሚገነባበትናአደጋሊቋቋሙየሚችሉበትንሁለገብእንቅስቃሴእንዲጠናከርለሚመለከተውአካልድጋፍያደርጋል፣

፲፪ ለአደጋ ምላሽ ስራ የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆነ ቁሳቁስ ያስተዳድራል፣

፲፫ የአደጋ ክስተት ስጋት ፕሮፋይል ዝግጅት ስራን ያስተባብራል፣ ፕሮፋይሉን መነሻ በማድረግ የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ የመጠባበቂያ ዕቅድ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣

፲፬ በአስተዳደር ደረጃ የአደጋ ሥጋትአመራር የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል ፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ይዘረጋል፣ በየደረጃውም ያሉ ቅድመ ማስጠንቀቂያ እንቅስቃሴዎችን ያቀናጃል፣

፲፭ በአደጋ ስጋት አመራር ሥርዓት ውስጥ ሚና ባላቸው ተዋንያን መካከል ቅንጅታዊ አሰራርን ለማስፈንና ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ የቅንጅት መድረኮች ይመሰርታል፣ ያስተባብራል፡፡

፲፮ በአደጋ ስጋት አመራር ዙሪያ ለታችኛው የአስተዳደር እርከን እና ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፣

፲፯ የአደጋ ክስተት ስጋት ስራ አመራር ስርዓትን ለማጠናከርና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ድጋፎችን ለማግኘት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያስተባብራል፣

፲፰ ከአጎራባች ክልሎች ጋር በአካባቢ ደረጃ በሚከሰቱ የአደጋ ጉዳዮች የተቀናጀ ምላሽ የሚገኝበትን ሁኔታ በጋራ ያመቻቻል፣

፲፱ በእያንዳንዱ መሪ ተቋማት ስር የሚቋቋመው የአደጋ ስጋት ስራ አመራር መዋቅሮች አሰራራቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣

፳.በመሪ ተጠሪ እና ሌሎች ተቋማት የአደጋ አመራር መዋቅሮችና አሰራሮች መዘርጋታቸውን ይከታተላል፣

፳፩ከአደጋ ስጋት ቅነሳ ጋር ተያያዥ የሆኑ ተግባራትን የሚያከናውኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የግል ዘርፎችን፣ የማህበረሰብ ተቋማትን እንዲሁም በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ያስተባብራል አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል ፤

፳፪.ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፷፩.<u>በስልታዊ ዘዴ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት</u>

ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የድሬዳዋ አስተዳደር በስልታዊ ዘዴ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤትን ለማቋቋም በወጣው ደንብ ቁጥር ፷፮/፪ሺ፲፩ ላይ የተገለፁት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፷፪.<u>የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሥልጣን ተግባር</u>

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ የአስተዳደሩን የፀረ-ሙስና የህግ ማዕቀፎችና ስትራቴጂዎችን ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፣ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣

፪ የአስተዳደሩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች ላይ የሚሾሙ፣ የሚመደቡ፣ ወይም የሚቀጠሩ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የሥነ-ምግባርና የሙስና መከላከል ስልጠና እንዲወስዱ ያደርጋል፣

፫ ኮሚሽኑ ሙስናን ለመፈፀም የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ሲጠረጥር ወይም ጥቆማ ሲደርሰው ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት አስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ በመስራት ሂደቱ እንዲቋረጥ ወይም አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣ ሆኖም ግን በተደረገው ክትትል ሙስና ስለመፈፀሙ ጥርጣሬ ሲኖረው በህግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ላለው አካል ያቀርባል፣

፬ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የልማት ድርጅቶች እና የህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ለሙስናና ብልሹ አሠራር የተጋለጡና ሊጋለጡ የሚችሉ የአሰራር ሥርዓቶችን በማጥናት ወይም እንዲጠኑ በማድረግ የተሰጡ የመፍትሄሀሳቦችን ያቀርባል፣ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ በማይፈጽሙት ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ በህግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ላለው አካል ያቀርባል፣

፭ የህዝብ ተመራጮችን፣ የመንግስት ተሿሚዎችና የመንግስት ሠራተኞችን፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች ሀብታቸውን

እንዲያሳውቁ፣ እንዲያስመዘግቡ፣ ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ፣ መረጃ ተደራጅቶ እንዲያዝና ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፣

፮ የሀብት ምዝገባ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እና ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ሶፍትዌር ያበለጽጋል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፣ ያስተዳድራል፣ አግባብነት ያላቸው አካላት መረጃ ሲጠይቁ ይህንኑ ከዳታ ቤዝ የተገኘውን መረጃ ይሰጣል፣

፯ የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግስት ተሿሚዎች፣ የመንግስት ሠራተኞች፣ የመንግስት ልማት ድርጅቶችና የህዝባዊ ድርጅቶች የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች ከተሰጣቸው ሃላፊነት፣ ከመቆጣጠርና ከመወሰን ሥልጣን ጋር በተያያዘ የሚፈጠር የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተገቢ የሆነ የእርምት እርምጃ  እንዲወሰድ በህግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ላለው አካል ያቀርባል፣ ዝርዝሩን በደንብ ይወስናል፣

፰ ሙስናን በመታገል እና በመከላከል ረገድ ጥሩ ውጤት ያስገኙ መስሪያ ቤቶችን፣ ድርጅቶችን፣ ግለሰቦችን እና ክበባትን አወዳድሮ ዕውቅና የሚያገኙበትን እና ለሽልማት የሚበቁበትን ሥርዓት እና መለኪያ ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፱ ለህዝብ ተመራጮች፣ ለመንግስት ተሿሚዎች፣ ለመንግስት ሠራተኞች፣ ለመንግስትና ለህዝብ ድርጅቶች የሥራ ሃላፊዎች እና ሠራተኞች የሚያገለግል የሥነ-ምግባር ደንብ ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ያስጸድቃል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣

፲ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭነትን ጥናት ያካሂዳል፣ እንደአስፈላጊነቱ ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፣

፲፩ የሥነ-ምግባርግንባታእናየሙስናመከላከልተግባራትንለመፈፀምየሚያስችሉአደረጃጀቶችንበመንግስትመስሪያ ቤቶች፣በመንግስትየልማትድርጅቶችእና በህዝባዊ ድርጅቶች እና በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ያደራጃል፣

፲፪ የፀረ-ሙስናህጎችመከበራቸውንይከታተላል፣ያረጋግጣል፣ስለአፈጻፀማቸውየምክርናድጋፍአገልግሎትይሰጣል፣

፲፫ በመንግስትመስሪያቤቶች፣በመንግስትየልማትድርጅቶችእናበህዝባዊድርጅቶችውስጥየሥነ -ምግባርመከታተያክፍሎችእንዲደራጁያደርጋል፣

፲፬ የአስተዳደሩንየመንግስትመስሪያ ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና የህዝባዊ ድርጅቶችን የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍሎችን ያስተባብራል፣ አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፣

፲፭ ተመሳሳይዓላማካላቸውየፌዴራል፣የክልልእናየከተማአስተዳደርአካላትጋርአስተዳደሩንበመወከልግንኙነትናትብብርያደርጋል፣

፲፮ በሀገሪቱህግናፖሊሲመሠረትዓለምዓቀፍእናአህጉራዊየፀረ-ሙስናኮንቬንሽኖችንእናትብብሮችሥራላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

፲፯ የሥነ-ምግባርትምህርትንለማስፋፋትናመልካምሥነ-ምግባርንለመገንባትእንዲያስችለውየተለያዩየመገናኛዘዴዎችንበመጠቀምትምህርትይሰጣል፣

፲፰ የሥነ-ምግባርግንባታ፣በሙስናወንጀልምርመራእናክስየመመስረትሥልጣንከተሰጣቸውእናከሌሎችአግባብነትካላቸውአካላትየሥራአፈጻፀምሪፖርትይቀበላል፣

፲፱ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፭፫.<u>የፍትህ ጽህፈት ቤት ሥልጣን ተግባር</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ በሕግ ጉዳዮች የአስተዳደሩ ዋና አማካሪና ተወካይ ሆኖ ይሠራል፤

፪ አስተዳደሩ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራምን ያቅዳል፤ ያስተባብራል፤ በእቅዱ መሰረት መከናወኑን ያረጋግጣል፤ ይከታተላል፤ ክፍተቶችን እየለየ ድጋፍ ያደርጋል፤

፫ የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሀ ግብር ይተገብራል፤ አስፈፃሚ አካላት በዋና ዕቅዳቸው ማካተታቸውን ያረጋግጣል፤ይደግፋል አፈፃፀሙንይከታተላል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያቀርባል፤

፬ የተያዙ ወይም የታሠሩ ሰዎች ህጋዊና ሰብዓዊ መብታቸው እንዲከበር ያደርጋል፤

፭ በሰው የመነገድ እና ሰውን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል ለመከላከል ፕሮግራሞችን ይቀርፃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ይመራል፤ ያስተባብራል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፮ በአስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች የአስተዳደሩና የነዋሪው መብትና ጥቅም ወኪል ሆኖ ይከራከራል፣ ያስከብራል፣ የሚከበሩበትን ሂደት ይከታተላል ይቆጣጠራል፤

፯ የአስተዳደሩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚያደርጉትን ውል እንደአስፈላጊነቱ ይመረምራል፤ ሕጋዊነታቸውን ያረጋግጣል፤ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል ወይም ይወስዳል፤

፰ የአስተዳደሩ የመንግስት መስሪያ ቤቶችንና የመንግስት ልማት ድርጅቶችን በመወከል በማንኛውም የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በግልግል ጉባኤ በመቅረብ ክስ ይመሰርታል፣ መልስ ይሰጣል፣ የጣልቃ ገብ፣ የመቃወም፣ የይግባኝ አቤቱታና የይግባኝ መልስ ያቀርባል፤

፱ የአስተዳደሩን ህዝብ መብትና ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በግልግል ጉባኤ በመቅረብ በስሙ ክስ ይመሠረታል፤ መልስ ይሰጣል፤ የጣልቃ ገብ አቤቱታ ያቀርባል፤ ይግባኝ ይጠይቃል፤

፲ የአስተዳደሩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም የአስተዳደሩየመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች እርስ በእርሳቸው ተከራካሪ ወገን የሆኑባቸው የፍትሐብሔር ክርክሮች በድርድር እንዲያልቁ ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፩ በሌሎችሕጎችየተደነገገውእንደተጠበቀሆኖ በፍርድ ቤት የተያዙ ወይም ፍርድ ቤት ከመቅረባቸው በፊት የማያዋጡ ወይም ለአላስፈላጊ ወጪ የሚዳረጉ ጉዳዮችን በአማራጭ ክርክር መፍቻ ዘዴዎች እንዲፈቱ ያደርጋል፤

፲፪ በአስተዳደሩ ውስጥ ለሚኖሩ አቅም ለሌላቸው ነዋሪዎች ነፃ የህግ ምክር ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፫ በዐቃቢያነ ሕግ የሚሰጡ ውሣኔዎች በሕግ መሠረት መከናወናቸውን ያረጋግጣል ጉድለቶችን በጥናት አስደግፎ ይለያል፤ በግኝቱ መሠረትም እንዲታረሙ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሲሆን እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤ መልካም ተሞክሮዎችን ያስፋፋል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

፲፬ የሕግ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፤ አስተዳደሩ ያወጣቸው ህጎች በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ የህግ ወይም የውል ረቂቅ ያዘጋጃል፣ የአስተዳደሩን ህግ ማርቀቅ ሥራ በበላይነት ይመራል፤

፲፭ ነዋሪው በሕገ መንግስቱና በቻርተሩ የተሰጡትን መብቶችና ነጻነቶች እንዲያውቅና እንዲጠቀም ተገቢውን የሕግ ስልጠና ይሰጣል፤የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የህብረተሰቡን ንቃተ ህግ የሚያሳድጉ ተግባራትን ያከናውናል፤

፲፮ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት በአስተዳደሩ ፍርድ ቤት ሥልጣን ስር የሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ ክስ ይመሰርታል፤ ይከራከራል፤ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

፲፯ የተሰጠ ውሳኔ የህዝብንና የመንግስትን ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ካገኘው ይግባኝ አቤቱታ ያቀርባል፣ ይከራከራል፤

፲፰ በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችን በአስተዳደሩ ፖሊስ ተጣርቶ ሲቀርብለት ወይም እንዲቀርብለት በማድረግ ክስ ያቀርባል፣ ይከራከራል፤ የተጀመረ ምርመራ በሕግ መሠረት እንዲቆም ያዛል፤ ክስ ያነሣል ወይም የምርመራ መዝገቡ በሕጉ መሠረት ይዘጋል፤ ሌሎች ሕጋዊ ተግባራትን ያከናውናል፤

፲፱ በአስተዳደሩ አስፈፃሚ አካላት የሚጣሉ የደንብ መተላላፍ ቅጣቶችን ያስፈፅማል፣ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

፳ በካቢኔው በሚፀድቅ ወይም በፀደቀ መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት የራሳቸው የህግ አገልግሎት እንዲኖራቸው የተፈቀደላቸው አካላትን ህግ አገልግሎቶች በሚመለከት ወቅታዊ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፣ የጉዳይ አያያዛቸውን ወይም ስራቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

፳፩ የአስተዳደሩን ሕጎች ይሰበስባል፣ ያደራጃል ፣እንዲሁም ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፳፪ አስተዳደሩ የሚሰጣቸው አስተዳደራዊ ውሣኔዎች ከሕግ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፳፫ ስለ ጥብቅና ፍቃድ አሰጣጥ ደንብና መመሪያ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ በአስተዳደሩ ውስጥ በሚገኙ የአስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ቆመው መከራከር ለሚችሉ ጠበቆች በደንቡ መሠረት ፍቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፣ ሥራቸውን ይቆጣጠራል፤

፳፬ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፳፬. <u>የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር፤</u>

ቢሮውየሚከተለት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ በሥሩ ያሉትን ተቋማት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪ ብቃት ያለው፣ ውጤታማና የህዝብ አገልጋይነት አመለካከት ያለው አመራርና ፈጻሚ እንዲገነባ ስልት ይቀይሳል፣ የብቃት ማረጋገጫ ስርአት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፫ በሰው ሀብት ልማት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ የትምህርትና ስልጠና ተቋማትን በክትትልና ድጋፍ አግባብ ያስተባብራል፤

፬ የአስተዳደሩ ፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ምልመላና መረጣ በብቃት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያደርጋል፤

፭ በአስተዳደሩ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶችና በግሉ ዘርፍ የሰው ሀብት ልማት በቀጣይነት የሚለማበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት ይቀይሳል፤

፮ የፐብሊክ ሰርቪሱ የሰው ሃይል በቀጣይነት በሚለማበት እና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣

፯ የአስተዳደሩ ሲቪል ሰርቪስ በብቃትና በአፈፃፀም ላይ የተመሰረተ የክፍያና የማበረታቻ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል ፣ ውጤታማነቱን ይገመግማል ፣ አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃ ይወስዳል፤

፰ የመንግሥት ዘርፍ አቅም ግንባታ ስራዎችን ያስተባብራል፣ የመንግሥት ዘርፍ አገልግሎት በቀጣይነት የሚሻሻልበትና ውጤታማ የሚሆንበትን ስልት ይቀይሳል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

፱ የፐብሊክ ሰርቪሱ የሰው ሃብት አመራርና የተቋማዊ መረጃዎች ስርዓት በወጥነት እንዲዳብርና እንዲተገብር ያደርጋል፣ ማዕከላዊ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፤

፲ በአስተዳደሩ የመንግስት ተቋማት መካከል የተቀናጀና ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ፍሰትና ልውውጥ እንዲኖር ድጋፍ ይሰጣል፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ ስለመዋሉ ይከታተላል፤

፲፩ በመንግስት ሠራተኞች ህግ መሠረት በአስተዳደሩ ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች የሚቀርቡ የይግባኝ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል፤

፲፪ የአስተዳደሩን ፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የሚመለከቱ አስተዳደራዊ ህጎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

፲፫ የመንግስት ሰራተኞች ቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለዉ መንገድ መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን እና ዉጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

፲፬ የአስተዳደሩን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሰው ሃብት አስተዳደር በበላይነት ይመራል፣ የስራ አመራር መመሪያዎችና የአፈፃፀም መስፈርቶችን ያዘጋጃል ያስፈጽማል፤

፲፭ የመንግሥት ሠራተኞችን አስተዳደር የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ህጎችን ያመነጫል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፮ በህግ መሰረት የአስተዳደሩ መንግስት ሠራተኞችን ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ በአገልግሎት ላይ ስለማቆየት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ውሣኔ ይሰጣል፤

፲፯ የተቋም አቅም ግንባታ ስራን የሚያሳልጡ ዘመናዊ አሰራሮችንና ተሞክሮዎችን በመለየት በአስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች ላይ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ አስፈላጊዉን የቴክኒክና ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፰ ሁሉም ተቋማት ዉጤታማ አፈጻፀም እንዲኖራቸዉ የሚያደርጋቸዉን አዳዲስ አሰራሮችን በራሳቸዉ ሴክተር ባህርይ በማፈላለግ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ያበረታታል፤ ይደግፋል፤ ይከታተላል፤

፲፱ የአስተዳደሩ አስፈጻሚ አካላት መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባራት ጥናት ያካሂዳል፤ ያማክራል፤ ለካቢኔዉ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተገቢዉን ይፈጽማል፤

፳ በአስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች የሚሰጡ አገልግሎቶች ተገቢዉ ስታንዳርድ መኖሩን ይለያል፤ እንዲያዘጋጁ ያደርጋል፤ ያጸድቃል፤ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

፳፩ በአስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ አፈጻፀም ይከታተላል፣ የተገልጋዩን እርካታ ምዘና ስርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፣ ከፍተትን መሰረት ያደረገ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

፳፪ የመንግስት ሰራተኛውን ወቅታዊ አፈፃፀም ምዘና የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል፤

፳፫ የመንግስት ሰራተኛዉ በብቃትና በአፈጻፀም ላይ የተመሰረተ የምደባ፣ የደረጃና የእርከን ጭማሪ፣ የጥቅማጥቅምና የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል፣ እንዲተገበር ያደርጋል፤ ዉጤታማነቱን ይገመግማል፣ አስፈላጊዉን የማሻሻያ እርምጃ ይወስዳል፤

፳፬ የአስተዳደሩሰራተኞችየስነምግባር መከታተያ ስርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፳፭ ለመንግስት ሰራተኛዉ የሚያስፈልጉ የስራ መደቦች፣ የትምህርት፣ የስልጠናና የስራ ልምድ አጠቃላይ መመዘኛዎች ያወጣል፤

፳፮የአስተዳደሩን የመንግስት ሰራተኞች አቀጣጠር፣ አመዳደብ፣ የደረጃ እድገት፣ ዝዉዉር፣ አበልና ጥቅማ ጥቅም፣ ስልጠናና ዲሲፕሊን በህግ መሰረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

፳፯ቢሮው በሚዘረጋቸው አዳዲስ አሰራሮች፤ አደረጃጀቶችና ማኑዋሎች ዙሪያ አጫጭር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ እንዲሰጥ ያደርጋል፣

፳፰ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፳፭.<u>የንግድ እናኢንዱስትሪ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቢሮውየሚከተለትስልጣንናተግባሮችይኖሩታል፡-

፩ በስሩ ያሉትን ተቋማት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪ በንግድ፣ኢንዱስትሪናኢንቨስትመንትዘርፍየወጡፖሊሲዎችናስትራቴጂዎችተፈፃሚየሚሆኑበትንስልትይቀይሳል፣ተግባራዊምእንዲሆኑያስተባብራል፣በበላይነትይመራል፤

፫ በኢንቨስትመንትፖሊሲናህግመሰረትተግባራዊሊሆኑየሚችሉየኢንቨስትመንትፕሮጀክቶችንሃሳብያመነጫል፣እንዲጠናእናሥራላይእንዲውሉያደርጋል፤

፬ የአስተዳደሩምርትውጤቶችበሀገርውስጥናከሀገርውጭየሚተዋወቁበትንስልትይቀይሳል፣ተግባራዊምእንዲሆንያደርጋል፤

፭ በሥሩ ያሉትን ተቋማትመረጃዎችተደራጅተውእንዲያዙያደርጋል፤

፮ ከአጠቃላይአዋጆችበመነሳትበሥሩ ያሉትን ተቋማትደንቦችናመመሪዎችንያዘጋጃል፣ሲፈቀድምለሚመለከታቸው አካላትበሥራላይእንዲያውሉትያስተላልፋል፤

፯ በስሩየሚመራቸውንተቋማትአቅምይገነባል፤

፰ በአስተዳደሩኢንዱስትሪዎችየሚጠናከሩበትንስልትይቀይሳል፣በሀገርአቀፍደረጃለዘርፉየወጡፖሊሲዎችንተግባራዊነትይከታተላልአስተዳደርአቀፍስትራቴጂያዘጋጃል፣ሲፀድቅምተግባራዊእንዲሆንያደርጋል፤

፱ የኢንዱስትሪልማትንለማፋጠንየወጡፖሊሲናስትራቴጂዎችተፈጻሚየሚሆኑበትንስልትይቀይሳል፤ተግባራዊነቱንምይከታተላል፤ይደግፋል፤

፲በስሩያሉትንተቋማትያስተባብራል፣ያቀናጃል፣ይመራል፣አስፈላጊውንድጋፍያደርጋል፤

፲፩ዓላማውንለማሳካትየሚረዱሌሎችተዛማጅ ተግባራትንያከናውናል፡፡

## ፳፮.<u>የኢንቨስትመንት እና ዲያስፖራ ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር</u>

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ የኢንቨስትመንትአመችነትንያጠናል፤ያስተዋውቃል፤ያስተባብራል፤ያስፋፋል፤ምክርናየቴክኒክድጋፍይሰጣል፤

፪ እንደሀገር
እናአስተዳደርፋይዳያላቸውየኢንቨስትመንትፕሮጀክቶችንይገመግማል፤ለሚመለከተውአካልበማቅረብእንዲጸድቅያደርጋል፤

፫ የኢንቨስትመንትጥያቄዎችሲቀርቡለትበህግመሰረትመርምሮየኢንቨስትመንትፈቃድይሰጣል፤ያድሳል፤የንግድወይምኢንዱስትሪፈቃድማግኘትእንዲችሉአግባብወዳለውአካልያስተላልፋል፤

፬ ለኢንቨስትመንትፕሮጀክቶችየማምረቻናየመሸጫቦታዎች፣የፋይናንስናየብድርአገልግሎች፣የጥሬዕቃናየማምረቻመሳሪያዎችየማግኘትዕድልናየተለያዩየመሰረተልማትአውታሮችየሚሟሉበትንሁኔታያመቻቻል፤

፭ ኢንቨስትመንትንለማስፋፋትናለማበረታታትእንዲሁምየአስተዳደሩንመልካምገጽታለመገንባትየሚረዱየማስተዋወቅስራዎችንይሰራል፤ጽሑፎችንያዘጋጃል፤ያሠራጫል፤ዓውደርዕዮችን፣ዓውደጥናቶችንናሴሚኖሮችንያዘጋጃል፤

፮ ኢንቨስትመንትንለማስፋፋትበባለሀብቶች፣በመንግስታዊመሥሪያቤቶችናበሌሎችኢንቨስትመንትንበተመለከተአግባብነትባላቸውአካላትመካከልግንኙነትእንዲኖርያደርጋል፤ያስተባብራል፤

፯ የኢንቨስትመንትፈቃድየተሰጣቸውንባለሀብቶችየኢንቨስትመንትፕሮጀክቶችአፈፃፀምይከታተላል፤የኢንቨስትመንትፈቃዱየያዛቸውሁኔታዎችመከበራቸውንናማበረታቻዎችለታለመላቸውዓላማመዋላቸውንያረጋግጣል፤ከህግአግባብውጪሆነውሲገኙየኢንቨስትመንትፈቃዱንይሰርዛል፤እርምጃእንዲወሰድያደርጋል፤

፰ የድህረ-
ኢንቨስትመንትየድጋፍናክትትልሥራንለዚህዓላማከተቋቋሙአካላትጋርበቅንጅትይሰራል
፤

፱ የኢንቨስትመንትፈቃድላወጡባለሀብቶችየአንድመስኮትአገልግሎትየሚያገኙበትንአሰራርስርዓትይዘረጋል፤

፲
እንደኢንቨስትመንቱዓይነትለፕሮጀክቱየሚያስፈልገውንየመሬትፍላጎትገምግሞየመሬትዝግጅትእንዲደረግለሚመለከተውአካልያስተላልፋል፤አግባብካለውአካልጋርበመቀናጀትለአ

ስተዳደሩአቅርቦያስወስናል፤ተፈፃሚእንዲሆኑይከታተላል፤ስለፕሮጀክቱአፈጻጸምከባለሃብ ቱጋርይዋዋላል፤ከህግአግባብውጪሆነውሲገኙይሰርዛል፡፡

፲፩ለኢንቨስትመንትልማትሊውሉየሚችሉመረጃዎችንያሰባስባል፣ያጠናክራል፣ይተነትናል፣ለተ ጠቃሚዎችየሚሰራጭበትንናለልማትግብዓትሊውሉየሚችልበትንሁኔታያመቻቻል፤

፲፪የአስተዳደሩንየሀብትክምችትመነሻበማድረግየኢንቨስትመንትአማራጮችንየሚያመለክቱ ጥናቶችንያካሂዳል፣ባለሀብቶችንለመሳብየሚያስችሉስልቶችንይቀይሳል፤

፲፫በውጭአገርየሚኖሩኢትዮጵያውያንናትውልደኢትዮጵያውያንበገንዘባቸውናበእውቀታቸው በአስተዳደሩበሚካሄደውየልማትእንቅስቃሴ፤በኢንቨስትመንትየሚሳተፉበትንሁኔታያመቻ ቻል፣አፈጻጸሙንምይከታተላል፤

፲፬ከዳያስፖራውየሚገኙየእውቀትእናየቴክኖሎጂሽግግርእድሎችንበአግባቡለመጠቀምየሚያስ ችልሥርዓትመዘርጋቱንይከታተላል፤

፲፭የዳያስፖራውማህበረሰብ በአስተዳደሩ ኢንቨስትመንት እንዲሳተፍ ባሉበት ሀገር ሆነው ያሉትን የኢንቨስትመንት አማራጮችየሚያውቁበትንምቹሁኔታዎችእንዲፈጠሩይሰራል፣ያስተባብራል፤

፲፮ ዓላማውንለማሳካት የሚረዱሌሎችተዛማጅተግባራትንያከናውናል፡፡

## ፳፯.<u>የንግድ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ በአስተዳደሩ ውስጥ ንግድን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ቀልጣፋ የግብይት ስርዓትና ተገቢ የንግድ አሰራር እንዲሰፍን ያደርጋል፤

፪ አግባብ ባለው ህግ መሠረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፣ የንግድ መዝገብ ያደራጃል፤

፫ ተገቢ ያልሆነ የንግድ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችል የተሟላ ስርዓት ይዘረጋል ፣ የንግድ ህጎች መከበራቸውን ያረጋግጣል ፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

፬ በህግ መሠረት ለሸማቾች ጥበቃ ያደርጋል፣ የንግድ እቃዎችንና አገልግሎቶችን ስርጭት ይቆጣጠራል፤

፭ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት እና የቁም ከብት ግብይት የወጡ አዋጆች ፣ ደንቦችን መመሪያዎችን ያስፈፅማል፤

፮ የንግድ ትርኢትና ባዛር የሚካሄድበትን የኢግዚብሽን ማዕከል ይገነባል ፣ምርትና አገልግሎት በንግድ ትርኢትና ባዛር የሚተዋወቅበትን እና የኢንዱስትሪ ምርቶች የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል

፯ አግባብ ባለው አካል የዋጋ ቁጥጥር የተደረገባቸውን መሠረታዊ የንግድ እቃዎችና አገልግሎቶች መተግበራቸውን ይቆጣጠራል፤

፰ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ እቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፣ ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ ይወስዳል፤

፱ የሀገሪቱ ህጋዊ ስነ ልክ ስርዓት በአግባቡ መተግበሩን ይቆጣጠራል፤

፲ የንግድና የዘርፍ የሙያ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል ፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

፲፩በህጉ መሠረት የግብይት ስርዓትን በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፪ሞዴልየንግድ ማህበራትን የመተዳደሪያ ደንብና የመመስረቻ ፅሁፍ፣ የማሻሻያና የስረዛ ቃለ ጉባኤዎችን ያዘጋጃል ሥልጣን በተሰጠው አካል ተመዝግቦ ሲቀርብፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በህግ መሠረት ይሰርዛል፤

፲፫. በአስተዳደሩ የሚገኙ የገበያ ማዕከላትን ደረጃ ያወጣል ፣ ያስተዳድራል፣ ደረጃውን የጠበቁ የገበያ ማዕከላት መገንባታቸውን ይቆጣጠራል ፣ ሊያድጉና ሊስፋፉ የሚችሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፬በአስተዳደሩ የንግድ ቁጥጥርና ክትትል ስራዎችን በማከናወን ህገ ወጥ ንግድ ስራዎችን ይከታተላል፣ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ እርምጃዎችን በመውሰድ ፍትሐዊ ንግድ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤

፲፭ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፳፰.<u>የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ኤጀንሲ ስልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲውየሚከተሉትስልጣንናተግባርይኖሩታል፡፡

፩ የኢንዱስትሪልማትዘርፉከተለያዩባለድርሻአካላትየተውጣጡአባላትንባከተተመልኩየስትሪንግኮሚቴበማዋቀርበአስተዳደሩከፍተኛአመራርእንዲመራሁኔታዎችንያመቻቻል፤የአሰራርመመሪያዎችንበመቅረፅተግባራዊእንዲሆንያደርጋል፣

፪ የአነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪልማትለማፋጠንየሚረዱየድጋፍማዕቀፎችንይቀርፃል፣ውሳኔዎችንተግባራዊያደርጋል፣

፫ ሀገራዊየኢንዱስትሪልማትፖሊሲናስትራቴጂመሰረትበማድረግየአነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪልማትንለማፋጠንየሚረዱፖሊሲዎችን፣ስትራቴጂዎችን፣እቅዶችን፣ፕሮግራሞችንእናፕሮጀክቶችንያዘጋጃል፣በመንግስትሲፈቀዱምተግባራዊያደርጋል፣

፬ ለአነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱሰትሪልማትምቹሁኔታእንዲፈጠርይሠራል፣ለተወዳዳሪነታቸውእንቅፋትየሆኑጉዳዮችንበጥናትበመለየትመፍትሄእንዲያገኙያደርጋል፣

፭ በአስተዳደሩመዋቅራዊፕላንመሰረትለማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪልማትየተለየመሬትይረከባል፣መሰረተልማትእንዲሟላያደርጋል፣በካቤኔውሳኔለማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪክላስተርልማትእናበተለዩየግልአምራችባለሀብቶችእንዲተላለፉያደርጋል፤አፈፃፀሙንምይከታተላል፣ያስተዳደራል፤

፮ የአነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪልማትለመደገፍናለማስተባበርኤጀንሲውስርየተደራጁተቋማትንእንዲሁምየቀበሌተቋማትንየማስፈፀምአቅምይገነባል፣

፯ የማኑፋክቸሪንግዘርፉንየእሴትስንሰለትመሠረትበማድረግድጋፍሰጪተቋማትለአነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪበፍላጎትናበዕድገትደረጃላይየተመሠረተየሥልጠና፣የፋይናንስ፣የቴክኖሎጂግብዓቶችንእንዲያቀርቡይደግፋል፣ይከታተላል፣

፰ የአነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱሰትሪልማትንሊያፋጥኑናተወዳዳሪሊያደርጉየሚችሉምርጥተሞክሮዎችንከሀገርውስጥናከውጪሀገርለይቶያጠናል፣ይቀምራል፣ያሰራጫል፣

፱ የአነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱሰትሪዎችበዘርፍማህበራትእንዲደራጁያደርጋል፣

፲

የአነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱሰትሪልማትጠቃሚየሆኑየአዋጭነትጥናቶችናፕሮጀክትፕሮፋይሎችእንዲዘጋጁያደርጋል፣መረጃዎችንይሰበስባል፣ይተነትናል፣ያደራጃል፣ለተጠቃሚዎችያሰራጫል፣

፲፩ኢንዱስትሪያሊስቶችንለማጠናከርእናለመፍጠርየኢንተርፕረነርሺፕፕሮግራምበመቅረጽተግባራዊያደርጋል፣የኢንዱስትሪያልኤክስቴንሽንአገልግሎትበቅንጅትለአነስተኛናመካከለ

ኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪዎችበተገቢውእንዲሰጥበማድረግምርትናምርታማነትእንዲጨ
ምርድጋፍያድረጋል፤

፲፪
በአስተዳደሩለአነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪአገልግሎትየሚውሉየኢንዱስትሪክላስተርልማትበማደራጀትመሠረተልማትየተሟላላቸውየኢንዱስትሪመንደሮችእናየእርስበእርስየገበያእድልሊፈጥርየሚችልዘመናዊናአለምአቀፍደረጃውንየጠበቀየመሸጫናማሳያማእከልእንዲገነቡተገቢውንእገዛናየአቅምግንባታድጋፍያደርጋል፣

፲፫ከአነስተኛወደመካከለኛእናከመካከለኛወደከፍተኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪየሚደረገውንሽግግርይደግፋል፣አነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪዎችእርስበእርስናከከፍተኛኢንዱስትሪዎችጋርበግብዓትበአቅርቦትናበምርትእንዲሁምበቴክኖሎጂትስስርእንዲፈጥሩያደርጋል፣የሀገርውስጥናየውጪሀገርየገበያትስስርተጠቃሚእንዲሆኑይደግፋል፣

፲፬ከጥቃቅንማኑፋክችሪንግኢንተርፕራይዞችወደአነስተኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪየሚሸጋገሩበትንሥርዓትበመዘርጋትከሚመለከታቸውአካላትጋርበቅንጅትተግባራዊያደርጋል፣

፲፭የአነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪዎችንምርታማነትንለማሳደግ፣እንዲሁምየሚያመርቷቸውምርቶችየጥራትደረጃቸውንየጠበቁእናተወዳዳሪእንዲሆኑአግባብነት ካለው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

፲፮አነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪንተወዳዳሪለማድረግበጥናትላይየተመሠረተየማበረታቻ፣የእውቅናእናሽልማትሥርዓትእንዲዘረጋያደርጋል፣ተፈጻሚነቱንያረጋግጣል፤

፲፯ከተለያዩአካላትጋርበመሆንአውደ-ርዕይ፣አውደጥናትሰሚናሮችናተመሳሳይመድረኮችንበማዘጋጀትናበማስተባበርበአነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪየተመረቱምርቶችናቴክኖሎጂዎችእንዲተዋወቁናኢንዱስትሪዎችየልምድልውውጥእንዲያደርጉናበውድድርመንፈስአቅማቸውንእያሳደጉእንዲሄዱሁኔታዎችንያመቻቻል፣ይደግፋል፡፡

፲፰እንደአስፈላጊነቱለአነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪዎችየአንድመስኮትአገልግሎትየሚሰጡማዕከላትንበቅርንጫፍደረጃያቋቁማል፣እንዲቋቋሙድጋፍያደርጋል፤

፲፱የአነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪዎችየምርትደረጃስልጠናእንዲሰጣቸውበማድረግየጥራትማረጋገጫሰርቲፊኬሽንእንዲያገኙድጋፍያደርጋል፤

፳
የአነስተኛናመካከለኛማኑፋክቸሪንግኢንዱስትሪዎችበአለምአቀፍደረጃጥራትያለውምርት

ማምረትእንዲችሉለመደገፍተመሳሳይአላማካላቸውበሀገርውስጥናበወጭሀገርከሚገኙየግል ናየመንግስትተቋማትጋርትብብርያደርጋል፤

፳፩በኢንዱስትሪመንደርየሚገነቡየኢንዱስትሪፕሮጀክቶችየኢንዱስትሪፖሊሲናስትራቴጂህጐችናመመሪያዎችንመሰረትያደረጉእንዲሆኑያደርጋል፣በኢንዱስትሪመንደርከሚገቡባለሃብቶችጋርውልይፈጽማል፣በውልመሰረትመፈጸሙንይከታተላል፣ይቆጣጠራል፤

፳፪የማምረቻኢንዱስትሪውበብቃትተወዳዳሪእንዲሆንየሚያስችሉየማምረቻመሥሪያናመሸጫማዕከላትየሚገቡአካላትንበግልፅተለይቶበተዘጋጀውመስፈርትተመልምለውእንዲገቡያደርጋል፤

፳፫የማምረቻኢንዱስትሪዎችበአካባቢጥበቃየወጡህጐችንመሰረትበማድረግበፕሮጀክትደረጃእናበማምረትሂደትየተቀመጡመስፈርቶችንእንዲያሟሉድጋፍያደርጋል፣ከሚመለከታቸውአካላትጋርበጋራይሰራል፤

፳፬ የንብረትባለቤትይሆናል፣ውልይዋዋላል፣በስሙይከሳልይከሰሳል፤

፳፭ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎችተዛማጅተግባራትንያከናውናል።

## ፳፱.<u>የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮሮፖሬሽን ስልጣንና ተግባር</u>

ኮሮፐሬሽኑ በድሬዳዋ አስተዳደር አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንድስትሪ ክላስተር ልማት ኮሮፐሬሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፺፮/፪ሺ፲የተገለፀው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፴.<u>የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ በስሩ ያሉትን ተቋማት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪ የአስተዳደሩየፊዚካል፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የአጭር፣የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ እቅድ ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

፫ በአስተዳደሩ አካላት ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የበጀት ጥያቄ የበጀት ድልድል መርምሮ የተጠቃለለ ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም በህግ መሰረት ያስተዳድራል፤

፬ የፊሲካል ፖሊሲን ያጠናል፤ እንዲጠና ያደርጋል፤ ውጤቱንም ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

፭ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማትን የተመለከቱ ደንቦችና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣

፮ በገቢዎች ባለስልጣን የሚሰበሰበውን፣ እንዲሁም በብድር፣ በእርዳታ፣ በስጦታ የሚገኝ ገቢ እና ሌሎች ልዩ ልዩ ገቢዎችን ያስተዳድራል፤ በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፯ የአስተዳደሩን ገንዘብ፣ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ብድርና የተለያዩ ፈንዶችን ይጠብቃል፣

፰ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ከሀገር ውስጥ ምንጮች ይበደራል፣

፱ ስለ አስተዳደሩ የፋይናንስ አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም ጥናት እያደረገ የመፍትሄ ሀሳብ ያመነጫል፣ አስተዳደሩን ያማክራል፣

፲ የግብር እና የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ የታሪፍ ማሻሻያ እንዲሁም አዳዲስ የገቢ ምንጭ በሚመለከተው አካል ተጠንቶ ሲፀድቅ ተግባራዊነቱ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፲፩ የአስተዳደሩን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት፤ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፤ የአፈጻጸሙን ውጤታማነት ይከታተላል፤ አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፲፪ ለመንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብና ገቢ ደረሰኞች፣ ቅጻቅፆች፣ መዛግብቶች ያሳትማል፤ እንዲታተም ያደርጋል፤

፲፫ ከአስተዳደሩ አጠቃላይ ሃብት ጋር የተጣጣመ የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፬ የአስተዳደሩግብር፣የታክስገቢእናወጪአጠቃላይከአስተዳደሩእድገትና ፍላጎት አንጻር መጣጣሙን እየገመገመ ለገቢና ወጪ ፍላጎት መጨመር መንስኤ የሆኑትን ወቅታዊ ምክንያቶች እንዲመረመር፣ እንዲጠናና የመፍትሄ ሀሳብ እንዲቀርብ ያደርጋል፣

፲፭ የአስተዳደሩአስፈጻሚአካላትየመንግስትየፋይናንስፖሊሲዎች፣ሕጎች፣ደንቦችእናመመሪያ ዎችንተከትለውመሥራታቸውንይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣

፲፮ የአስተዳደሩየፋይናንስአስተዳደርያለበትንሁኔታበየጊዜውለአስተዳደሩእናለፌደራሉገንዘ ብ ሚኒስቴር ሪፖርት ያደርጋል፣

፲፯ የድሬዳዋአስተዳደርአስፈጻሚናማዘጋጃቤትአገልግሎትአካላትንእንዲሁምየታችኛውንየአ ስተዳደርእርከንየሂሳብናየግዥሰነዶችንይመረምራል፣

፲፰ የውስጥኦዲትበሴክተርመሥሪያቤቶችናየታችኛው የአስተዳደር እርከንእንዲቋቋሙ ያደርጋል፤አፈጻጸማቸውንይከታተላል፤

፲፱ የአስተዳደሩንአክሲዮኖችየሚተላለፉናየማይተላለፉየገንዘብሰነዶችንእናሌሎችተመሳሳይ ተቀማጭየገንዘብሀብቶችንይይዛል፣ ይቆጣጠራል፣

፳ የአስተዳደሩንየዕቃግዥናንብረትአስተዳደርናአጠቃቀምመመሪያያወጣል፣ተግባራዊነቱን ምይቆጣጠራል፣ይከታተላል፡፡ድጋፍያደርጋል፣በግዥሂደትለሚቀርቡቅሬታዎችንአጣርቶ ምላሽይሰጣል፣

፳፩የአደራንብረትናገንዘብያስቀምጣል፣

፳፪በአስተዳደሩሥር ባሉ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ስም የመንግስት ገንዘብ የሚቀመጥበት የባንክ ሂሳብ ሊከፍት እና የተከፈተውንም የባንክ ሂሳብ ሊዘጋ ይችላል፣

፳፫ቢሮውማናቸውምየመንግስትገንዘብየሚሰበሰብበትደረሰኝያትማል፣በሕጉመሠረትያሰራጫ ል፣ይመረምራል፣

፳፬ በአስተዳደሩ የተለያዩ ተቋማት የሚሰበሰብ ውስጠ ገቢን አሰባሰብና አጠቃቀምን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል የወጡ አፈፃፀሙንም ኦዲት ያደርጋል፤

፳፭ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፣

## ፴፩.የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ በፌዴራል መንግስት የሚዘጋጁ የተለያዩ የምጣኔ ሀብት ማህበራዊ ፖሊሲዎችን በማጥናትና ከአስተዳደሩ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ ለሚከተለው አካል ለውሳኔ ያቀርባል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣ ከፈፃሚ አካላትም ግብረ መልስ በመውሰድ ማስተካከያዎችን የማድረግ ስራ ይሰራል፤

፪ የሥነ ህዝብ የድርጊት መርሀ ግብር ያዘጋጃል፣ ለአስተዳደሩ ወቅታዊ ልማት የሚያስፈልግን ሀብት ለማፈላለግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ፕሮጀክቶችን ይቀርፃል፣ በተቀረፁ ፕሮጀክቶች መነሻ ከመንግስት ፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ከአበዳሪ ባንኮች፣ ከህዝብ እና ከሌሎች ምንጮች ገንዘብ ያፈላልጋል፣ እንዲሁም የመርሀ ገብሩን አፈፃፀም ይከታተላል፣ይገመግማል፤፤

፫ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረታዊ መረጃዎችን በማሰባሰብ የማደራጀት፣ የመተንተን፣ እነዚህንም በመጠቀም እና ከመንግስት ወቅታዊ የልማት ፖሊሲ አቅጣጫ ጋር በማጣጣም የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ እቅድ ያዘጋጃል፤

፬ የገቢ አቅም ፣የቀመር ዝግጅት፣ የታሪፍ፣ የመካከለኛ ዘመን ወጪ ማዕቀፍ፣ የጠቅላላ ምርት አገልግሎት ግመታ፣ የሥራ አጥነት፣ የሥነ-ህዝብ፣ የከተማ የእድገት አመልካች እና የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ጥናቶችን ያሰናዳል፣ የጥናቱን ውጤት ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፣ የጥናቶቹን ውጤታማነት ይገመግማል።

፭ የአስተዳደሩን የፊዚካል፣ የማህበራዊ ፣ የካፒታል፣ የገንዘብና የሰው ኃይል ሀብት ጥናት ለማካሄድ፣ መረጃ ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ማስተካከያዎችን አድርጎ ያፀድቃል፣ ለሴክተር መስሪያ ቤቶች ያሳውቃል፣ እቅዶቻቸውን በጥናቱ ውጤት ዙሪያ እንዲያቀርቡ ያደርጋል ፣ ተፈፃሚነቱን የመከታተልና የመቆጣጠር ስራ ይሰራል፣ በየጊዜው መረጃዎችን ወቅታዊ በማድረግ ቀጣይ እቅዶችን ዝግጁ የማድረግ ሥራ ያከናውናል።

፮ በሥነ-ህዝብ ልማት ጉዳዮች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ የሥነ ህዝብ ምክር ቤት ያቋቁማል፣ የሥነ ህዝብ ፖሊሲ አፈፃፀምን፣ የሥነ ህዝብ ኢንፎርሜሽን ትምህርት፣ ኮሚኒኬሽንና ኦዲዮ ቪዥዋል ያዘጋጃል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፣ ይገመግማል።

፯ በጥናት ላይ የተመረኮዘ የሥነ-ህዝብ መረጃዎችን አዘጋጅቶ ያሰራጫል።

፰ የሴክተር መስሪያ ቤቶችን የመደበኛ ሥራና የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ይከታተላል፣ የመስክ ግምገማ ያደርጋል፣ አስተዳደራዊ የሩብ፣ የግማሽ እና ዓመታዊ ሪፖርቶችን ያዘጋጃል።

፱ የአስተዳደሩን አጠቃላይ የልማት እቅድና በጀት በማዘጋጀት የተቀናጀና የሚተገበር የልማት ሥራ የአጭርና የመካከለኛ ዘመን እቅድ ያዘጋጃል፣ በየጊዜውም አስፈላጊውን የማስተካከያ ክለሳ ያደርጋል።

፲.በእርዳታ፣ በብድር እንዲሁም ከለጋሽ ድርጅቶች በሚገኝ ሀብት የሚሰሩ የአስተዳደሩ የልማት ስራዎችን እቅድ በማሰባሰብ ክትትልና ግምገማ ያካሂዳል። የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ፕሮፋይል ያዘጋጃል፣ የአስተዳደሩን የካፒታል በጀት ፍላጎት ለማጥበብ የሚያስችሉ ስራዎችን ያከናውናል።

፲፩.የአስተዳደሩን የሴክተር መስሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ጥያቄዎች ተቀብሎ መስተካከል ያለበትን አስተካክሎ ከባለበጀት መስሪያ ቤቱ ጋር በመነጋገር የውስጥ ዝውውር የማድረግና የበጀት እጥረት ሲከሰት የመጠባበቂያ በጀት ጥያቄን የመቀበልና የማስተናገድ ስራ ይሰራል።

፲፪.መረጃዎችን ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ፣ ከግል ድርጅቶች ፣ ከታተሙና ካልታተሙ የተለያዩ የማዕከላዊ ስታስቲክስ መረጃዎች በማሰባሰብ እንዲሁም የተጓደሉ መረጃዎችን ለማሟላት በተወሰኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የአስተዳደሩን ዓመታዊ ምርት እና አገልግሎት መጠን ከምርትና ከወጪ አንፃር በመገመት የአስተዳደሩን ዓመታዊ የኢኮኖሚ እድገት ያሰላል ፣ የወደፊቱን የኢኮኖሚ እድገት ይተነብያል፤

፲፫.ከአጠቃላይ የምርትና አገልግሎት ግመታ ጥናት በመነሳት ሴክተር ተኮር የሆኑ መረጃዎችን ያወጣል ፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

፲፬.የተጠቃለለ የአስተዳደሩን ዓመታዊ መሪ እቅድ እና የትኩረት አቅጣጫዎችን ያዘጋጃል፣ ያሳትማል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

፲፭.ዓላማውን ለማሳካትየሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፴፪.የመንግስት ግዢና ንብረት ባለሥልጣን

ባለሥልጣኑ በድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፷፯/፪ሺ፭ ላይ የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፴፫.የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጽህፈት ቤት ስልጣንና ተግባር

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ ዝርዝራቸው በፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚወሰን የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ እቃዎችና አገልግሎቶች እንዲሁም አስተዳደራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን እቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ያከናውናል፤

፪ በመንግስት መስሪያ ቤት ይዞታ ስር የሚገኙ አገለግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በአዋጁ እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ያስወግዳል፤

፫ ለመንግስት መስሪያ ቤቶች እንዲሁም ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግስት የልማት ድርጅቶች በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ የአገር ውስጥና የአለም አቀፍ የግዥ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

፬ የግዥ አገልግሎትን በሚመለከት የምክርና ሥልጠና አገልግሎት ይሰጣል፡፡

፫ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ እቃዎችና አገልግሎቶች የአገር ውስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም ይህንኑ የመንግስት መስሪያ ቤቶች እንዲያውቁት ያደርጋል፤

፬ የመንግስት ግዥና ንብረት የማስወገዱ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፤

፭ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ እቃዎችና አገልግሎቶች ዓለም አቀፍ ግዥ እንዲሁም አስተዳደራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን እቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ሂደት በማጠናቀቅ እቃዎቹና አገልግሎቶቹ ለተጠቃሚ አካላቱ እንዲያደርሱ ያደርጋል፤

፮ ልዩ የግዢ ሙያዊ እውቀት በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች አግባብ ካላቸው መንግስታዊ ተቋማት መረጃ ይጠይቃል፤

፯ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማች ተግራትን ያከናውናል፡፡

## ፴፪.<u>የገቢዎች ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባር፤</u>

ባለስልጣኑ የድሬዳዋ አስተዳደር የገቢዎች ባለስልጣንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፳፫/፪ሺ፬ ላይ ከተገለፀው ስልጣንና ተግባር በተጨማሪ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፤

በአስተዳደሩ ከማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች የሚመነጭ የተለያዩ ገቢዎችን ይሰበስባል፣ ለሚመለከተው አካልም ያሳውቃል፡፡

## ፴፫.<u>የሰላም ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ስልጣንና ተግባር</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ በስሩ ያሉትን ተቋማት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪ የብሔራዊ የፀጥታና የሰላም ፖሊሲን መሠረት በማድረግ የአስተዳደሩን የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳይ ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ አስተዳደር አቀፍ እስትራቴጂ ይነድፋል፤ ህግ ያመነጫል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

፫ በፀጥታ ጉዳዮች የአስተዳደሩ ዋና የፀጥታ አማካሪ ሆኖ ይሰራል፤ ለፀጥታና ሰላም አስጊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ተገቢ የሆነ አፋጣኝ እርምጃ ይወስዳል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም እንደ አግባብነቱ ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የእርምት እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፬ የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን ይዘረጋል፤ የግጭት መንስዔዎችን በጥናት ይለያል፣ ግጭት እንዳይከሰት ይከላከላል፤ ሲከሰትም ባህላዊና ዘመናዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በመጠቀም ይፈታል፤ እንዲፈቱም ያደርጋል፤

፭ የሰላም እሴት ግንባታ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ያዘጋጃል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ደረጃውን ለይቶ በመተንተን ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

፮ አለመግባባቶችና ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ያስተባብራል፤

፯ በአስተዳደሩ ልዩ ልዩ ሀይማኖትና እምነት ተከታዮች መካከል ሰላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግና ግጭትንም ለመከላከል እንዲቻል አግባብነት ካላቸዉ የፌደራል እና የአስተዳደሩየመንግሥት አካላት፣ የኃይማኖት ተቋማትና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤ የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤

፰ በግጭት መከላከል፣ አያያዝም ሆነ አፈታት፣ በነዋሪው ደህንነት፣ ሰላም እና ፀጥታ አጠባበቅ ጉዳዮች ዙሪያ አግባብነት ካላቸው የፌደራል፣ የክልል፣ የከተማ አስተዳደር እና ሌሎች አካላት ጋር የሥራ ግንኙነቶችን ያደርጋል፤ እንደአግባብነቱ ችግሮችን በተናጠል ወይም በጋራ ይፈታል፤

፱ ህግና ስርዓት መከበሩንና የህብረተሰቡ ሰላምና ደህንነት መጠበቁን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፤

፲ ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል ለማፍረስና በስውር የህዝቡንና የመንግስትን ጥቅም ጉዳት ላይ ለመጣል የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችን፣ ቡድኖችንና ድርጅቶችን በመከታተል ነዋሪውንና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፩ የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማጎልበት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ወንጀል፣ የደንብ መተላለፍ እና ተያያዥ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈፀሙ

የሚመለከታቸው አካላትን በማስተባበር ይከላከላል፤ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፣ ተፈፃሚነቱን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፪ የህግ አስከባሪ አካላት በሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አያያዝና አጠባበቅ፤ በህገ-መንግስታዊ እና በወቅታዊ ጉዳዩች ዙሪያ አቅማቸውን በመገንባት የህዝብ አገልጋይነት ሚናቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፤

፲፫ ከጸጥታ አስተዳደር ጋር የተያያዙ ቅሬታ እና አቤቱታዎችን ይቀበላል፤ ይመረምራል፤ እንደአግባብነቱ በቢሮው ወይም በተጠሪ ተቋማት ወይም በሌሎች በሚመለከታቸው አካላት ቅሬታዎቹንና አቤቱታዎቹን መልስ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፲፬ በሌሎች ህጎችና አሰራሮች ያሉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የጦር መሳሪያ ፈቃድ በሚመለከት የድጋፍ ደብዳቤ ይሰጣል፤ መረጃ ያደራጃል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

፲፭በአስተዳደሩ የሀይማኖት ተቋማት፣ ሀይማኖታዊ ማህበራትን እና ብዙሃን ማህበራት መረጃ ያደራጃል፤ ይከታተላል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፤ ህገ-ወጥ ተግባራት ላይ በተሰማሩ አካላት ላይ ህጋዊ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል ወይም እዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፮በፌደራል መንግስት የተመዘገቡ እና ፈቃድና እድሳት የተሰጣቸውን የሀይማኖት ተቋማት እና የብዙሀን ማህበራት ይመዘግባል፤ ህገ-መንግስቱንና ሌሎች ህጎችን አክብረው ስለመስራታቸው ይከታተላል፤

፲፯ የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት በህብረተሰብ ተሳትፎ ላይ እና በመስፈርቱ መሰረት ስለመከናወኑ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

፲፰የፀጥታ አስተዳደር እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፲፱የፀጥታ ሁኔታ መረጃ ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣ ውጤቱን ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፳ የመንግስት፣ የግል ተቋማትን እና ነዋሪውን በአካባቢያቸው የፀጥታ፣ ሰላም እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሚሳተፉበትን ስልት ይቀይሳል፤ ተቋማዊ አደረጃጀት ይፈጥራል፤ ያስተባብራል፤

፳፩የሰላማዊ ሰልፍ በአደባባይ ላይ ለሚከናወኑ የተለያዩ ፕሮግራሞች እና ስብሰባዎች የአስተዳደሩን ከንቲባ ያማክራል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፳፪ህጋዊ የሆኑ ሰላማዊ ሰልፎች በሰላም የሚጠናቀቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል ህገ ወጥ በሆኑ ሰላማዊ ሰልፎች፣ ሌሎች ፕሮግራሞች እና ስብሰባዎችን ላይ በህግ አግባብ እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፤

፳፫የፀጥታ ምክር ቤት አደረጃጀትና አሰራር አጥንቶ ለአስተዳደሩ ከንቲባ ያቀርባል፤ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፳፬በህብረተሰብ ተሳትፎ አቀናጅቶ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ በመስራት ደንብ መተላለፍን እንዲቀንስ ያደርጋል፤

፳፭በአስተዳደሩ ባሉ በገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ሚሊሻ ያደራጃል፣ ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑማቴሪያሎች እንዲሟሉ ያደርጋል፣ ያሰማራል፣ የሥራ አፈፃፀማቸውን ይገመግማል፣ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤

፳፮በሚመለከተው አካል ጥያቄ ሲቀርብ የብሔራዊ ተጠባባቂ ጦር አባላት እንዲመለመሉ ያደርጋል፤

፳፯በተለያዩ ሃይማኖቶችና እምነት ተከታዮች መካከል ሰላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግና ግጭትንም ለመከላከል እንዲቻል አግባብ ካላቸው የመንግስት አካላት፣ የሃይማኖት ተቋማትና ከሌሎች ማናቸውም አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

፳፰በሃይማኖት ሽፋን የሚደረግ አክራሪነትና ጽንፈኝነትን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፳፱ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፴፮<u>ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና የነዋሪዎች መረጃ ኤጀንሲ</u>

በአዋጅ ቁጥር ፵፬/፪ሺ፰ የተቋቋመው የወሳኝ ኩነት ምዝገባጽህፈት ቤት የወሳኝ ኩነት ምዝገባና የነዋሪዎች መረጃ ኤጀንሲ በሚል ስያሜ ተሻሽሎ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡

፩ የክብር መዝገብ ሹም በኤጀንሲው ይመደባል፣ እንደ አስፈላጊነቱም በታችኛው የአስተዳደር እርከን እንዲመደብ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሠራል፣

፪ በአስተዳደሩ ወሣኝ ኩነት በአግባቡ መመዝገቡንና ምስክር ወረቀት መስጠቱን ያረጋግጣል፤

፫ የወሳኝ ኩነት የድርጊት መርሃ ግብር እና የመረጃ አጠቃቀም ሥርዓትን አግባብ ካለው የፌዴራል አካል ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፬ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አስፈላጊነትና ጥቅም አስመልክቶ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለአስተዳደሩ ነዋሪዎች ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል፤

፭ የወሣኝ ኩነት ምዝገባ የጥራትና የሽፋን ደረጃ ጥናት ያካሂዳል፣ በምዝገባ ሂደት በታዩ የአሠራር ችግሮች ላይ የመፍትሔ ሃሣቦች ያቀርባል፤

፮ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተስማሚ በሆነ ቴክኖሎጂ እየታገዘ የሚሰራበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፯ የልደት፣ የጋብቻ፣ የፍቺና የሞት፣ ጉዲፈቻ ምስክር ወረቀት ያዘጋጃል ማስረጃ ይሰጣል፣ ለዚህ የሚያገለግሉ ፎርማቶችና ካርዶች ያዘጋጃል ያሠራጫል፤

፰ የነዋሪነት መታወቂያና ሌሎች የነዋሪዎች አገልግሎቶችን ይሰጣል፤እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፱ ነዋሪዎችን በሚመለከት ስታስቲክስ መዝግቦ ይይዛል፣ በዚህም የአስተዳደሩ የወሊድ፣ የሞት፣ የሚገቡና የሚወጡ ነዋሪዎች አሃዝ በየጊዜው እየመዘገበ የአስተዳደሩ ህዝብ ብዛት እንዲታወቅ የሚችልበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲ ስታስቲክሳዊ መረጃዎችን ያጠናቅራል፣ ለሚመለከተውም የአስተዳደሩና የፌደራል የመንግሥት አካል ያስተላልፋል፤

፲፩ በአስተዳደሩ የሚያገለግሉ የክብር መዝገቦች ዝግጅትና ሥርጭትን በሚመለከት አግባብ ካለው የፌዴራል አካል ጋር ይተባበራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ የክብር መዝገቦች ለሁሉም የከተማና የገጠር ቀበሌ አስተዳደሮች መስራጨታቸውን ያረጋግጣል፤

፲፪ በአዋጅ መሠረት የተሰበሰቡ የወሳኝ ኩነት መረጃዎች አግባብ ላለው የፌዴራል አካል በወቅቱ እንዲተላለፍ አስፈላጊውን የማስተባበር ሥራ ያከናወናል፤

፲፫ ለሚሰጠው አገልግሎት የታሪፍ ተመን ያወጣል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፬ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፴፯.<u>የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ የህብረተሰቡን ፀጥታ ፣ ማህበራዊና የጤና ደህንነት በጠበቀ መልኩ የወጡ ህጎች ተግባራዊ እንዲሆን ደንቦችና መመሪያዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ፣ ያስከብራል፤

፪ ህገ-ወጥ ግንባታ፣ ህገ-ወጥ ንግድ እና ሌሎች የደንብ መተላለፎችን ይከላከላል ፣ ሲከሰትም በህግ መሠረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል ፣ ያስወስዳል፤

፫ የአስተዳደሩን ህጎች ደንቦች ፣ ኮዶች፣ መመሪያዎችና ደረጃዎች በማሰባሰብ ደንብና ስርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ያስከብራል፤

፬ የከተማ ስነ-ስርዓት ከማስከበር ጋር በተያያዘ በተለያዩ መንግስታዊ አካላት፣ ማህበራትና ድርጅቶች ሲጠየቅ ድጋፍ ያደርጋል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ስልጠና ይሰጣል፤

፭ የከተማው ነዋሪዎች የአስተዳደሩን ደንብና ስርዓቶች የሚያከብሩ እንዲሆኑ የተለያዩ ስልቶችን ይቀይሳል፣ የትምህርትና የስልጠና መመሪያዎችን በሚመለከተው አካል እንዲወጣ ያደርጋል ፣ ስራ ላይ ያውላል ፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፮ የከተማው ነዋሪ የአካባቢውን ፀጥታና ስነ ስርዓት አክባሪና አስከባሪ እንዲሆንና ደንብና ስርዓትን በሚጥሱ አካላት ላይ ጥቆማ እንዲቀርብ ያስተባብራል፣ ያበረታታል፤

፯ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፴፰.<u>የሚሊሻ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፡-

፩ በአስተዳደሩ ባሉ በገጠር ቀበሌዎች ውስጥ የሚሊሻ ሃይል ያደራጃል፣ ያሰማራል፣ የሥራ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤

፪ የሚሊሻ ሃይል አቅም እንዲጎለብት ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊና ስነ-አምሯዊ ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፫ የሰለጠኑየሚሊሻአባላትንወታደራዊትጥቅናአልባሳትእንዲኖራቸውያደርጋል፣ ስምሪትይሰጣል፤

፬ በአስተዳደሩ ገጠር ቀበሌዎች ያለውን የፀጥታ ሁኔታን ጥናት በማድረግ እና በአካባቢው ያለውን የጥበቃ ክፍተት በተመለከተ ከህብረተሰቡ ጋር በመወያየት በተለይም አዲስ የሚሊሻ ሃይል አስፈላጊነትን በማሳመን ለአካባቢው የሚሰማራ የሚሊሻ አባል ከራሱ ከህብረተሰቡ መካከል እንዲመለመል ያስተባብራል፤

፭ የአስተዳደሩ ህዝብ ደህንነት፣ ሰላምና ፀጥታ መጠበቁን በሚመለከት ከፌዴራልና ከክልል መስተዳድሮች (አጎራባች ወረዳና ቀበሌዎች) የፀጥታ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣

፮ የሚሊሺያ ኃይል አደረጃጀት፣ ምልመላ፣ ሥልጠና፣ ሎጂስቲክስና ስምሪት እስታንዳርዶች በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል፤

፯ በገጠር ቀበሌዎች ውስጥ በመደበኛነት ተመድበው እየሰሩ ላሉ የሚሊሻ አባላት ሎጀስቲክ ያቀርባል፣ ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎች እንዲሟሉ ያደርጋል፣

፰ የገጠር ቀበሌ ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፱ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፴፱.<u>የግብርና ፤ የውሃ ፤ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ በስሩ ያሉትን ተቋማት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪ የገጠርመሬትናተፈጥሮሀብትአጠቃቀምንከአስተዳደሩተጨባጭሁኔታጋርበማገናዘብበቀጣይናዘላቂልማትተስማሚፕሮግራምአዘጋጅቶያቀርባል፣ተግባራዊቱንምይከታተላል፣

፫ በገጠርቀበሌዎችየተፈጥሮሀብትአጠቃቀም፣በእርሻእናበግጦሽመሬትይገባኛልለሚነሱአለመግባባቶችናግጭቶችአግባብካላቸውአካላትጋርበመሆንፈጣንምላሽናውሳኔይሰጣል፣

፬ በገጠርቀበሌአስተዳደሮችየግብርናናገጠርልማትፖሊሲንናስትራቴጂዎችንበላቀደረጃለማስፈፀምበሚያስችልመልኩአስተዳደሩንወክሎአቅማቸውንይገነባል፣ይከታተላል፣

፭ የግብርናልማትስራበጥምርግብርና፣በአርብቶአደርናበከፊልአርብቶአደርአካባቢእንዲስፋፋያደርጋል፣

፮ በገጠርያለውንየኢንቨስትመንትምቹሁኔታአግባብካላቸውአካላትጋርበመሆንመረጃእንዲሰበሰብያደርጋል፣

፯ በገጠርለግንባታናለኢንቨስትመንትለሚቀርቡየመሬትጥያቄዎችአግባብካላቸውአካላትጋርበመሆንውሳኔይሰጣል፣

፰ ለህዝብጥቅምሲባልየገጠርየመሬትይዞታእንዲለቀቅሲደረግለባለይዞታውካሳየሚከፈልበትንሁኔታይወስናል፣

፱ውሃ፣ማዕድንናኢነርጂሴክተሮችየወጡፖሊሲዎችእናስትራቴጂዎችከአስተዳደሩተጨባጭሁኔታጋርተጣጥሞእንዲተገበሩያደርጋል፣

፲የህብረት ስራ ማህበራት እንዲስፋፋ ፣ እንዲጠናከሩና በምርት በአገልግሎት ዘርፍ ተሳትፎአቸው እንዲጎለብት ያደርጋል፣

፲፩በምርትግብይትየእሴትሰንሰለትመሻሻልአግባብካላቸውአካላትጋርበመሆንደጋፊሚናይጫወታል፣

፲፪በገጠርለምግብዋስትናየተጋለጡአካባቢዎችናየህብረተሰብክፍሎችንይለያል፣መንስኤውንያጠናል፣ይደግፋል፣በዘርፉየተሰማሩባለድርሻአካላትንያስተባብራል፣በበላይነትይመራል፣

፲፫በልዩልዩአካላትለሚከናወኑተግባራትየፋይናንስናቁሳቁስድጋፍናየሀብትድልድልንያስተባብራል፣

፲፬በገጠሩየሥራእድልፈጠራየሚስፋፋበትንሁኔታያመቻቻል፣መርሃግብሮችእየተዘጋጁእንዲተገበሩያደርጋልየስልጠናእናየአቅምግንባታሥራዎችእንዲስፋፉያደርጋል፣

፲፭በሥራእድልማስፋፋትጠቃሚየሆኑየገጠርኢንተርፕራይዞችናማህበራትእንዲስፋፉአግባብነትካላቸውአካላትጋርበመሆንምችችትያደርጋል፣

፲፮አላማውንለማሳካትየሚረዱሌሎች ተዛማጅተግባራትንያከናውናል፡፡

## ፵.<u>የውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

ጽህፈትቤቱየሚከተሉትስልጣንናተግባሮችይኖሩታል፡-

፩ የአስተዳደሩንአጠቃላይየልማትእቅድመሰረትበማድረግየውሃሀብትልማትእቅድንያዘጋጃል፣

፪ በአስተዳደሩየውሃሀብትንየተመለከቱመረጃዎችንይሰበስባል፣ያጠናቅራል፣

፫ በአስተዳደሩየውሃሀብትጥናትዲዛይንያከናውናል፣

፬ በአስተዳደሩየሚካሄዱየውሃፕሮጀክቶችንያስፈጽማል፣

፭ የገጠሩህብረተሰብበውሃልማትሥራላይእንዲሳተፍያደራጃል፣ያስተምራል፣ለህብረተሰቡየቴክኒክድጋፍይሰጣል፣

፮ የገጠርመጠጥውሃኮንስትራክሽንእናየመስኖልማትስራዎችያካሂዳል፣

፯ በአስተዳደሩበውሃልማትኮንስትራክሽንእናለውሃሥራባለሙያዎችየሥራናየሙያፍቃድይሰጣል፣ከዚህምስራገቢያሰባስባል፤

፰ ለውሃጉድጓድቁፋሮድርጅቶችናባለሀብቶችበጥናትላይተመርኩዞፍቃድይሰጣል፣ያድሳል፣ይሰርዛል፣ተገቢውንቁጥጥርያደርጋል፣

፱ የአስተዳደሩየውሃሀብትመጠን፣ጥራትእናስርጭትያጠናል፣መረጃይሰበስባል፣ያጠናቅራል፣በአስተዳደሩየሚተገበሩየውሃሀብትልማትስራዎችንያስተባብራል፣ይከታተላል፣የሙያድጋፍምይሰጣል፣

፲ ውሃንአምርቶእናአሽጎበማሰራጨትየተሰማሩአካላትእንቅስቃሴንይከታተላል፣ይደግፋል፣ይቆጣጠራል፤

፲፩ የውሃጥራትቁጥጥርንአግባብካላቸውአካላትጋርበመሆንያከናውናል፣የማሻሻያእርምጃምበቅንጅትይወስዳል፣

፲፪ የማዕድንሀብትንበመጠበቅረገድከሚመለከታቸውአካላትጋርይተባበራል፣በአስተዳደሩውስጥለሚካሄድየማዕድንናኢነርጂልማትሥራዎችአስፈላጊውንድጋፍይሰጣል፣

፲፫ ለባህላዊየማዕድንአምራቾችየኮንስትራክሽንናሌሎችማዕድናትየመፈለግ፣የመመርመርናየማልማትፍቃድይሰጣል፣ያድሳል፣ይሰርዛል፣ተገቢውንቁጥጥርያደርጋል፣በህጉመሰረትገቢይሰበስባል፣

፲፬ በአማራጭየኢነርጂልማትላይልዩልዩየልማትሀይሎችእንዲሳተፉምቹሁኔታይፈጥራል፣ይደግፋል፣

፲፭ የባዮጋዝቴክኖሎጂእንዲስፋፋያደርጋል፣የቴክኖሎጂማሻሻያእንቅስቃሴዎችንይደግፋል፣ያቀናጃል፣

፲፮ የተሻሻሉኢነርጂቆጣቢምድጃዎችእንዲስፋፉናእንዲሰራጩያደርጋል፣በሌሎችአካላትየሚሰራጩናበገበያላይያሉትምደረጃቸውንመጠበቃቸውንይከታተላል፣አግባብያለውማሻሻያእንዲወስድያደርጋል፣

፲፯ የሶላርቴክኖሎጂዎችንስርጭትይደግፋል፣በልዩልዩአካላትየሚሰራጩትንደረጃቸውንይቆጣጠራል፣እርምጃይወስዳል፣

፲፰ በአስተዳደሩያሉታዳሽየኢነርጂአማራጮችንበመፈተሽስራላይየሚውሉበትንሁኔታያመቻቻል፣አተገባበሩንምይከታተላል፣

፲፱ በአስተዳደሩውስጥበገጠርየኤሌክትሪክኃይልአቅርቦትለማዳረስበነዳጅእናበአማራጭኃይልየሚሰሩናአነስተኛኃይልማመንጫጣቢያዎችስለሚቋቋሙበትሁኔታያጠናል፣ሲፈቀድምበስራላይእንዲውልያደርጋል፣አነስተኛየኤሌክትሪክኃይልየማመንጨትናማሰራጨትፍቃድይሰጣል፣ይቆጣጠራል፣

፳ በውሃማዕድንናኢነርጂዘርፍለተሰማሩአገልግሎትሰጪዎችየብቃትማረጋገጫይሰጣል፣

፳፩ ዓላማውንለማሳካትየሚረዱሌሎችተዛማጅ ተግባራትንያከናውናል፡፡

## ፵፩.የግብርና እና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ በሀገሪቱበየዘርፉየወጡ ፖሊሲናስትራቴጂዎችንመሰረትበማድረግበአስተዳደሩውስጥየግብርናልማትእንዲስፋፋ ያደርጋል፣ያበረታታል፣

፪ በሀገሪቱየመሬትአጠቃቀምናአስተዳደርደንብናከዚህጋርበተያያዘበሚወጡትዝርዝርየአፈ ፃፀምመመሪያዎችመሰረትበግለሰብ፣በማህበራትናበድርጅትለሚለሙየገጠርመሬቶችየይ ዞታዋስትናማረጋገጫሰነድይሰጣል፣

፫ የመሬትባለይዞታዎችበመሬትየመጠቀምናይዞታውንየማስተላለፍመብቶችምበገጠርመሬ ትአስተዳደርናአጠቃቀምህግመሰረትተግባራዊእንዲሆንያደርጋል፣

፬ በገጠርመሬትየመጠቀምመብትየተሰጠውግለሰብ፣ማህበርናድርጅትመሬቱንለተፈለገውተ ግባርማዋሉንናበገጠር መሬት አጠቃቀምፕላንመሰረትመተግበሩንበየጊዜውይከታተላል፣ይገመግማል፣ይቆጣጠራል፣

፭ የአስተዳደሩንየግብርናልማትለማፋጠንየሚረዱየምርመርየስልጠናፕሮግራሞችንያካሂዳ ልአግባብካላቸውአካላትጋርበመተባበርየግብርናቴክኖሎጂዎችእንዲስፋፉያደርጋል፣

፮ በአስተዳደሩውስጥየግብርናኤክስቴንሽንአገልግሎትይሰጣል፣

፯ በአስተዳደሩውስጥየግብርናኢንቨስትመንትእንዲስፋፋአግባብካላቸውአካላትጋርበመተባ በርሁኔታዎችንያመቻቻል፣ለአገርውስጥኢንቨስተሮችአስፈላጊውንሙያዊየቴክኒክድጋፍ ይሰጣል፣

፰ የአስተዳደሩንየተፈጥሮሀብትልማት፣ጥበቃናአጠቃቀምፖሊሲዎች፣አዋጆችደንቦችናመ መሪያዎችበአስተዳደሩውስጥተግባራዊእንዲሆኑያደርጋል፣

፱ በአስተዳደሩውስጥየሚገኙተፋሰሶችንያጠናል፣በተፋሰሶቹውስጥየሚገኙየተፈጥሮሀብቶች ክምችትናስርጭትየተመለከተመረጃዎችንሰብስቦበማደራጀትለተጠቃሚእንዲደርሱእና በጥናቱመሰረትተፋሰሶቹእንዲለሙያደርጋል፣

፲ የሜትሪዮሎጂመረጃዎችንይሰበስባል፣ያሰራጫል፣

፲፩ የግብርናምርትበጥራትየሚመረትበትንናለገበያየሚቀርብበትንእንዲሁምየሚጎለብትበት ንምቹሁኔታይፈጥራል፤

፲፪ አርብቶአደሩቋሚየግብርናእንቅስቃሴእንዲኖረውምቹሁኔታይፈጥራል፤አግባብያለውንድ ጋፍይሰጣል፤

፲፫ በህግተለይቶ በተሰጠውስልጣንመሰረትበግብርናውዘርፍለተሰማሩአገልግሎትሰጪዎችየብቃትማረጋገጫሰርተፍኬትይሰጣል፤

፲፬ በአስተዳደሩውስጥየገጠርልማቱንለማፋጠንየሚያስችሉምርጥናየተሻሻሉየእጽዋትዝርያዎች፣የገጠርቴክኖሎጂማስፋፊያማዕከላት፣የገበሬማሰልጠኛማእከላትንእናሌሎችተቋማትንያቋቁማል፣ያስተዳድራል፣

፲፭ በአስተዳደሩውስጥበሰብልዝርያዎችላይየሚደረጉህገወጥእንቅስቃሴዎችንእናዝውውሮችይቆጣጠራል፣እርምጃይወስዳል፣

፲፮ ወደአስተዳደሩበሚገቡናከአስተዳደሩበሚወጡእጽዋትናአዝርዕትተዋጽዖውጤቶችላይተገቢውንየኳራንቲንቁጥጥርያደርጋል፣

፲፯ በእጽዋትበሽታዎችላይጥናትያካሂዳል፣በጥናቱውጤትመሰረትየመቆጣጠሪያስልቶችንበማዘጋጀትተግባራዊያደርጋል፣

፲፰ የፀረ- ተባይኬሚካሎችንያስተዳድራል፣ይቆጣጠራል፣ጊዜያለፈባቸውንመድሃኒቶችንምእንዲወገዱያደርጋል፣

፲፱ የአስተዳደሩንየተፈጥሮሀብቶችማለትምብዝሃህይወትን፣ውኃን፣አፈርንናማዕድናትን፣አጠቃቀማቸውበዘለቄታዊመርህላይየተመሰረተእንዲሆንሁኔታዎችንያመቻቻል፣ተፈጥሮአዊናሰውሰራሽየአካባቢሀብቶችእንዲጠኑናአስፈላጊውእንክብካቤእንዲደረግላቸውዘዴዎችንይቀይሳል፣ሲፈቀድምተግባራዊያደርጋል፤

፳ አግባብካላቸውመስሪያቤቶችጋርበመሆንበረሀማነትንለመከላከል፣የድርቅንአሉታዊተፅእኖእናየስ- ምህዳርመዛነፍንለመቀነስየሚያስችሉጥናቶችንያካሂዳል፣መፍትሔዎችንያዘጋጃል፤ለአተገባበራቸውምምቹሁኔታንይፈጥራል፣

፳፩ አግባብነትባላቸውየህግድንጋጌዎችመሰረትየደንጥበቃግዴታዎችመከበራቸውንያረጋግጣል፤

፳፪ የአስተዳደሩንየአካባቢናየደንእንዲሁምለአየርንብረትየማይበገርአረንጓዴኢኮኖሚንየሚመለከትሪፖርትያቀርባል፤

፳፫ አነስተኛየደንልማት፣በግል፣ወልይዞታእናበተፋሰስውስጥእንዲለማናጥቅምላይእንዲውልሥርዓትይዘረጋል፣ትግበራውንምያረጋግጣል፤

፳፬የአስተዳደሩየተፈጥሮደንእንዲጠበቅናእንደአስፈላጊነቱዘላቂጥቅምላይእንዲውልሥርዓት ይዘረጋልትግበራውንምያረጋግጣል፤

፳፭የተጎዱናየተራቆቱየደንመሬቶችእንዲያገግሙናየአካባቢዋናኢኮኖሚያዊጠቀሜታቸውእን ዲሻሻልስርዓትይዘረጋል፣ትግበራውንምያረጋግጣል፣

፳፮በአስተዳደሩየመሬትአጠቃቀምፕላንመሠረትለደንልማትየሚሆኑቦታዎችንበመለየትየተለ ያዩሀገርበቀልዛፎችየሚለሙበትንስልትይቀይሳል፣ሲፈቀድምተግባራዊያደርጋል፤

፳፯በአስተዳደሩበተለያዩስነ-ምህዳርየሚገኘውየብዝሃህይወትልማትበአግባቡእንዲተገበር፣ጥበቃውምህብረተሰቡንባሳተ ፈመልኩእንዲከናወንየመፍትሔአቅጣጫያስቀምጣል፤መረጃዎችንያሰባስባል፤ተግባራዊነ ቱንይከታተላል፤

፳፰የአስተዳደሩንየደንናየደንውጤቶችንየአስተዳደሩንህግበተከተለመንገድእንዲከናወንየመከ ታተልናየመደገፍሥራይሠራል፤

፳፱የችግኝጣቢያዎችንያስፋፋል፣ያስተዳድራል፤

፴ህገ-ወጥየደንጭፍጨፋናየዱርአራዊትግድያእንዳይኖርየሚከላከሉህጎችእንዲወጡየመነሻሀሳብ ለአስተዳደሩያቀርባል፣ህጉሲፀድቅምተግባራዊያደርጋል፤

፴፩አላማውንለማሳካትየሚረዱሌሎች ተዛማጅተግባራትንያከናውናል፡፡

## ፵፪.<u>የህብረትስራማህበራትማደረጃ፣ ማስፋፊያ፣የግብዓትእናግብይትኤጀንሲ</u>

ኤጀንሲውየሚከተሉትሥልጣንናተግባሮችይኖሩታል፡-

፩ ለህብረትሥራማህበራትእንቅስቃሴናዕድገትየሚበጁየፖሊሲሀሳቦችንያቀርባል፣አፈፃፀሙ ንይከታተላል፤

፪ የህብረትሥራማህበራትአደረጃጀትበህብረትሥራማህበራትመሠረትእንዲሆንያደርጋል፤

፫ በፌደራልመንግሥትናበአስተዳደሩየወጡፖሊሲዎችናሕጎችበሥራላይመዋላቸውንያረጋ ግጣል፤

፬ ባህላዊናሀገርበቀልራስአገዝማህበራትወደዘመናዊየህብረት ሥራ ማህበርየሚያድጉበትንጥናትናምርምርያደርጋል፣የጥናቱንውጤትያስተዋውቃል፤ያሰራ ጫልበተግባርመተርጎሙንምይከታተላል፤

፭ የህብረትሥራዕሴቶች፤መርሆዎች፤አደረጃጀትናጠቀሜታበህብረተሰቡይበልጥእንዲታወ ቁያደርጋል፤

፮ በአስተዳደሩደረጃየሚደራጁየህብረትሥራማህበራትንይመዘግባል፤የሕጋዊሰውነትማረጋገጫየምስክርወረቀትይሰጣል፤ሂሳባቸውንይመረምራል፤ሂሳብአጣሪምይመድባል፤ሲፈርሱምከመዝገብ
ይሰርዛል፣የህብረትሥራማህበራትየሂሳብአያያዝናምርመራእንዲኖርያደርጋል፤

፯ የህብረትስራማህበራትምርቶችገበያእንዲያገኙሙያዊድጋፍይሰጣል፤ሸማቹናአምራቹበቀጥታየሚገናኙበትንሁኔታያመቻቻል፤

፰ የህብረትስራማህበራትምርቶችተጨማሪዕሴትወይምዋጋእንዲኖራቸው፤ወደኢንዱስትሪምርትነትእንዲለወጡናየእጅጥበብምርቶችእንዲያድጉየሙያናየቴክኒክድጋፍያደርጋል፤

፱ ለህብረትሥራማህበራትእድገትየሚበጁፕሮጀክቶችንበማጥናትናበማዘጋጀትከሚመለከታቸውአካላትጋርበመነጋገርማህበራትድጋፍየሚያገኙበትንመንገድያመቻቻል፤

፲ በአስተዳደሩተደራጅተውየሚገኙየህበረትሥራማህበራትከሌሎችክልሎችየህብረትሥራማህበራትጋርየምርት፣ የገበያ፣ የመረጃየልምድልውውጥእንዲያደርጉሁኔታዎችንያመቻቻል፤

፲፩ የህብረትስራማህበራትእንቅስቃሴንእናዕድገትንለማፋጠንከህብረትሥራማህበራትጋርግንኙነትካላቸውየሀገርውስጥድርጅቶችጋርግንኙነትያደርጋል፤

፲፪ እንደየህብረትሥራማህበራቱአይነትናደረጃሊለዋወጥየሚችልየማህበራትሞዴልየመተዳደሪያደንብያዘጋጃልያሰራጫል፤

፲፫ ለግብርናልማቱአስፈላጊየሆኑየግብዓትናየእርሻመሣሪያዎችለተጠቃሚውበብድርእንዲቀርብያደርጋል፤ተጠቃሚዎችየብድርአገልግሎትየሚያገኙበትንሁኔታያመቻቻል፤

፲፬ በተቋሙበልዩልዩመንገድየሚቀርቡብድሮችንበተያዘለትጊዜያሰባስባል፣ እንዲሰበሰብያደርጋል፤

፲፭ የአምራቹምርትግብይትእንዲጎለብትየመረጃ፤መሠረተልማትናቴክኒካዊድጋፍይሰጣል፤

፲፮ በገጠሩየምርትግብይትእንቅስቃሴላይጥናትናምርምርያደርጋል፤የተሻለአሰራርናየግብይትሥርዓትእንዲፈጠርስልቶችይቀይሳል፣ ተግባራዊያደርጋል፤

፲፯ የግብርናግብዓትናምርጥዘርበማምረትናበማከፋፈልሥራላይለሚሰማሩአካላትየሙያብቃትማረጋገጫይሰጣል፤አስፈላጊውንምቁጥጥርያደርጋል፤

፲፰ ዓላማውንለማሳካትየሚረዱሌሎችተግባራትንያከናውናል፡፡

## ፵፫ <u>የገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲውየሚከተሉትሥልጣንናተግባራትይኖሩታል፡-

፩ በገጠር ስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ መሠረት በማድረግ የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪ በፌደራል ደረጃ የገጠር የስራ ፈጠራና ምግብ ዋስትና ስራዎችን ለማስፋፋትና ለማልማት የወጡትን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መሠረት በማድረግ በገጠር አስተዳደር ውስጥ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን እንዲስፋፉና እንዲለሙ ያደርጋል፤

፫ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለማስፋፋትና ድጋፎችን ለመስጠት እንዲሁም የገጠር ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መመሪያዎችን፣ ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

፬ የምግብዋስትናፕሮግራሞችንበገጠርውስጥለማስፈጸምፈንድወይምሌላየገቢምንጭያፈላል ጋል፣ጉዳዩበሚመለከተውየመንግስትአካል፣መንግስታዊባልሆኑድርጅቶች፣ወይምበህዝብማ ህበራትስራላይእንዲውልያደርጋል፣ይቆጣጠራል፤

፭ በገጠርየሥራዕድልፈጠራናየምግብዋስትናንለማረጋገጥአስፈላጊየሆኑጉዳዮችእንደሥራአጥ ዜጎችማስረጃ፣መስራትየሚችሉእናየማይችሉ፣ለማህበራዊችግሮችተጋላጭየሆኑትንበጥናትበ መለየት መረጃይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤

፮ የስራእድልፈጠራስትራቴጂንከግብለማድረስበገጠርውስጥያሉሥራአጦችንይመዘግባል፤ግን ዛቤይፈጥራል፤ያለውንየሥራዕድልበመለየትእንደየፍላጎታቸውበግልወይምበማህበርበመደ ራጀትእንዲሰሩሁኔታዎችንያመቻቻል፤

፯ በገጠር የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም በመቅረፅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፰ የገጠር ምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አኳያ ከመንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፱ በገጠር ህብረተሰብ ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፣ ለስራ ዕድል ፈጠራ እና ለጥቃቅን ኢንተርፕራየይዞች ልማትና ተወዳዳሪነት እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን ለመለየት ጥናቶች እንዲከናወኑ ያደርጋል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

፲ በገጠር ውስጥ የሚገኙትን ስራ አጥ የሆኑ ወጣቶችና ሴቶችን በብዛት በማሳተፍ አምራች ዜጋ ሊያደርጉ የሚችሉ የተለያዩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ፕሮጀክቶች እንዲጠኑ ያደርጋል፣ ተግባረዊነታቸውንና ውጤት ማስገኘታቸውን ያረጋግጣል፤

፲፩ በገጠር የአንድ ማዕከል አገልግሎት ለማደራጅት፣ ለማጠናከር አገልግሎቱን በአግባቡ ለመስጠት የሚያስችል የተሻሻሉ አዳዲስ ስርዓቶችን በመዘርጋት የማዕከሉን አቋም ይገነባል፤

፲፪ የገጠር ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የሚውል መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤ የድጋፎች ፍላጎትና አቅርቦት ጥናት ያካሂዳል፤

፲፫ የገጠር ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፲፬ የስልጠናና የብድር አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂና የማምረቻ መሳሪያች አቅርቦት ያመቻቻል፣ የገበያ ትስስር ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፭ ለገጠር ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻ፣ የመሸጫ ቦታ ግንብቶ ያቀርባል፤ ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን እንዲያኙ ያደርጋል፤

፲፮ ሞዴል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ይፈጥራል፣ ያሸጋግራል፤

፲፯ የገጠር ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ እንዲስፋፋ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፣ ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ እና ከግል ድርጅቶች ጋር ትስስር በመፍጠር ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ተፈፃሚነቱን ያረጋግጣል፣

፲፰ በገጠር ውስጥ የሚገኙ ነዋሪዎች የስራ ዕድል መፍጠር እንዲችሉ ስልጠናዎችን በመለየትና በመቀመር እውቀትና ክህሎት እንዲቀስሙ ያደርጋል፣ ያበረታታል፣ የንግድ ስራ ክህሎት የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

፲፱ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ስራቸውን በአግባቡ መምራት እና ምርትና ምርታማነታቸውን ማሳደግ እንዲችሉ ሙያዊ ድጋፍና ክትትል አገልግሎት ይሰጣል፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

፳ በገጠር ውስጥ የሚገኙትን ነዋሪዎች አምራች ዜጋ ለማድረግ የሚያስችሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ፕሮጀክቶችን ያጠናል፣ ፕሮጀክት ፕሮፋይል በማዘጋጀት ፍላጎቱ ይለያል ስራ አጥ ወጣቶች ያስተዋውቃል፣ በስራው እንዲሰማሩ ያበረታታል፤

፳፩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተሰማሩበትን የስራ ዘርፍ በአግባቡ ማካሄድ የሚያስችላቸው የፋይናንስ ብድር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፳፪ ዓላማውንከግብሊያደርሱየሚችሉሌሎችተዛማጅተግባራትንያከናውናል፤

## ፵፬<u>የእንሰሳት ሀብት ልማትና ጤና ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲውየሚከተሉት ሥልጣንና ተግባርይኖሩታል፡-

፩ ዘርፉንበሚመለከትተቀደምሲልየወጡናለወደፊትምየሚወጡፖሊሲዎችን፣ስትራቴጅዎችን፣አዋጆቸን፣ደንቦችንናመመሪያዎችንበአስተዳደሩውስጥያስፈጽማል፣ይቆጣጠራል፤

፪ የአስተዳደሩንየእንስሳትልማትአካባቢዎችበልማትቀጠናዎችይለያል፣የልማትቀጠናውንመሠረትያደረገስትራቴጅክዕቅድያዘጋጃል፣ይተገብራል፣ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፤

፫ የአስተዳደሩንየእንስሳትሃብትየስጋ፣የወተት፣የእንቁላልናየማርምርትናጥራትበማሳደግየእንስሳትሃብትልማትዘርፉንአስተዳደራዊናሃገራዊኢኮኖሚያዊጠቀሜታእንዲጨምርያደርጋል፤

፬ የእንስሳትመኖልማትያካሂዳል፣የተከለሉየግጦሽመሬትናየእንስሳትዘርእንዲሻሻልናእንዲጠበቅያደርጋል፤

፭ የእንስሳትሀብትልማትናጤናአጠባበቅፖኬጆችንይፈጽማል፣ይከታተላል፣ከምርምርአካላትጋርበመቀናጀትያሻሽላል፣አዳዲሶችንምእየለየይቀርፃል፣ቴክኖሎጂዎችንአባዝቶያስፋፋል፣

፮ የእንስሳትየመጠጥውሃእጥረትባለባቸውአካባቢዎችከሚመለከታቸውአካላትጋርበመተባበርየውሃእጥረቱእንዲፈታያደርጋል፤ሁኔታዎችንያመቻቻል፤

፯ የሀገረሰብእንስሳትንለመጠበቅከሚመለከታቸውአካላትጋርበቅንጅትይሰራል፣

፰ የእንስሳትሀብትልማቱንከደንልማቱጋርበማቀናጀትለመጠቀምከሚመለከታቸውአካላትጋርበቅንጅትይሰራል፣

፱ አግባብካላቸውባለድርሻዎችጋርበመተባበርህጋዊናህገ-ወጥየቁምእንሰሳት፣የቆዳናሌጦ፣የእንሰሳትእርድ፣የግልእንስሳትመድሃኒትናየክሊኒክአገልግሎትንግድናሌሎችንግዶችንይቆጣጠራል፣የብቃትመስፈርቶችንያወጣል፣ማስረጃይሰጣል፣የኳራንቲንናየፍተሻማዕከላትንያደራጃል፤

፲ የቁራአገልግሎትየብቃትናየጥራትፍተሻያካሂዳል፣ከአጎራባችክልሎችናከፌዴራሉመንግሥትአካላትጋርበቅርበትይሰራል፣በሚወጡህጎችመሰረትእርምጃዎችንይወስዳል፣እንዲወሰዱያደርጋል፤

፲፩ በአስተዳደሩውስጥየእንስሳትንግድየጉዞመስመሮችንበመለየትበሕግእንዲታወቁናተገቢውንጥበቃእንዲያገኙያደርጋል፣የኳራንቲንናየፍተሻማዕከላትንያደራጃል፣ከአጎራባችክልሎችናከፌደራልመንግስትአካላትጋርበትብብርይሰራል፣

፲፪ የበሽታመከላከልንመሰረትያደረገየእንስሳትጤናአገልግሎትይሰጣል፣የእንስሳትበሽታዎች ምርመራ፣አሰሳናቁጥጥርሥራዎችንያካሂዳል፣አስፈላጊሆኖከተገኘየእንስሳትእንቅስቃሴንይ ገድባል፣በአስተዳደሩየበሽታቁጥጥርስትራቴጂይነድፋል፣ከበሽታነጻቀጣናዎችንያቋቁማል፣

፲፫ ለዘርፉልማትናጥበቃየሚያስፈልጉመሰረተልማቶችንያቋቁማል፣እንዲቋቋሙናእንዲስፋፉ ያደርጋል፣አደረጃጀታቸውንበማሟላትሙሉአገልግሎትእንዲሰጡያደርጋል፤

፲፬ ለተጠቃሚውህብረተሰብከበሽታነፃየሆነናጥራቱየተጠበቀስጋእንዲቀርብበቄራዎችየስጋም ርመራእንዲካሄድያደርጋል፣ከሚመለከታቸውአካላትጋርበመተባበርደረጃቸውንየጠበቁቄራ ዎችበአስተዳደሩተገቢውንአገልግሎትእንዲሰጡያደርጋል፣

፲፭ በዘርፉየተሰማሩባለሀብቶችጥራትናደረጃውንየጠበቀየእንሰሳትምርትእንዲያቀርቡናአገል ግሎትእንዲሰጡያደርጋል፣የአቅምግንባታሥራናየሙያድጋፍይሰጣል፤

፲፮ የእንስሳትብዜትናዝርያማሻሻልከኤጀንሲውስትራቴጅጋርአገናዝቦበመወሰንናበመቅረጽየ ብዜትማዕከሉተደራሽነትግብእንዲሳካእቅድያወጣል፣ያስተባብራል፣ያደራጃል፣ይከታተላል ፣

፲፯ የእንስሳትብዜትናዝርያማሻሻልንበሚመለከትመረጃዎችንይሰበስባል፣ሙያዊግምገማያካሂ ዳል፣ውጤቱንመነሻበማድረግስራውንለማጠናከርአመቺየሥራፕሮግራምይነድፋል፣ለሚመ ለከታቸውያስተላልፋል፣

፲፰ የእንስሳትበሽታዎችስርጭትንያጠናል፤በበሽታስርጭትየተነሳመወሰድያለባቸውንእርምጃ ዎችለመንግስትናለአርቢዎችያሳውቃል፤ለእንስሳትአርቢዎችየእንስሳትህክምናናየክትባት አገልግልትይሰጣል፤እንዲሰጥያደርጋል፤የዕብድውሻበሽታመከላከያክትባትይሰጣል፤

፲፱ ለእንስሳትአርቢዎችየማዳቀልአገልግሎትይሰጣል፤የተሻሻለየግብርናቴክኖሎጂውጤቶች፣ ምርጥዘርለአርሶአደርእንዲዳረስያደርጋል፤ውጤታማነታቸውንምይከታተላል፤ትምህርት ናሥልጠናእንዲሁምየሙያድጋፍይሰጣል፤

፳ ዓላማውንለማሳካትየሚረዱሌሎችተግባራትንያከናውናል፡፡

## ፵፭.<u>የጤና ቢሮ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ በስሩ ያሉትን ተቋማት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪ የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲና ደረጃ በማገናዘብ የአስተዳደሩን የጤና አገልግሎት ደረጃ ያወጣል፣ ተግባራዊነቱንያረጋግጣል፣ በጤና ጉዳዮችላይ የግንዛቤ ማስፋፊያ ትምህርት ለአስተዳደሩ ነዋሪዎች አመቺ በሆነ ዘዴይሰጣል፣ ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፫ የአስተዳደሩን የጤና አጠባበቅ ፖሊሲዎች ያመነጫል፣ ለፖሊሲው አተገባበር የሚረዳ መርሀ ግብር እና ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤

፬ የባህል ህክምና ከዘመናዊ ህክምና ጎን ተጣናክሮ የሚካሄድበትን ስልት ይቀይሳል፤

፭ የጤና ተቋማትን የመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀምን ይቆጣጠራል፤

፮ የእናቶችና ህፃናት ጤና ክብካቤ አገልግሎት ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፤

፯ በአስተዳደሩ ውስጥ የሚከናወኑ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከል ስራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም የሌሎች በሽታዎችን መከላከልና ቁጥጥር ተግባራት መረጃ ያጠናቅራል፣ በአግባቡ በመተንተን ለሚመለከታቸው ያቀርባል፤

፰ በአስተዳደሩ ባለቤትነት ሥር የሚገኙትን ሆስፒታሎችና የመድኃኒት ፋርማሲዎች እንደአስፈላጊነቱ የህክምና መሳሪያዎች ጥገና ማዕከልና እንዲሁም በአስተዳደሩ ለሚቋቋሙ ጤና ተቋማት  የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

፱ በባለሀብቶችና በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ለሚቋቋሙ የጤና አገልግሎት ድርጅቶች፣ የምርመራ ማዕከላትና የከተማ አቀፍ የጡና አገልግሎት ፕሮግራሞች ለሚሰጡ ጤና ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ የወጣውን ደረጃ ጠብቀው መስራታቸውን ይቆጣጠራል፤

፲ ቢሮው የሚያስተዳድራቸው፣ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና በባለሀብቶች በተያዙ ተቋማት ውስጥ በህዝብ ጤና አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች የተወሰነውን ደረጃ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

፲፩ የጤና ፖሊሲውንና የአቅም ግንባታ ስትራቴጂውን መሠረት በማድረግ፣ የጤና አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል የሚረዱ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችና ሥራዎች የሚካሄዱበት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ስልቶችን ይቀይሳል፣ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤

፲፪ ተላላፊበሽታዎችን ለመከላከልና ለማጥፋት ክትባቶች እንዲሰጡ ፣የአካባቢ ጤና አገልግሎትእንዲስፋፋ፣ የጤናአጠባበቅ ትምህርት እና የቁጥጥር መረጃ እንዲሰራጭና ሌሎች ተገቢ እርምጃዎችም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፫ በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ አስቸኳይ እርምጃና ሪፖርት የሚጠይቁ ተላላፊ በሽታዎች ሲከሰቱ ተገቢና ፈጣን እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፬ በአስተዳደሩ የህብረተሰቡን ጤና የሚመለከቱ ህጎች እንዲወጡ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ያዘጋጃል፣ የወጡት ህጎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ ይከታተላል፤

፲፭ የምግብ አምራቾችና አቅራቢ ድርጅቶች ደህንነቱ የተጠበቀና ለጤና ተስማሚ የሆነ ምግብ ለሰው ልጅ እንዲያቀርቡ ያስተምራል፣ ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል፣ ሙያው የሚያዘውን ሁሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለተፈፃሚነቱ ይሰራል፤

፲፮ ለጤና ተቋማት የግንባታ ፍቃድ ከመሰጠቱ በፊትና ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ አገልግሎት ሳይጀመር የህክምና ተቋሙ ተገቢውን ስታንዳርድ ማሟላቱንና በጤና ላይ ጉዳት እንደማያስከትል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያረጋግጣል፤

፲፯ በአስተዳደሩና በሌሎችም አካላትየሚገነቡትን የመጠጥ ውሃ ግንባታዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ቢሮው ብቁ መሆኑን ሲያረጋግጥ ለህዝብ አገልግሎት እንዲውሉ ያደርጋል፤

፲፰ የህዝብ ጤንነት ችግሮችን ለመፍታት ተግባራዊ ጥናቶችን በማካሄድ የጥናቱን ግኝት ለመፍትሄነት እንዲውል ያደርጋል፤

፲፱ የአደገኛ መድኃኒት ቁጥጥርን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያደርጋል፣ ይህንኑ በሚመለከት ለህብረተሰቡ መረጃን ያሰራጫል፤

፳ ስልጣኑ በግልጽ ለሌላ አካል በህግ ካልሰጠ በስተቀር በዘርፉ ለሚሰሩ አካላት ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤

፳፩ ከሜዲካል ዶክተሮችና ስፔሻሊስቶች በስተቀር ለሁሉም የዲግሪና ዲፕሎማ የጤና ባለሙያዎች እንዲሁም ባህላዊ ህክምና አዋቂዎች የሙያ ፍቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፤

፳፪ የአካባቢ ጤና አጠባበቅን በተመለከተ ህግ እንዲወጣ ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ያቀርባል፣ በወጣው ህግ መሠረትም ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

፳፫ የአስተዳደሩን የጤና መረጃ ያጠናቅራል፣ ያደራጃል፤

፳፬ መንግስታዊ ጤና ተቋሚት የሚሰጡትን የሕክምና መረጃዎች ያረጋግጣል፤ ይከታተላል፤ እንደ አስፈላጊነቱም እርምጃ ይወስዳል፡፡

፳፭ በስሩ ያሉትን የመንግስት ጤና ተቋማትን ይመራል፣ እስትራቴጂክና ዓመታዊ እቅድ ያወጣል፣ ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤

፳፮ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፵፮.የምግብ፣ መድሃኒትና ጤና ነክ ቁጥጥር ባለስልጣንሥልጣንና ተግባር

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ የምግቦችን ደህንነትና ጥራት፣ የመድኃኒቶችን ደህንነት፣ ፈዋሽነት፣ ጥራትና አግባባዊ አጠቃቀም፣ የህክምና ባለሙያዎችን ብቃትና አሰራር፣ የኃይጅን፣ የአካባቢ ጤናን እና የጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማት የቁጥጥር ደረጃዎች ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

፪ ለጤና ተቋማት፣ የመድኃኒት አከፋፋዮችና ማከማቻዎች፣ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ያግዳል፤ ይሰርዛል፤

፫ ለጤና ነክ ተቋማት የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፤ የንጽህናና የጤና ደረጃዎችን ማሟላታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፬ የህጻናት ማቆያዎችን የሙያ ደረጃ ፈቃድ ይሰጣል፣ የንጽህና፣ የጤንነትና ተስማሚነት ደረጃዎችን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፭ የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ የጤና ባለሙያዎች እና የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማትን በሚመለከት የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

፮ በምግብ ወይም በመድኃኒት መመረዝ ወይም መበከል ምክንያት ለሚደርስ ሞት፣ የጤንነት መታወክ መንስኤ የሆነውን ንጥረ ነገር ልዩ ልዩ ናሙናዎች በመውሰድ ምንነታቸው እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤ እርምጃ ይወስዳል፤

፯ አግባብ ባለው ህግ መሰረት የባህል መድሀኒት አዋቂዎች በባህል ህክምና ዘርፍ ላይ እንዲሰማሩ ፈቃድ ይሰጣል፣ የባህል መድሀኒቱ ምን አይነት ይዘት እንዳለው በላብራቶሪ እንዲመረመር ያደርጋል፣ ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

፰ በደረጃው ለተፈቀደለት የጤና ባለሙያ የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ያግዳል ይሰርዛል፤

፱ የባህል ሕክምና ከዘመናዊ ሕክምና ጎን ተጠናክሮ የሚሄድበትን ሥልት ይቀይሳል፤

፲ በባለስልጣኑ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማት ላይ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ምግቦች፣ መድኃኒቶችና ጥሬ ዕቃዎችቻቸው በአግባቡ መወገዳቸውን ያረጋግጣል፤

፲፩ ሕገወጥ ምግቦችን፣ መድኃኒቶችና፣ የጤና አገልግሎቶችን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤

፲፪ አስተዳደሩ በሚቆጣጠራቸው የጤና ተቋማት አበረታች መድሀኒቶች፣ የናርኮቲክ መድኃኒት፣ ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች እና ፕሪከርሰር ኬሚካሎች ለህሙማን ማዘዝን፣ ማደልን፣ አጠቃቀምን፣ መመዝገብንና ሪፖርት ማድረግን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊ ሲሆን ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፫ በአስተዳደሩሥርያሉጤናነክቁጥጥርየሚደረግባቸውተቋማትተገቢውንየሐይጅንናአካባቢ ጤናአገልግሎትመስፈርትማሟላታቸውንያረጋግጣል፤

፲፬ የሥነ-ምግባርግድፈትበሚያሳዩየጤናባለሙያዎችላይተገቢውንእርምጃይወስዳል፤

፲፭ ለሥራውአስፈላጊየሆኑትንየጥራትምርመራላቦራቶሪያደራጃል፤ለሚሰጠውአገልግሎትበህ ጉ መሰረትክፍያያስከፍላል፤

፲፮ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፵፯.<u>የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ሥልጣንና ተግባር</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉትስልጣንናተግባርይኖሩታል፡-

፩ የህብረተሰብ ጤናና ሥነ ምግብን በተመለከተ አስተዳደራዊ የምርምር አጀንዳ ይቀርጻል፣ በአጀንዳው ላይ የተሞረኮዘ ምርምር ያካሂዳል፣ በተገኙ የምርምር ውጤቶች ላይ ተመርኩዞ የስትራቴጂ ሐሳብ ያቀርባል፣ የምርምር ውጤቶችን ያሰራጫል፣የተሰሩ ምርምሮችን ፋይዳ ይገመግማል፣

፪ በአስተዳደሩ ውስጥ የሚከናወኑ ምርምሮች የሚቀናጁበትና ውጤታማ የሚሆኑበት አሰራር ይዘረጋል፣ አስተዳደር አቀፍ የምርምር መረጃ ቋት ይመሰርታል፣ተቋማት ለሚያከናውኗቸው ምርምሮች ድጋፍ ይሰጣል፣

፫ ለህብረተሰቡ ዋና ዋና የጤና ችግሮች የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማስረጽ ክትባትን፣ የበሽታ መመርመሪያ ኪቶችን፣የምግብ ሳይንስና ሥነ ምግብ ምርምር ውጤቶችን እና ሌሎች ለጤና አገልግሎት ጠቃሚ የሆኑ ግብዓቶችንና ውጤቶችን እንደ አስፈላጊነቱ ያመርታል ወይም በአገር ውስጥ በስፋት እንዲመረቱ ሳይንሳዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

፬ በስርዓተ ጤናውና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ምርምሮች እና ግምገማዎችን በማድረግ በሽታን ለመከላከል እና ጤናን ለማበልፀግ የሚደረገውን ጥረት ያግዛል፤

፭ የአካባቢና የሥራ ቦታ ደህንነትና ጤና መሠረት ያደረጉ የህብረተሰብ ጤና ምርምሮች ይሰራል፣

፮ በአስተዳደሩ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች፣በሥነ ምግብ፣ በአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣በጤና ሥርዓቱ ላይ እና በሌሎች መሰል የጤና ጉዳዮች ላይ ዳሰሳና ቅኝቶችን ያካሂዳል፣

፯ የምግብ እጥረትና ያለመመጣጠን የሚያስከትሏቸው በሽታዎች የሚወገዱበትን መንገድና በቤተሰብ ደረጃ የአመጋገብ ሁኔታ እንዲሻሻል የሚያስችል ምርምር ያካሂዳል፣መረጃዎችን ይሰበስባል፣ያጠናቅራል፣

፰ በባህል መድሃኒቶችና ሕክምና ዘዴዎች እንዲሁም በዘመናዊ መድሃኒቶች ላይ ምርምር ያካሂዳል፣ፍቱንነታቸው፣ደህንነታቸው እና ጥራታቸው የተረጋገጠላቸው የባህል መድሃኒቶች በዘመናዊ መንገድ የሚመሩባቸውን ስልቶች ይቀይሳል፣በጤና አገልግሎት ሥርዓት ውስጥ እንዲካተቱ የሚያስችላቸው ሀሳብ ያቀርባል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለባህል መድሃኒቶች የሚውሉ ዕፅዋቶች እንዳይጠፉ ለመጠበቅ ለሚደረጉ ሥራዎች የበኩሉን ድጋፍ ያደርጋል፣

፱ በአስተዳደሩ በማንኛውም የህብረተሰብ ጤና ምርምር ላይ የምርምር ተሳታፊውን ደህንነት፣መረጃ አያያዝ፣ በአጠቃላይ የምርምር ሥነ ምግባርን እና መልካም የምርምር አሰራርን የሚመለከቱ የአፈጻጸም መመሪያዎችና ማንዋሎችን ያወጣል፣

፲ ከአገር ውስጥ የምርምር ተቋማት ጋር የጋራ ምርምሮችን ይሰራል፣እንደአስፈላጊነቱ ምርምሮችን በገንዘብ ድጋፍ በመስጠት በሌሎች አካላት አማካኝነት እንዲሰሩ ያደርጋል፤

፲፩ በህብረተሰብ ጤና ምርምር፣በድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥርና የላብራቶሪ ጥራት ስርዓት በሚመለከት ተጨባጭ ፍላጎቶችን መሰረት ያደረጉ የአጭር ጊዜና የስራ ላይ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣የረጅም ጊዜ ሥልጠናዎችን በመስጠት ረገድም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በትብብር ይሰራል፣እንደ አስፈላጊነቱ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

፲፪ በአስተዳደሩበተመረጡየጤናሥጋቶች፣በወረርሽኝመልክየሚከሰቱበሽታዎች፣የሥነምግብ ችግርእናየአካባቢጤናችግሮችንበተመለከተቅኝትያካሂዳል፣ይተነትናል፣ወቅታዊመረጃያ ሰራጫል፣

፲፫ የህብረተሰብጤናአደጋዎችንለመከላከልናለመቀነስስልቶችንይቀይሳል፣ የአፈጻጸም መመሪያዎችን ያወጣል፣የዝግጅትና የምላሽ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ አቅም ይገነባል፣

ጠንካራ የቅንጅትና የትብብር ሥርዓት ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፣ የህብረተሰብ ጤና አደጋ ተጋላጭነት ዳሰሳና የጤና አደጋ ሥጋት ትንተና ያካሂዳል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣

፲፬ በአስተዳደሩወረርሽኝወይምሌላየህብረተሰብጤናአደጋወይምየህብረተሰብጤናአደጋሥጋቶችሲከሠቱእንደአግባብነቱበቦታውተገኝቶምርመራያካሂዳል፣ክስተቶችን ያረጋግጣል፣ ያነቃል፣ ያስጠነቅቃል፣ መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል ያሰራጫል፣ ግብአቶችን ያንቀሳቅሳል ወይም እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋል፣ እንደ አስፈላጊነቱ በየደረጃው ለሚደረጉ የምላሽ ሥራዎች ድጋፍ ይሰጣል፣

፲፭ ኢንስቲትዩቱከሌሎችአካላትጋርበመተባበርበሰውሰራሽወይምበተፈጥሮአደጋዎችምክንያትጤናንበተመለከተበአስተዳደሩየደረሰውንጉዳትበማጥናትወደነበረበትእንዲመለስድጋፍ ያደርጋል፣

፲፮ በአገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ቀውስ የሚያስከትሉ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎችን በተመለከተ አገር አቀፍ የጤና ህጎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣

፲፯ በአስተዳደሩየሪፈራልዲያግኖስቲክእናአናሌቲካልየላብራቶሪምርመራአገልግሎትይሰጣል፣

፲፰ የአስተዳደሩላብራቶሪዎችብሔራዊናዓለምአቀፋዊየላብራቶሪጥራትሥርዓትንየሚመለከቱመስፈርቶችንእንዲያሟሉየሚያስችላቸውንስራዎችይሰራል፣

፲፱ ኢንስቲትዩቱለሚሰጠውየማማከር፣ሪፈራል ዲያግኖስቲክ እና አናሌቲካል የላብራቶሪ አገልግሎቶች መንግስት ባፀደቀው ተመን መሰረት ክፍያ ያስከፍላል፣

፳ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ውል ይዋዋላል፣በስሙ ይከሳል፣ይከሰሳል፣

፳፩ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፵፰.<u>የትምህርት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ በስሩ ያሉትን ተቋማት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪ በአስተዳደሩየትምህርት አደረጃጀትና አስተዳደር፣ህብረተሰቡን፣ መምህራንና ተማሪዎች ተቀናጅተው እንዲሳተፉ ያደርጋል፤

፫ የትምህርት ፖሊሲ እና ስልጠናን መሠረት ያደረገ መመሪያዎች እና ማንዋሎች ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ በዘርፉ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፤

፬ በአገሪቱ የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ መሠረት የአስተዳደሩን የትምህርትና ስልጠና እቅድ እና ፕሮግራሞች ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል፤

፭ የአስተዳደሩን የትምህርት መረጃ ያጠናቅራል፣ ያደራጃል፤

፮ በየትምህርት እርከኑ የሚሰለጥኑ መምህራን በችሎታቸው በታታሪነታቸውና ባላቸው የሙያ ዝንባሌ እየተመለመሉ ለማስተማር ብቁ የሚያደርጋቸውን ስልጠናዎች ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፣ ተከታታይ ስልጠናዎች ይሰጣል፤

፯ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራንን ለማጠናከር እንዲሰለጥኑ ያደርጋል ፣ያሰለጥናል፣ ለአካል ጉዳተኞች መምህራንና ተማሪዎች ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

፰ በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙና እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት የመማር እድል የሚያገኙበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ መደበኛ ያልሆነ ትምህርትም እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

፱ የሀገሪቱንየትምህትናስልጠናፖሊሲናሥርዓተትምህርት መሠረት በማድረግ የመማሪያና ማስተማሪያ መፃህፍት ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤›

፲ የአስተዳደሩንየመጀመሪያደረጃትምህርትመልቀቂያፈተናያዘጋጃል፣ያስፈፅማል፣የምስክር ወረቀትይሰጣል፣በሀገርአቀፍደረጃተዘጋጅተውየሚሰጡየሁለተኛደረጃመልቀቂያ ፈተናዎችን ያስፈጽማል፤

፲፩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የትምህርት ቤቶችን የስፖርት ውድድር ያስተባብራል፤

፲፪ የአገሪቱን የትምህርት ስታንዳርድ ተከትሎ እና የአስተዳደሩን የአካባቢ ሁኔታ በማገናዘብ የአፀደ ህፃናት ፣ የአንደኛ ደረጃ ፣ የሁለተኛ ደረጃ፣ የጎልማሶች፣ የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ፣ አዳሪ ትምህርት ቤቶችንና የትምህርት መገናኛ ዘዴዎችን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

፲፫ ለትምህርት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ የግንባታ ሥራዎችን ያቅዳል ፣ ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፬ በመገናኛ ዘዴዎች የተደገፉ የትምህርት ፕሮግራሞች እንዲሰጡ ያደርጋል፤ መደበኛና ኢ-መደበኛ የትምህርት ፕሮግራሞች የሚስፋፉበትን ሁኔታ ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፭ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚወጡ የብቃት መመዘኛዎች መሠረት መምህራንና ሌሎች የትምህርት ባለሙያዎችን ያሰለጥናል፣ እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፤ ሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፮ ትምህርት ቤቶችን ማቋቋምና ማስፋፋት ለሚፈልጉ አካላት የመረጃ አገልግሎትና ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፯ በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች የመማርና ማስተማር ሂደት በበላይነት ይመራል፤ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፲፰ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚወጣውን መስፈርት መሠረት በማድረግ በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙትን ትምህርት ቤቶች ደረጃ እንዲሻሻል ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

፲፱ የመጀመሪያደረጃትምህርትፈተናእናሌሎችፈተናዎችለመተግበርደንብይቀርፃል፣በሚመለከተውአካልሲፀድቅምያስፈጽማል፤

፳ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፵፱.<u>የድሬዳዋ አስተዳደር የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ</u>

ኮሌጁ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፩ ንዑስ አንቀጽ ፬ በተሻሻለው መሠረት በድሬዳዋ አስተዳደር የመምህራን ትምህርትኮሌጅ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፲፪/፪ሺ፲ የተገለፀው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፶.<u>የሴቶች፣ ህፃናት እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ አገራዊ የሆኑሴቶችን፣ ህፃናትን፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች እና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችንየሚመለከቱፖሊሲዎች፣ዝርዝርየህግማዕቀፎችእንዲሁምስታንዳርዶችበአስተዳደሩተፈጻሚ እንዲሆንያደርጋል፤

፪ በሁሉም አስፈፃሚ አካላት፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶችና ሌሎች የአስተዳደሩ አካላት የስርዓተ ፆታንና ህጻናት ጉዳይ በዕቅዳቸው ላይ ማካተታቸውን ይከታተላል፤ በስርዓተ ፆታ እኩልነት ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ይደርጋል፤

፫ በአስተዳደሩ መንግስት አካላት የሚዘጋጁ ሕጎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶች፣ የአረጋዊያን፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የህጻናትና

ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መብትና ደህንነት ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤

፬ የሴቶች፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች ህጻናትና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መብቶች ስለመጣሳቸው መረጃ ሲደርሰው ከሚመለከተው አካል ጋር ጉዳዩን በማጣራት ውጤቱን ለሚመለከተው የፍትህ አካል ያስተላልፋል፤ ይከታተላል፤

፭ የሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያንና መብቶችን በተመለከተ ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎችን ይሰራል፣ ይመራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

፮ የሴቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ህጻናት፣ አረጋውያን እና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች አቅም የሚያጎለብቱ ትምህርታዊ፣ ሙያዊና የተጨማሪ ክህሎት ሥልጠናዎችን ያዘጋጃል፤ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፯ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ሴቶች፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች በማህበራት እንዲደራጁ፣ የብድርና የቁጠባ አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፰ ለሴቶች፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ህጻናት ፣ጎዳና ተዳዳሪዎች እና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መብት፣ ደህንነትና ጥቅም የሚሰሩ ማህበራት እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

፱ የሴቶች፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ህጻናትና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በሁሉም የተባበረ ጥረት መፍትሄ እንዲያገኝ ያስተባብራል፤ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤

፲ ለሴቶች፣ ህጻናትና አካል ጉዳተኛ ልዩ ትኩረት በመስጠት በሁሉም የልማት ሥራዎች ውስጥ ፍላጎቶቻቸው እንዲካተት ለማድረግ ከተለያየ ጥቃት መከላከል፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞቻቸው ለማስከበር ከሌሎች አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤

፲፩ ሴቶች፣ ህጻናት እና አካል ጉዳተኞች ያላቸውን አቅምና ችሎታ ለህብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ አገልግሎቶች ለማበርከት የሚያስችላቸው የበጎ ፈቃደኝነት ባህል እንዲያጎለብቱ ያበረታታል፤

፲፪ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሴቶች፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች ህጻናትና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የኑሮ ሁኔታ የሚሻሻልበትን ሁኔታ ያጠናል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፫ በየደረጃው ያሉ የሕፃናት አደረጃጀቶችን አቅም በማጎልበት የሕፃናት ተሳትፎ እንዲያድግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

፲፬ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በማጠናከር የነዋሪዎች ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት እና ዋስትና የሚሻሻሉባቸውና የሚጠበቁባቸው አሰራር ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፭ የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና ክብካቤ ጥምረት ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ በማድረግ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች በማህበረሰብ አቀፍ የተሀድሶ አገልገሎት እንዲታቀፉ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤

፲፮ በማህበረሰብ አቀፍ ሊታቀፉና ሊደገፉ ያልቻሉ፣ በወንጀል ነክ ድርጊት ውስጥ የተሳተፉ፣ የሱስ ተጋላጭ ህጻናት፣ ጧሪና ደጋፊ የሌላቸው አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች እና ሰርቶ ለማደር አቅም የሌላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች በአስተዳደሩና መንግስታዊ ባልሆኑ ማዕከላት ውስጥ ክብካቤና ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፲፯ በመንግስት በጀት የሚተዳደሩ የህጻናት የክብካቤ መስጫ ማዕከላትን ያስተዳድራል፤ ያስፋፋል፣ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፰ በአስተዳደር ተቋማት ውስጥ የህጻናት ማቆያ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

፲፱ የማህበራዊ ልማት ፈንድ የሚያስገኝ ፕሮጀክት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፳መስራት የማይችሉና ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተስብ ክፍሎች በሴፍቲኔት ቀጥታ ድጋፍ ማዕቀፍ ውስጥ ተጠቃሚ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤ ያስተባብራል፤

፳፩በአስተዳደሩ ውስጥ ያሉ መሠረታዊ እድር እና በየደረጃው የሚገኙት የእድር ምክር ቤቶችን ይመዘግባል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤ ባህላዊና ታሪካዊ እሴታቸውን ጠብቀው እንዲሄዱ ድጋፍ ያደርጋል፤ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ እንዲያጠናክሩ ያበረታታል፡፡

፳፪ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

## ፺፩.የመንግሥት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ የአስተዳደሩን የኢንፎርሜሽን ሥራን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪ የአስተዳደሩን የኢንፎርሜሽን ዋነኛ ምንጭ በመሆን ያገለግላል ፣ በልዩ ልዩ መንገዶች ያሰራጫል፣ በዋና ዋና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ የመንግስትን አቋም ይገልፃል፤

፫ የአስተዳደሩን ሴክተር መስሪያ ቤቶችን የህዝብ ግንኙነት ሥራ አቅጣጫን ያስቀምጣል፣ ያስተባብራል፤

፬ ብሄራዊ መግባባትን ለመፍጠር የሚያስችሉና የአስተዳደሩን መልካም ገፅታ የሚያጎለብቱሁኔታዎችን ይፈጥራል፣ ያስተባብራል፣ ያስተዋውቃል ፣ በነዚህ ተግባራት ላይ የሚያተኩሩ የሚዲያ ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁና እንዲሰራጩ ያደርጋል፤

፭ በአስተዳደሩ ኢንፎርሜሽንኮሙኒኬሽን እንዲሁም በብሄራዊ መግባባት እና በገፅታ ግንባታ ሥራዎች ከሴክተሮች፣ ከታችኛው የአስተዳደር እርከንና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የግንኙነት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤

፮ የአስተዳደሩን የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ከታችኛው የአስተዳደር እርከን የህዝብ ግንኙነት ሠራተኞችን የአቅም ግንባታ ተግባሮችን ያከናውናል፣ የሠራተኞቹንም ምልመላና ቅጥር በተመለከተ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፯ የሚዲያ ሞኒተሪንግ፣ የፕሬስ ዘገባ የከባባዊ ቅኝት ሥራዎችን ያከናውናል፣ ትንተና ያዘጋጃል፣ እንዲሁም የህዝብ አስተያየት ያሰባስባል፤

፰ ሚዲያዎች ከአስተዳደሩ ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ያስተባብራል፣ ለሚዲያ ኢንፎርሜሽን ጥያቄ አግባብ ባላቸው የመንግስት አካላት ምላሽ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፱ በመንግስት ፖሊሲዎችና በተለያዩ አስተዳደራዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ለመስጠትና ግልጽነትን ለመፍጠር ህዝባዊ ውይይት መድረኮችን ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል፤

፲ ከፍተኛ የአስተዳደሩ ባለስልጣናት ህብረተሰቡን በአካል አግኝተው እንዲያነጋገሩና ተቋማትን፣ ድርጅቶችን፣ ሁነቶችን፣ የሥራ አፈፃፀሞችንና ክንውኖችን እንዲጎበኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፲፩.ልዩ ልዩ ህትመትና የኦዲዮ ቪድዮ ቀረፃ፣ የአርማና ህትመት ዲዛይን እንዲሰራላቸው ሲጠይቁ የማዘጋጀትና የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤

፲፪. ለንግድ ዓላማ የሚታተምም ሆነ የንግድ ዓላማ ለሌላቸው ስርጭታቸው በአስተዳደሩ ብቻ ለሆኑ ጋዜጦችና መጽሄቶች የሙያ ፍቃድ ይሰጣል፡፡ በህጉ መሠረት መስራታቸውን ይከታተላል፤

፲፫.የማስታወቂያ ስራ ህግን ተከትሎ ለአስተዳደሩ እና ለሀገር ልማት አስተዋጽኦ ሊያደርግ በሚችልበት አቅጣጫ ስለመከናወኑ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

፲፬.በአስተዳደሩ ውስጥ በቋሚ የዜና ወኪልነት ለሚመደቡ የውጪ አገር እና የአገር ውስጥ የዜና ወኪሎች ፍቃድ መውሰዳቸውን ያረጋግጣል፣ ህግ አክብረው መስራታቸውን ይከታተላል፤

፲፭.የመንግስትፖሊሲዎች ለማስተዋወቅና ለገፅታግንባታ የሚረዱ የሬድዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራም ያዘጋጃል፡፡ የአስተዳደሩ መስሪያ ቤቶችም ፕሮግራም እንዲሰራላቸው ሲጠየቁ በተመሳሳይ ሁኔታ ያዘጋጃል፣ ያማክራል፤

፲፮. በአስተዳደሩ ለሚገኙ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገራት ጋዜጠኞችእንደአስፈላጊነቱ መግለጫዎችን ይሰጣል፤

፲፯. አስተዳደሩ ሊታወቅበት በሚገባው ትክክለኛ ገጽታ እንዲታወቅ ሰፊ መረጃ ይሰጣል፣ በአስተዳደሩ ላይ የሚሰነዘሩ የተሳሳቱ መረጃዎች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፰. በኮሚኒኬሽን ሥራ ዙሪያ በሚመለከታቸው መንግስታዊ ፣ በበጎ አድራጎት በባለድርሻ ወገኖች መካከል በጋራ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የአጋርነት ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲፱. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፺፪.<u>የመሬት ልማት እና ማናጅመንት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ በስሩ ያሉትን ተቋማት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪ በወጡ ፖሊሲዎችና ህጎች መሠረት የከተማ ቦታ ያስተዳድራል ፣ የይዞታ ማረጋገጫ ፣ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፫ የአስተዳደሩን የመሬት ልማት እና ከተማ ማደስ አፈጻጸም ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፤ ሲጸድቅም እንዲተገበሩ ያደርጋል፤አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፬ የከተማዋን መዋቅራዊ እና ዝርዝር የአካባቢ ልማት ፕላኖች መሰረት በማድረግና ፍትሃዊና ኢኮኖሚያዊ የመሬት ልማትና አቅርቦት እንዲሁም የከተማ ማደስ ጥናት

ስራዎችን ያከናውናል ወይም እንዲከናወን ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፭ ለልማት የተመረጡ አካባቢዎች በአካባቢ ልማት ፕላኑ መሰረት የተቀናጀ የከተማ ዲዛይን መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፤ በሚመለከተው አካል ያፀድቃል፤

፮ በአስተዳደሩ ክልል ውስጥ ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ስራዎች የሚውል መሬት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ያረጋግጣል፤

፯ ለልዩ ልዩ የልማት ስራዎች የለማ መሬት በመሬት ባንክ መመዝገቡን ወጥ የሽንሻኖ ቁጥር መሰጠቱን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤

፰ መሠረተ ልማት ተሟልቶላቸው የተዘጋጁ የአስተዳደሩ ቦታዎች ለአልሚዎች የሚተላለፉበትን ስርዓት ይዘረጋል ወይም እንዲዘረጋ ያደርጋል፤ ለአልሚዎች የሚተላለፉ ቦታዎችን አግባብነት ይመረምራል፤ በውል መሰረት የሊዝ ክፍያው መሰብሰቡን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

፱ የቦታ አጠቃቀም ደረጃ ያዘጋጃል ፣ የቦታና የንብረት ዋጋ ስሌት ያዘጋጃል እንዲሁም የቦታ ኪራይ እና የቤት ግብር ተመን እያጠና ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲ የከተማውን መሬት ለማልማት ከግል ባለሀብቶች ጋር በጋራ ይሰራል፤

፲፩ የመሬት ፍላጎት ጥናት ያካሂዳል ፣ የመሬት ምንጭ ዳሰሳና ምዝገባ ያደርጋል፣ የመሬት ጥናትና መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ የልማት አካባቢ ይከፍላል፣ የካሣ ጥናትና መመሪያ ያዘጋጃል፣ የመልሶ ማቋቋም ስራ ይሰራል፤

፲፪ በልማት ምክንያት ለሚነሱ ህጋዊ ባለይዞታዎች ተገቢውን ካሣና ምትክ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ይሰጣል፤

፲፫ በህገ መሠረት ቦታና ንብረት ያስለቅቃል፤

፲፬ የቦታ ዝግጅት የዲዛይን ሽንሽና ጥናት ያደርጋል፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ የስራ ዋጋ ዝርዝር ያዘጋጃል፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታና ማሻሻያ ያደርጋል፤

፲፭ በከተማው የመሬት አቅርቦትና ፍላጎት ሚዛኑን ጠብቆ መሄድ እንዲችል የተለያዩ ጥናቶችን በማድረግ የመፍትሄ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

፲፮ የከተማ መሬት አስተዳደር ስርዓትን ያስፈፅማል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የከተማ መሬት አቅርቦትና አስተዳደር ስርዓት ይዘረጋል፤

፲፯ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል የለማ መሬት ያዘጋጃል ፣ ለተገልጋዩ ያቀርባል ፣ የአቅርቦቱን ፍትሐዊነት ያረጋግጣል፣ የተላለፈ መሬት ህጋዊነቱን ተከትሎ ለልማት መዋሉን ይከታተላል፣ ህገወጥ ግንባታዎችን ይቆጣጠራል፣ህጋዊ ስርዓትን ያስይዛል፤

፲፰ የማይንቀሳቀስንብረትይመዘግባል፣የዋጋግምትይሰራል፤

፲፱ የከተማ ቦታ ደረጃ እና የሊዝ መነሻ ዋጋ ጥናት ያካሂዳል፣ ለአስተዳደሩ ካቢኔ አቅርቦ ያጸድቃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ይህን አስመልክቶ የሚወጡ ወቅታዊ መረጃዎችን ለኅብረተሰቡ ያሰራጫል፤

፳ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፶፫. የመሬት ልማትእና ከተማ ማደስ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን እንዲሁም የአካባቢ ልማት ዝርዝር ፕላኖችን መሠረት በማድረግ የመሬት ልማትና የከተማ ማደስ፣የመሬት ፍላጎት ፣ ተነሺዎችን መልሶ የመቋቋም ጥናት ሥራ ያከናውናል፤

፪ በመልሶ ማልማትና ለመሬት ዝግጅት ተፈላጊዉን መሠረተ ልማት ያጠናል፤ ለሚመለከታቸዉ ያሳዉቃል፤የግንባታ ቅንጅት ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፫ በአስተዳደሩ ክልል ውስጥ ለተለያዩ የልማት ሥራዎች የሚውል ቦታዎችን በማዘጋጀት በመሬት ባንክ ዳታ ቤዝ እንዲመዘገብ ያደርጋል ፣ ባንክ የተደረጉ ቦታዎችን ለልማት እንዲውሉ ለአልሚዎች በጨረታና ምደባ መሰረት ሲፈቀድ ያስተላልፋል ፤

፬ የከተማዋየተጎዱናየደቀቁአካባቢዎችንበመልሶ ማልማት ሥራ ያለማል ፤ ያድሳል፤

፭ በልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችና በመልሶ ማልማት ምክንያት ተነሺ ለሚሆኑ ሰዎች የካሣ ክፍያ እንዲፈፀም ያደርጋል ፤ በህግ መሠረት ምትክ ቦታ እና የምትክ ቤት መቀበያ ሰርተፊኬት እና ምትክ ቦታ ይሰጣል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ የመልሶ ማቋቋም ስራ ከሚመለከተው ጋር በመሆን ይሰራል፤

፮ በአስተዳደሩ ውስጥ ለሚዘረጉ የመሠረተ ልማት አውታሮች፤ ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች፣ ለመናፈሻ ቦታዎች፣አረንጓዴ ቦታዎች እንዲሁም ለሕዝብ መሰብሰቢያ ፕላዛዎች በፕላኑ መሠረት ወሰናቸውን ያስከብራል፤ የወሰን ማስከበር ሥራዎች ያከናውናል የይዞታ የምስክር ወረቀት እንደ የአግባቡ እንዲሰጥ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤

፯ አግባብነት ባለዉ ህግ መሠረት በህገ ወጥ መንገድ የተያዙ ከተማ ቦታዎችን የማስለቀቅ ትዕዛዝ ይሰጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፰ ለተነሺዎች ምትክ ቦታ ያዘጋጃል ፤ የምትክ ቤት ፍላጎትን ያጠናል፡ ለሚመለከተዉ አካል ያሳዉቃል ፤ ሲፈቀድም ለተነሺዎቹ ምትክ ቦታና ቤት ድልድል ያደርጋል፤

፱ በይዞታነት ለማንም አካል ያልተላለፉ የተዘጋጁና ያልተዘጋጁ ቦታዎችን ይከልላል፣ በዲጂታል እና በፕላን ፎርማት ተገቢውን መረጃ ይይዛል፣ የቦታውንም አገልግሎት ደረጃ እና አስፈላጊ መግለጫዎችን የያዘ የመለያ ሰሌዳ ይተክላል፤

፲ በማስፋፊያ፤ በመሸጋገሪያና እና በመልሶ ማደስ አካባቢዎች ለልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች የለማ መሬትን በባንኩ በመመዝገብ ወጥ የሽንሻኖ ቁጥር በመስጠት ጨረታ ያወጣል፤ ለአሸናፊዎች ቦታውን በመስክ ያስተላልፋል፤

፲፩ በሊዝ አዋጁ ላይ በተቀመጠው መሰረት ለማንኛውም ግንባታ የሚውል ቦታ ወደ ሊዝ ስሪት እንዲገባ ያደርጋል፤በሊዝ ሕግ መሠረት ያስተዳድራል፤ በጨረታ ወይንም በምደባ ያስተላልፋል ፤ የሊዝ ውል ይዋዋላል፤ ቦታ ያስረክባል ፤ በውል መሰረት የሊዝ ክፍያ ይሰበስባል፤

፲፪ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፺፬.<u>የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት</u>

ጽህፈት ቤቱ የድሬዳዋ አስተዳደር የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽህፈት ቤትን ለሚቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፷፭/፪ሺ፲፫ላይ የተገለፁትንስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፺፭.<u>የከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ቢሮ ስልጣንና ተግባር</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ በስሩ ያሉትን ተቋማት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪ በአስተዳደሩ ውስጥ ተፈፃሚነት የሚኖራቸውን የከተማ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎችን ይነድፋል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫ የከተማና የገጠር ትስስር እና የከተሞች የእርስ በእርስ ትስስር እንዲጠናከር ስትራቴጂ ይቀይሳል፣ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬ በከተማ ልማት ስራዎች መካከል ቅንጅታዊ አሰራር እንዲፈጠር የተለያዩ ስልቶችን በጥናት ይቀይሳል፣ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ በማፀደቅ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

፭ ከተሞች የልማት ማዕከላት እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፣ የከተማ አሰፋፈርና የዕድገት አቅጣጫውን ያጠናል፣ ይከታተላል፤

፮ የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን እና የተቀናጀ የመሰረተ ልማት ፕላን ያዘጋጃል፤ ያፀድቃል፤ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፯ በአስተዳደሩ ውስጥ መሪ የከተማ ፕላንን የጠበቁ የመሰረተ-ልማት አውታሮች የሚስፋፉበትን ዘዴ ይቀይሳል፣ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

፰ የአስተዳደሩ ከተሞች ውብ፣ ፅዱና አረንጓዴ እንዲሁም ለኑሮም ሆነ ለሥራ ተስማሚና ተወዳዳሪዎች ሆነው እንዱገኙ አስፈላጊውን ድጋፍና እገዛ ያደርጋል፤

፱ የግሉ ዘርፍ በከተማ ልማት ስራዎች በንቃት የሚሳተፉበትን ስልት ይቀይሣል፤

፲ የአስተዳደሩን ልማት ለማፋጠንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያግዙ የተለያዩ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሌሎች እንዲካሄድ ያደርጋል፤

፲፩ የአስተዳደሩን የመንግስት ህንፃዎችንና ቤቶችንይመዘግባል፣ በላይነት ያስተዳድራል፣ ያድሳል፣ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ህንፃዎች በመለየት እንዲጠገኑ ያደርጋል፤

፲፪ የጋራ መኖሪያ ቤቶችንና ንግድ ቤቶችን ለማስተላለፍ፣ ለማከራየትና ለማስተዳደር እንዲሁም ሌሎች የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት፣ የግል ቤት አልሚዎች እና ሪል ስቴቶችን ለመምራት የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ፣ ስልትና ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ ይተገብራል፤ የመኖሪያ ቤት አይነቶችን መደብና ደረጃ ያወጣል፤

፲፫ የአስተዳደሩ ከተሞች ሁለን-አቀፍ በሆነ ደረጃ የሚጠቀሙባቸውን የህግ ማዕቀፍች ያዘጋጃል፣ የዕድገት ደረጃቸውን በጠበቀ መንገድ እንዲሻሻል ያደርጋል፤

፲፬ ከተሞች ከአጋር አካላት ጋር በጋራ የሚሰሩባቸውን ስልቶች በመንደፍ ያልተማከለ አስተዳደር ስርዓት የሚጠናከርበትን ዘዴ ይቀይሣል፤

፲፭ በአስተዳደሩየኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚመራበትን አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፀድቁም ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ ከወቅቱ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እንዲከለሱና እንዲበለፅጉ ያደርጋል፤

፲፮ በአስተዳደሩ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ብቁና ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ተቋራጮችን፣ አማካሪዎችና የኮንስትራክሽን እቃና መሳሪያ አምራችና አቅራቢ ድርጅቶች እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

፲፯ በአስተዳደሩ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት እና የኮንትራት አስተዳደር አቅም እንዲጎለብት ይሰራል፣ ለአስተዳደሩ ተቋማት ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፰ በግንባታ ዘርፍ የሚሰማሩ የምህንድስና ባለሙያዎች አማካሪዎችና የስራ ተቋራጮችን ይመዘግባል ፣ የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል ፣ ያድሳል ፣ ይሰርዛል፤

፲፱ በአስተዳደሩ መንግስት ለሚካሄዱ ግንባታዎች የዋጋ ጥናት ያካሂዳል፣ የምህንድስና ግምት ያዘጋጃል ፣ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣ በውለታው መሰረት መፈፀሙን የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን ያካሂዳል፣ የጥራት ቁጥጥር ያደርጋል፣ ክፍያዎችን ያፀድቃል፤

፳በአስተዳደሩ ለሚገነቡ ህንፃዎች የዲዛይንና የግንባታ ውሎች ስለሚይዟቸው የውል ቃሎች የቴክኒክ መመሪያ ያዘጋጃል፣ በተገቢው ውል መሰረት የጥራት ደረጃቸው የጊዜና የዋጋ ገደቦች ተጠብቀው መሰራታቸውን ይቆጣጠራል ፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል ፣ እርምጃ ይወሰዳል፤

፳፩የኮንስትራክሽን ግብዓት ጥራትና ደረጃ ለማረጋገጥ በላብራቶሪ እየተፈተሸ ለግንባታ አገልግሎት መዋሉን ያረጋግጣል፤ ለዚህ ተግባር እንዲያግዝም ላቦራቶሪ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

፳፪የአስተዳደሩን የኮንስትራክሽን ዲዛይን ስራዎች ፍላጎት ከተቋማት፣ ይሰበስባል በራስ አቅምና በአማካሪ የሚሰራውን ይለያል፣ በራስ አቅም የሚሰሩ ዲዛይኖችን በጥራት ያዘጋጃል ፣ በአማካሪዎች ወይም በሌላ አካላት ለሚሰሩ ዲዛይኖች የማወዳደሪያ ሰነድ ያዘጋጃል፣ የአማካሪ ደረጃ ይወስናል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል ፣ የተሰሩ ዲዛይኖች ይገመግማል ፣ የጥራት ቁጥጥር ያደርጋል ፣ የአገልግሎት ክፍያቸውን ያፀድቃል፤

፳፫የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና የቁጥጥር ስራዎችን ያከናውናል፤

፳፬የሀገሪቱ የህንፃ ኮድ፣ የዲዛይንና ኮንስትራክሽን ስራ ደረጃዎች በአስተዳደሩ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

፳፭ በአስተዳደሩ በጀት የሚገነቡ የመንግስት ህንጻዎች፣ መንገዶችና መሰል የመሰረተ-ልማት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ ዲዛይኖች፣ ፕላኖች፣ የስራ

ዝርዝሮችና የኮንስትራክሽን ስራ ውሎች በራስ ሃይል ወይንም በአማካሪ ድርጅት በጥራት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

፳፮የግንባታ ፕሮጀክት አዋጭነት ጥናት ያካሂዳል፣ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፳፯ የስራ ተቋራጭ የጨረታ ሰነድ ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ጨረታውን ያወጣል፤ አሸናፊውን ይለያል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፳፰ የመንግስት ህንጻ ግንባታ በተገባው ውል መሠረት፣ የጥራት ደረጃ፣ የጊዜና የዋጋ ገደብ ተጠብቆ መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፤ በበላይነትም ይቆጣጠራል፤

፳፱ አስተዳደሩን ወክሎ የህንጻና ተመሳሳይ የግንባታ ስራዎችን አግባብ ባለው ህግ መሰረት ውል ይፈጽማል፤ ኮንትራት ያስተዳድራል፤ ግንባታው ሲጠናቀቅም በውሉ መሰረት መከናወኑን አረጋግጦ ይረከባል፤ ህንጻው ወይም ግንባታው ለተከናወነለት ተቋም በሰነድ ያስረክባል፤

፴በአስተዳደሩ ውስጥ የምህንድስና ባለሙያዎች፣የስራ ተቋራጮችንና አማካሪዎችን ይመዘግባል፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ የቴክኒክ መገምገሚያ መስፈርቶችን ያዘጋጃል፣ አፈፃፀማቸውን ይመዝናል፣ ደረጃ ያወጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ፈቃዳቸውን ይሰርዛል፤

፴፩በአስተዳደሩ የዲዛይንና የኮንስትራክሽን ዘርፍ ለተሰማሩ አማካሪዎች፣ ኮንትራክተሮች እና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያከናውናል፤

፴፪ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፶፮.<u>የከተማ ፕላን ኢንስቲቲዩት</u>

አንስቲቲዩቱ የድሬዳዋ አስተዳደር የከተማ ፕላን ኢንስቲቲዩትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር /፪ሺ.፬ ላይ የተገለፁት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፶፯.<u>የመንግስት ግንባታና የውል አስተዳደር ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩ ከየተቋማቱ የሚቀርበውን የግንባታ ፍላጎት መሠረት በማድረግ የሚገነቡ የመንግስት ህንጻዎች የስትራቴጂያዊና ዓመታዊ የፊሲካልና የፋይናንሻል ዕቅድ በጋራ ያዘጋጃል፤

ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ያዳብራል፤ በሚመለከተው አካል አጸድቆ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪ በሚመለከተው አካል የተዘጋጁ ዲዛይኖችን ከግንባታ ሳይቶች ጋር የማጣጣም ስራ ይሰራል ወይም እንዲሰራ ያደርጋል፤

፫ ፍላጎቱን ካቀረበው ተቋም ጋር በመሆን የግንባታ ፕሮጀክት አዋጭነት ጥናት ያካሄዳል፣ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬ የመንግስት ህንጻ ግንባታ በተገባው ውል መሠረት፣ የጥራት ደረጃ፣ የጊዜና የዋጋ ገደብ ተጠብቆ መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፤ በበላይነትም ይቆጣጠራል፤

፭ አስተዳደሩን ወክሎ የህንጻና ተመሳሳይ የግንባታ ስራዎችን አግባብ ባለው ህግ መሰረት ውል ይፈጽማል፤ ኮንትራት ያስተዳድራል፤ ግንባታው ሲጠናቀቅም በውሉ መሰረት መከናወኑን አረጋግጦ ይረከባል፤ ህንጻው ወይም ግንባታው ለተከናወነለት ተቋም በሰነድ ያስረክባል፤

፮ ለግንባታና ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ የሚያስፈልገውን መሠረተ-ልማት እንዲሟላ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ያቀርባል፤ መሟላቱንም ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

፯ ግንባታው ሲጠናቀቅ ኤጀንሲው ለሚመለከተው አካል የመጠቀሚያ ፈቃድ እንዲሰጠው ጥያቄ ያቀርባል፤ ፈቃዱን ይረከባል፤

፰ በውሉ መሰረት ባልተፈጸሙ፣ በሚታዩ ጉድለቶችና ጥፋቶች ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድም ያደርጋል፤

፱ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፺፰.የመንግስት ህንፃዎችና ቤቶች አስተዳደር ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩ በመንግስት ህንጻና ቤቶች አስተዳደር ላይ ለከተማ አስተዳደሩ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤ ያማክራል፤

፪ የአስተዳደሩን ህንፃዎችንና የመንግስት ቤቶች ይመዘግባል፤ በበላይነት ያስተዳድራል፤ ያድሳል፤ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ህንፃዎች በመለየት እንዲጠገኑ ያደርጋል፤

፫ የህንጻና ቤቶች አስተዳደር እና አጠቃቀም ዘመናዊ ስርዓትን ይዘረጋል፤ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ያረጋግጣል፤ ምድረ ግቢን ውብና ማራኪ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፬ የመንግስት ህንፃዎች አጠቃቀም፣ ለተጠቃሚው ያላቸው ተደራሽነት እና ከወጪ አንፃር ውጤታማ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፭ የተቋማትን ፍላጎት፣ የስራ ባህሪይ እና የተገልጋይ ሁኔታን በማጥናት የስራ ቦታ ይደለድላል፤

፮ የአስተዳደሩ የመንግስት ተቋማት ለአገልግሎት አሰጣጥ የሚያስፈልጋቸውን ህንፃዎች የኪራይ ደረጃ አጥንቶ ይወስናል፤ ለመንግስት አገልግሎት የሚውሉ ህንፃዎች እንዲገነቡ ያደርጋል፤

፯ ግንባታቸው ተጠናቆ የመጠቀሚያ ፍቃድ ያገኙ የመኖሪያ ቤቶችን በማስተላለፊያ ዋጋቸው ለተጠቃሚዎች በእጣ ወይም በምደባ ያስተላልፋል፣ የቤቶቹን አስፈላጊ ሰነዶች ሁሉ ቤቱ ለደረሳቸው ባለመብቶች በወቅቱ ያስረክባል፤

፰ በሚገነቡ የጋራ ህንፃዎች ለንግድ አገልግሎት የሚውሉት ቤቶች በጨረታ ይሸጣል፤

፱ የመንግስት ቤቶች ባላቸው ይዞታ መሠረት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲኖራቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል፣ ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፲ የመንግስት ህንፃዎች ወጥ የሆነ ስታንዳርድ እና ዲዛይን እንዲኖራቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል፤ ያስገነባል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፲፩ የህንጻ አስተዳደር ሥራዎች የተቀላጠፉና ውጤታማ እንዲሆኑ የውስጥ አደረጃጀት እና የቢሮ ቁሳቁስ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ እንዲተገበር ያደርጋል፤

፲፪ በመንግስትየንብረትአያያዝስርዓትመሰረትየመንግስትቤቶችበአግባቡስለመያዛቸውእናጥቅ ምላይስለመዋላቸውኦዲት ያደርጋል፤

፲፫ በኤጀንሲው የህንጻና የቤቶች ኦዲት ውጤት መሰረት ተገቢው የእርምት እርምጃ ያልወሰዱ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ለይቶ ለቢሮውና ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤

፲፬ አግባብ ባለው ህግ የመንግስት ቤቶች ዋጋ እንዲወጣላቸው እና በየዓመቱ የዕልቀት ዋጋ እንዲሰላላቸው በማድረግ መንግስት ቤቶች የያዙትን ዋጋ እንዲያውቅ ያደርጋል፤

፲፭ ኤጀንሲውበሚያስተዳድራቸውህንጻዎችናቤቶችላይየሚፈጸሙህገወጥድርጊቶችንይከላከላ ል፤ተፈጽሞምሲገኝህጋዊእርምጃይወስዳልወይምእንዲወሰድያደርጋል፤

፲፮ የመንግስትህንፃዎችየሚገነቡበትቦታያስፈቅዳል፤ ይመዘግባል፤ ተገቢውን የይዞታ ማረጋገጫ እና የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ይጠብቃል፣

፲፯ አላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፻፱.የሥራ፣ ክህሎት እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩ በስሩ ያሉትን ተቋማት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪ የከተሞች ስራ ዕድል ፈጠራ ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ የአስተዳደሩን የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫ የከተሞች ስራ ዕድል ፈጠራን በሚመለከት የፖሊሲ ጥናቶችን፣ የምርምር ስራዎችንና ስትራቴጂክ ፕላኖችን እያጠና ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬ በፌደራል ደረጃ የከተሞች የስራ ፈጠራ ስራዎችን ለማስፋፋትና ለማልማት የወጡትን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መሠረት በማድረግ በከተማው አስተዳደር ውስጥ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን እንዲስፋፉና እንዲለሙ በማድረግ ለኢንዱስትሪ ልማት መሠረት እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፭ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለማስፋፋትና ድጋፎችን ለመስጠት የሚያስችሉ መመሪያዎችን፣ ደንቦችንና ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፡፡ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

፮ በአስተዳደሩ ውስጥ ባሉ የአሰሪና ሠራተኛ ወገኖች መካከል የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፍን የትምህርት እና የሥልጠና አገልግሎት ይሰጣል፣ የሙያ ምክር አገልግሎት ስለሚስፋፋበት፣ ሥራና ሠራተኛ ስለሚገናኝበት ዘዴ ይቀይሳል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፯ አግባብ ባለው የፌደራል መንግስት አካል በወጣ መመሪያ መሠረት የአሰሪና ሠራተኛ ማህበራትን ይመዘግባል፣ እንዲመዘገቡ ያደርጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

፰ በአሰሪና ሠራተኛ ወገኖች ድርድር ወቅት የሚቀርቡ የህብረት ድርድርልዩነቶች በስምምነት እንዲያልቅ ጥረት ያደርጋል፣ የህብረት ስምምነት በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት መፈፀማቸውን በማረጋገጥ ይመዘግባል፤

፱ የወል የሥራ ክርክሮችን በማየት ተከራካሪ ወገኖችን ለመስማማት ጥረት ያደርጋል፤

፲ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በአስተዳደሩ ውስጥ በሥራ ላይ ስለተሰማራው፣ ሥራ አጥ ስለሆነው የሰው ኃይል እንዲሁም ስለሙያ አመዳደብ ጥናት ያደርጋል፣ መረጃዎችን ይይዛል፤

፲፩ የድርጅቶች የሥራ ሁኔታን፣ የሙያ ደህንነትን፣ ጤንነት እና የሥራ አካባቢን ለመጠበቅ የወጡ የሥራ ሁኔታ ደረጃዎችና የመከላከያ ዘዴዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

፲፪በአስተዳደሩ ውስጥ ሥራና ሠራተኛ ለሚያገናኙ ኤጀንሲዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፣ እንዲሰጥ ያደርጋል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣ በህግ መሠረት መስራታቸውን ይቆጣጠራል፤

፲፫አሰሪና ሠራተኛን በሚመለከት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በአስተዳደሩ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤ ጥናት እያደረገም ህጎች ያለባቸውን ክፍተት በመፈተሸ የማሻሻያ ሀሳቦችን ያቀርባል፤

፲፬በአስተዳደሩ የሰው ኃይል፣ የሥራ ስምሪት፣ ስለሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም አሰሪና ሠራተኛን ስለሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል ከትንተና ጋር ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፤

፲፭በአስተዳደሩ ውስጥ የሥራ ስምሪት ለማስፋፋት የሚያስችሉ የሥራ ገበያ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ያሰራጫል፤

፲፮ ሥልጣኑ በግልጽ ለሌላ አካል በህግ ካልተሰጠ በስተቀር በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ዘርፍ ለሚሰማሩ አካላት የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤

፲፯ የዘርፉ የልማት ስትራቴጂ በተገቢው ሁኔታ መተግበሩን ያረጋግጣል፣ በስትራቴጂው አፈፃፀም ለሚከሰቱ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣል፤

፲፰ ለከተማው ህብረተሰብ የስራ ዕድል ፈጠራ፣ ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች፣ ከማኑፋክቸሪንግ ውጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትና ተወዳዳሪነት እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን ለመለየት ጥናቶች እንዲከናወኑ ያደርጋል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

፲፱ የስራ ዕድል ለመፍጠር የስራ አጦች፣ መስራት የሚችሉና የማይችሉ እንዲሁም ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን መረጃ በጥናት በመለየት ይሰበስባል፤

፳ በከተማው ውስጥ የሚገኙትን ስራ አጥ የሆኑ ወጣቶችና ሴቶችን በብዛት በማሳተፍ አምራች ዜጋ ሊያደርጉ የሚችሉ የተለያዩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ፕሮጀክቶች እንዲጠኑ ያደርጋል፣ ተግባራዊነታቸውንና ውጤት ማስገኘታቸውን ያረጋግጣል፤

፳፩የዘርፉ ምርቶች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ገበያ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ምርቱን ለማስተዋወቅና ህብረተሰቡን ስለ ተቋማቱ ጠቀሜታ ግንዛቤ እንዲኖረው ጉዳዩከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ ስልቶችን ይቀይሳል፤ ትምህርታዊ መግለጫዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤

፳፪በከተማው ህብረተሰብ ውስጥ ያለውን የስራ ባህል እና አመለካከት መቀየር የሚያስችሉ ግንዛቤ ማዳበሪያ የህዝብ ንቅናቄ ስራዎችን ያከናውናል፤

፳፫የአንድ ማዕከል አገልግሎት ለማደራጀት፣ ለማጠናከር እና አገልግሎቱን በአግባቡ ለመስጠት የሚያስችል የተሻሻሉ አዳዲስ ስርዓቶችን በመዘርጋት የማዕከሉን አቅም ይገነባል፤

፳፬ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የሚውል መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤ የድጋፍ ፍላጎትና አቅርቦት ጥናት ያካሂዳል፤

፳፭የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፳፮የስልጠናና አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂና የማምረቻ መሳሪያዎች አቅርቦት ያመቻቻል፣ የገበያ ትስስር ድጋፍ ይሰጣል፤

፳፯ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ እንዲያኙ ያደርጋል፤

፳፰ሞዴል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ይፈጥራል፣ ያሸጋግራል፤

፳፱የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የኦዲትና ኢንስፔክሽን አገልግሎት ይሰጣል፤

፴ በከተማ የስራ ዕድል ፈጠራ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማጥናትና በመቀመር የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ያስፋፋል፤

፴፩የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ እንዲስፋፋ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፣ ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ እና ከግል ድርጅቶች ጋር ትስስር በመፍጠር ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ተፈፃሚነቱን ያረጋግጣል፣

፴፪በአስተዳድራችን ውስጥ የሚገኙ የከተማ ነዋሪዎች የስራ ዕድል መፍጠር እንዲችሉ ስልጠናዎችን በመለየትና በመቀመር እውቀትና ክህሎት እንዲቀስሙ ያደርጋል፣ ያበረታታል፣ የንግድ ስራ ክህሎት የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

፴፫ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ስራቸውን በአግባቡ መምራት እና ምርትና ምርታማነታቸውን ማሳደግ እንዲችሉ ሙያዊ ድጋፍና ክትትል አገልግሎት ይሰጣል፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

፴፬በአስተዳድሩ ውስጥ የሚገኙትን ነዋሪዎች አምራች ዜጋ ለማድረግ የሚያስችሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ፕሮጀክቶችን ያጠናል፣ ፕሮጀክት ፕሮፋይል በማዘጋጀት ፍላጎቱ ላላቸው ስራ አጥ ወጣቶች ያስተዋውቃል፣ በስራው እንዲሰማሩ ያበረታታል፣

፴፭የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተሰማሩበትን የስራ ዘርፍ በአግባቡ ማካሄድ የሚያስችላቸው የፋይናንስ ብድር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

፴፮የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ማምረቻ፣ ማሳያ እና መሸጫ ማዕከላትን ማስገንባት እንዲቻል ከሚመለከተው አካል መሬት ይረከባል፣ ካርታ የሌላቸው ነባር ይዞታዎን ካርታ እንዲሰራላቸው ያደርጋል፣የማምረቻ፣ ማሳያ እና መሸጫ ማዕከላትን የአስተዳድሩን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ እና ለስራ ተስማሚ በሆነ መልኩ ያስገነባል፣

፴፯በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ላይ የተሰማሩ አንቀሳቃሾች የማምረቻ፣ ማሳያ እና የመሸጫ ቦታዎች በኪራይ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ የጥሬ ዕቃ፣ የማምረቻ መሣሪያዎች እና የመሰረተ ልማት አውታሮች የሚሟሉበት ሁኔታ ያመቻቻል፣

፴፰የማምረቻ፣ ማሳያ እና መሸጫ ማዕከላትን አጠቃቀምና አስተዳደር የሚመለከት መመሪያ ያወጣል፣ ያስተዳድራል፣

፴፱የማምረቻ፣ ማሳያ እና መሸጫ ማዕከላትን እና መስሪያ ቦታዎች በህገ-ወጥ መንገድ እንዳይተላለፉ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣ ተላልፈውም ሲገኝ ሁኔታውን በአግባቡ በማጣራት ተገቢውን ህጋዊ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ ወይምእንዲወስድ ያደርጋል፣

፵የማምረቻ ፣ ማሳያ እና መሸጫ ማዕከላትን በተመለከተ የተደራጀ መረጃ በመመዝገብ ይይዛል፣ ለተጠቃሚዎች በውሉ መሰረት በኪራይ ያስተላልፋል፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆታራል፣ የውል ዘመኑ ሲያበቃተከታትሎ ይረከባል

፵፩የማረቻ፣ ማሳያና መሸጫ ማዕከላት እድሳት እንዲያገኙ ያደርጋል፣

፵፪ለጥቃቅንና አነስተኛ አገልግሎት እንዲውሉ የተዘጋጁ ቦታዎችን፣ ሼዶችን፣ ተለጣፊ ሱቆችን፣ በመንግስትና በተለያዩ በጎ አድራጎት የተገነቡ መደብሮችን ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፣

፵፫በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ለተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሙያ ማበልፀጊያ ስልጠናዎችና አውደ-ርዕዪች እንደዘጋጁ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፣

፵፬የእንቀሳቃሾችን የገበያ ችግር ለመቅረፍ ከተለያዩ አካላት ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ያደርጋል፣ምርቶቻቸውንና አገልግሎታቸውን ለተጠቃሚው ለማስተዋወቅ እንዲችሉና የገበያ ዕድላቸውን ለማስፋት ኤግዚቢሽንና ባዛሮች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣

፵፭የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች በግል ንግድ፣ በሽርክና እና በህብረት ስራ ማህበር እንዲደራጁ ያመቻቻል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣ ያበረታታል፡ኢንተርፕራይዞቹ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ኢንትተፕራይዝ መሸጋገር የሚገባቸው በመለየት አንዲሸጋገሩ ያደርጋል፣

፵፮የመረጃና የምክር አገልግሎት ለተጠቃሚዎች የሚሰጥበትን ስርዓት ይዘረጋል፣

፵፯ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎችተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፷.የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ

ኤጀንሲው በድሬዳዋ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፪ሺ፬ ላይ የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፷፩.የኢትዮ-ጣሊያን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

ኮሌጁ በድሬዳዋ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፯/፪ሺ፬ ላይ የተገለፀው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፷፪.የድሬዳዋ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ

ኮሌጁ በድሬዳዋ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር፯/፪ሺ፬ ላይ የተገለፀው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፷፫.የልህቀት ማዕከል

ማዕከሉ በድሬዳዋ አስተዳደር የልህቀት ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፯/፪ሺ፫ ላይ የተገለፀው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፷፬.የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሺን ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣን ተግባር ይኖሩታል፡-

፩ የልማት ፍላጎት መሰረት ያደረገ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት እቅዶች ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፪ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን እንቅስቃሴችን በበላይነት ያስተባብራል፣ በኢንዱስትሪዎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ተቋማት እና ቴክኒክና ሙያ ተቋማት መካከል ጠንካራ ትስስርና ትብብር እንዲፈጠር ያደርጋል፣

፫ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማትን አስመልክቶ ተገቢውን መረጃ መከታተል፣ ማሰባሰብና መተንተን የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፣ አቅምን ይገነባል፣

፬ የአስፈፃሚ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጣቸው በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ያደርጋል፣ ደረጃ በደረጃም ለተጠቃሚዎች በቀጥታ አገልግሎት ሊሰጥ በሚችሉበት ሁኔታ መመቻቸታቸውን ያረጋግጣል፣

፭ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ክፍተትን ይለያል፣ አስፈላጊ መስፈርቶችን በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ይዘረጋል፣ እንዲዘረጋም ያደርጋል፣

፮ ደረጃ አውጥቶ ወይም በወጣው ደረጃ መሰረት ሃርድዌርና ሶፍትዌር ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ለአስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች ያቀርባል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣ በዚህ መልኩ ለሚያዘጋጃቸው የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስም ይሰጣል፣ከአጠቃቀም ጋር በተያያዘ ያማክራል፣

፯ የአስተዳደሩ ተቋማት የኮምፒውተር መረቦችና አፕሊኬሽኖች እንዲቀናጁና እንዲናበቡ ያደርጋል፣ ያረጋግጣል፣

፰ የአስተዳደሩን የመረጃ ስርዓት ያደራጃል፣ ጥራቱ፣ ደህንነቱና አስተማማኝነቱን ይጠብቃል፣

፱ የአስተዳደሩ ውስጥ የኮምፒውተር መረብ ዝርጋታ ስራዎችና ለሚሰሩ አካላት በጥናት ላይ የተመሰረተ ፈቃድ ይሰጣል፣

፲ ከሚመለከታቸውሌሎችአካላትጋርበመተባበርበአስተዳደሩየቴክኖሎጂፓርኮችእንዲቋቋሙ ያደርጋል፣

፲፩ የሳይንስናቴክኖሎጂእንቅስቃሴዎችየገንዘብናየዓይነት፣የማቴሪያልናየቴክኒክድጋፎችየሚያገኙበትንስርዓትይዘረጋል፣

፲፪ የአዕምሮአዊ ንብረት መብት ጥሰቶችን ለመከላከልና የህብረተሰቡ ግንዛቤ ለማሳደግ ከሚመለከታቸው የፌዴራል አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፣

፲፫ የጥራት መሰረተ ልማትና የጨረራ እና ጨረር አመንጪ መከላከያ እንቅስቃሴዎችን ያስተባብራል፣ ለተግባራዊነቱም የበኩሉን ጥረት ያደርጋል፣

፲፬ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ፕሮቶኮሎች ሥነ-ምግባርን ተከትለው መካሄዳቸውን ይከታተላል፣ የስነ-ምግባር ጉድለት ሲያጋጥም አስፈላጊ የሆኑ ሕጋዊ እርምጃዎች እንዲወስዱ ያደርጋል፣

፲፭ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ስራዎች (ፕሮቶኮሎች) እና የባዮኢቲክስ ምርምሮች ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲተገበሩ ለማድረግ እንዲቻል ስራውን በበላይነት የሚመራ አካል እንዲቋቋም ሀሳብ ያቀርባል፣

፲፮ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፳፭.<u>የወጣቶች፣ ስፖርት ፣ ባህል እና የበጎፍቃድ አገልግሎት ማሰተባበሪያ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ በሥሩ ያሉትን ተቋማት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪ የአስተዳደሩን የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላትን ያስፋፋል፣ ይደግፋል፤

፫ በአስተዳደሩ መንግስት ተቋማት የሚዘጋጁ ሕጎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የወጣቶችን ሁለንተናዊ መብትና ጥቅም እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤

፬ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በራስ መልካም ፈቃድ፣ ተነሳሽነት እና ያለማንም አስገዳጅነት ለሚሳተፉ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤ ያስተባብራል፤ ይመራል፤

፭ በአስተዳደሩ ዘላቂ የወጣቶችና የበጎፍቃድፍኖተካርታያዘጋጃል፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የወጣቶችን እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በእቅዶቻቸውና በፕሮግራሞቻቸው ውስጥ አካትተው እንዲሰሩ ድጋፍ ይሰጣል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፮ በወጣቶች መብት፣ ጥቅም እና ደህንነት ላይ የሚሰሩ ማህበራት እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ የወጣቶች መብት መጣሱን መረጃ ሲደርሰው ጉዳዩን ከሚመለከተው አካል ጋር በማጥናትና በማጥራት የህግ ከለላ ማግኘት እንዲችሉና ተገቢው መፍትሔ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፯ የወጣቶችን አቅም የሚያጎለብቱ ትምህርታዊ፣ ሙያዊና የተጨማሪ ክህሎት ስልጠናዎችን ያዘጋጃል፤ ያመቻቻል፤ ይሰጣል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት በተለያዩ በኪነ-ጥበብ እና በቴክኖሎጂ የፈጠራ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ ያበረታታል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

፰ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ወጣቶች በማህበር እንዲደራጁ፣ የመስሪያ ቦታ እንዲመቻችላቸው፣ የማምረቻ መሳሪያ አቅርቦት፣ የብድርና የቁጠባ አገልግሎት እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፱ ወጣቶች በአስተዳደሩ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጥምረት ይሰራል፤

፲ በበጐፍቃድ አገልግሎት የሚሰማሩወጣቶች፣ የሞያ ማህበራት፣ መንግስትናመንግስታዊያልሆኑተቋማት እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን ያስተባብራል፣የእውቅና እና ምስክርወረቀትይሰጣል፤ ያበረታታል፤

፲፩ የአስተዳደሩ ህብረተሰብ በኢኮኖሚው እና በማህበራዊ ያለውን የመረዳዳት፣ የመደጋገፍ እና በጎ የሆኑ አገልግሎቶችን እንዲያከናውን እና ባህል ሆኖ እንዲያጎለብቱ ስልት ይነድፋል፣ ተግቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ያበረታታል፤

፲፪ የወጣቶች የሱስ ማገገሚያ ማዕከላትን ያቋቁማል፤ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

፲፫ የስፖርት ልማት ፈንድ የሚቋቋምበትን እና ባለሀብቱ በስፖርት ኢንቨስት የሚያደርግበትን ስልት ይቀይሳል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፬ የስፖርት ማህበራት ያደራጃል፤ የማዘውተሪያ ስፍራ አጠቃቀም የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ የስፖርት ማህበራትንና ክለቦችን እንዲሁም ጅምናዚየሞችን ይመዘግባል፤ የምዝገባ የምስክር ወረቀትና አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፭ የአስተዳደሩን ነዋሪዎች የስፖርት ተሳትፎ ለማጎልበት ያቅዳል፤ የስፖርት ውድድሮችንና የመዝናኛ ትርዒቶችን ያዘጋጃል፤ ይመራል፤ ከሚመለከተው ጋር በመተባበር የትምህርት ቤቶች የስፖርት ውድድር እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ያደርጋል፤

፲፮ በአስተዳደርደረጃ የብዙሃን የአካል እንቅስቃሴ እና የስፖርት መዝናኛ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤ ይመራል፤

፲፯ በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶችን ያጠናል፣ በሕግ መሠረት ይጠብቃል፣ ያስጠብቃል፣ ብሔር፣ ብሔረሰቦች ህዝቦች ታሪክና ባህል ተመዝግቦ እንዲያዝ ያደርጋል፣ የባህል ሙዝየሞችን ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሑፎች እንዲዳብሩ ያደርጋል፣

፲፰ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፳፯.<u>የባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ በአስተዳደሩ የህዝብ ቤተ መፃህፍትን እና የሲኒማ ቤቶች ድርጅት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣

፪ በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶችን ያጠናል፣ በሕግ መሠረት ይጠብቃል፣ ያስጠብቃል፣ የብሔር ብሔረሰቦች ታሪክና ባህል ተመዝግቦ እንዲያዝ ያደርጋል፣ የባህል ሙዝየሞችን ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሑፎች እንዲዳብሩ ያደርጋል፣

፫ በባህል ተፅዕኖ ሳቢያ ማህበራዊ ዕድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሠራሮችን የመለወጥ ተግባሮችን ያከናውናል፣

፬ የባህል ዘርፍ ልማዳዊ አስተዋጽኦ እንዲስፋፋ ያድርጋል፣ ባህል፣ ኪነጥበብ፣ ሥነ ጥበብ እና የፈጠራ ችሎታ በአስተዳደሩ ውስጥ እንዲዳብሩና እንዲስፋፋ ያደርጋል፣

፭ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ግብረ-ገባዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን የሚያራምዱና የሚያስፋፉ እንቅስቃሴዎችን ይከታተላል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፣

፮ በአስተዳደሩ ሥር የሚገኙ የህዝብ ቤተ መጽሐፍትን፣ ቤተመዛግብትና አብያተ-መዘክርን ያስተዳድራል፣ ይመራል፣ እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ በባህል ዘርፍ የህዝብን ተሳትፎ መሠረት ለማስያዝ ሌሎች የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ያድርጋል፣

፯ በአስተዳደሩ የቱሪዝም መስህቦችና መልካም ገጽታ ለሀገር ውስጥና ለውጪ እህት ከተሞች የቱሪዝም ገበያ በስፋት ያስተዋውቃል፣

፰ በአስተዳደሩ የቱሪስት መስህቦችና መዳረሻዎችን ተለይተው እንዲታወቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲደራጁ፣ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲስፋፉ፣ የከተማው ነዋሪም ከቱሪዝም ጥቅሞች ተካፍይ እንዲሆን ያድርጋል፣

፱ ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሙያ ፍቃድ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፲ የቱሪስትአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ደረጃዎችን ይወስናል፣ተፈፃሚነቱን ይቆጣጠራል፤

፲፩ በቱሪዝም የሰመረ አገልግሎት እንዲኖርና የቱሪስቶችም ደህንነት እንዲረጋገጥ ከሚመለከታቸው ጋር ይሠራል፤

፲፪ የቱሪዝም ሴክተር የማስፈፀም አቅም ይገነባል፤

፲፫ የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሠራጫል፤

፲፬ በአስተዳደሩ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የኪነ ጥበብና የቱሪዝም ተቋማትን፣ ማህበራትን፣ ክበባትን፣ ሞያተኞችን በሕግ መሠረት ይመዘግባል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፭ በባህልና ቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፮ ዓላማውንለማሳካትየሚረዱሌሎችተዛማጅተግባራትንያከናውናል፡፡

## ፳፮.<u>የስፖርት ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር</u>

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ የአስተዳደሩን የስፖርት ትምህርትና ሥልጠና ማዕከላትን፣ የስፖርት ማዘወተሪያዎች፣ የስፖርት ልህቀት ማዕከላት በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ያስተዳድራል፤ እንዲስፋፉና አቅማቸው እንዲገነባ ያደርጋል፤

፪ የአስተዳደሩን ነዋሪ በስፖርት ለሁሉምና በባህላዊ ስፖርት ተሣታፊና ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፫ በስፖርት የሠለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል፤

፬ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችንና ማበልፀጊያ ማዕከላት እንዲገነባ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤

፭ ለስፖርት ተግባራት የሚውሉ የስፖርት ትጥቆችና መሣሪያዎች አቅርቦት የሚሟላበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያመቻቻል፤

፮ አግባብ ባለው ህግ የስፖርት ህክምና አገልግሎት መደራጀቱን፣ በስፖርት አበረታች መድሃኒቶችና ዕፆች መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

፯ የስፖርት ማህበራት ያደራጃል፤ የማዘውተሪያ ስፍራ አጠቃቀም የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ የስፖርት ማህበራትንና ክለቦችን እንዲሁም ጅምናዚየሞችን ይመዘግባል፤ የምዝገባ የምስክር ወረቀትና አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፰ በሳይንሳዊ ጥናት ላይ የተመሰረቱ የአካል ብቃት ማሰልጠኛ ዘዴዎችን በማዘጋጀት ስፖርተኞች፣ አሰልጣኞች የስፖርት ዳኞችና የመሳሰሉት እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፤

፱ የአስተዳደሩን ነዋሪ የስፖርት ተሳትፎ ለማጎልበት ያቅዳል፤ ስፖርት ውድድሮች ያዘጋጃል፤ ይመራል፤ ከሚመለከተው ጋር በመተባበር የትምህርት ቤቶች የስፖርት ውድድር እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ያደርጋል፤

፲ በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርት ከማህበሩ እንዲቀርብለት በማድረግ የስፖርት ማህበራት ገቢ ለአላማቸው ብቻ መዋሉን ያረጋግጣል፤

፲፩ የአስተዳደሩን ስፖርት ምክር ቤት በየደረጃው በማቋቋም አግባብ ባለው ህግ አደረጃጀቱን ያጠናክራል፤ ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፪ የስፖርት ልማት ፈንድ የሚቋቋምበትን እና ባለሀብቱ በስፖርት ኢንቨስት የሚያደርግበትን ስልት ይቀይሳል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፫ የአካል ጉዳተኞችና ልዩ ፍላጎት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በስፖርት ያላቸው ተሳትፎ እንዲጎለብት አሰራር ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፬ የታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ስልጠና ከታችኛው የእድሜ ክልል የሚጀምርበትን ስልት ይቀይሳል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፭ በአስተዳደር ደረጃ የብዙሃን የአካል እንቅስቃሴ እና የስፖርት መዝናኛ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤ ይመራል፤

፲፮ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## **ክፍል አራት**

## **ስለሌሎች አስፈፃሚ አካላት**

## ፳፰.<u>የመንግስት ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች</u>

፩ በአስተዳደሩየሚገኙ የመንግስት ሆስፒታሎች እና ጤና ጣቢያዎች ራሳቸውን የቻሉ የህግ ሰውነት ያላቸው የአስተዳደሩ የጤና ተቋማት ሆነው በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡፡

፪ የጤና ተቋማቱ ተጠሪነት ለጤና ቢሮ ይሆናል፡፡

፫ የጤና ተቋማቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባር የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፳፱.<u>የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ ድርጅት</u>

፩ የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ ድርጅትራሱን የቻለ ህግ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪ የድርጅቱ ተጠሪነት ለግብርና ውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ይሆናል፡፡

፫ የድርጅቱ አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባር የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፴.<u>የቤቶች ልማት ድርጅት</u>

፩ የቤቶች ልማት ድርጅትራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪ የድርጅቱ ተጠሪነት ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፡፡

፫ የድርጅቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባር የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፴፩.<u>የጋራዥ አገልግሎት</u>

፩ የጋራዥ አገልግሎት ራሱን የቻለ ህግ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪ የአገልግሎቱ ተጠሪነት ለሥራ ክህሎት ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡

፫ የአገልግሎቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባር የአስተዳደሩ ካቢኑ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፴፪.<u>የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች</u>

፩ በአስተዳደሩ የሚገኙ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ራሳቸውን የቻሉ የህግ ሰውነት ያላቸው የአስተዳደሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሆነው በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡፡

፪ የትምህርት ቤቶቹ ተጠሪነት ለትምህርት ቢሮ ይሆናል፡፡

፫ የትምህርት ቤቶቹ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባር የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፸፫.<u>የካይዘን ኢንስቲትዩት</u>

፩ የካይዘን ኢንስቲትዩትራሱን የቻለ ህግ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡፡

፪ የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ይሆናል፡፡

፫ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባር የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፸፬.<u>የሥራ አመራር ኢንስቲቲዩት</u>

፩ የሥራ አመራር ኢንስቲቲዩትራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪ የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡

፫ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባር የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

# <u>ክፍል አምስት</u>

# <u>ስለ ማዘጋጃ ቤት አገልሎት አካላት</u>

## ፸፭.<u>የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት  አካላት መቋቋም</u>

፩ የሚከተሉት የማዘጋጃት ቤት አገልግሎት አካላት ህጋዊ ሰውነት በማግኘት ተቋቁመዋል፤

ሀ.የከተማው ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት፤

ለ. የጽዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት ኤጀንሲ፣

ሐ. የቄራ አገልግሎት ድርጅት፤

መ. የአካባቢ ልማት እና ህብረተሰብ ተሳትፎ ኤጀንሲ፤

፪ እያንዳንዱ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካል ኃላፊ፣ የራሱ የሆነ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፤

፫ የከተማው ስራ አስኪያጅ የሚመራቸው የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ድጋፍ ሰጭ አገልግሎቶች በጋራ ሊጠቀሙ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያፀድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት ይወሰናል፤

## ፸፪ስለ ከተማው ሥራ አስኪያጅ

የከተማው ሥራአስኪያጅ ተጠሪነቱ ለከንቲባው ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ መሠረት የካቢኔ አባል ይሆናል፡፡

## ፸፪.ተጠሪነት

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፸፭ በንዑስ አንጽ (፩) ከፊደል "ሀ" እስከ "መ" ድረስ የተጠቀሱት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ተጠሪነታቸው ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፡፡

## ፸፰.ስለሌሎች ማዘጋጃቤት አገልግሎት አካላት

፩ የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ተጠሪነት ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ቀደም ብሎ በተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር ፴፯/፪ሺ፯መሠረት ሥራውን ይቀጥላል፤

፪ የመንገዶች ባለስልጣን ተጠሪነት ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ቀደም ሲል ባለሥልጣኑን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፯ በተደነገገው መሠረት ስራውን ይቀጥላል፡፡

## ፸፱.የማዘጋጃቤትአገልግሎትአካላት የወል ሥልጣንና ተግባር

እያንዳንዱ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካል በየደረጃው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ የተቋማቱን ስትራቴጂዎች እቅድ፣ ዓመታዊ እቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድምተግባራዊ ያደርጋል፤

፪ ተቋሙን በሚመለከት አግባብ ባለው አካል ሲፈቀድለት መመሪያ ያወጣል፣ ሲፈቀድም ይተገብራል፤

፫ ሠራተኞቹን አግባብ ባለው ህግ መሠረት ያስተዳድራል፤

፬ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፤

፭ የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ፕሮግራሞችና እቅዶች እንዲዘጋጅ ያደርጋል ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤

፮ በህግ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

፯ አግባብ ካላቸው አካላትና ከአስተዳደሩ ነዋሪዎች ጋር በመተባበር በአጋርነት ይሰራል፡፡

## ፹.ከተማው ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤትሥልጣንና ተግባር

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ተግባሮችና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩ እያንዳንዱን የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እና በሥሩ ያሉ ድጋፍ ሰጪ የአገልግሎት ክፍሎችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት የተሟላ አገልግሎት መስጠታቸውን ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል ፣ ያረጋግጣል፤

፫ በታችኛው የአስተዳደር እርከን ያሉ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን በተመለከተ እቅድና በጀት ለከንቲባው ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬ የአገልግሎት አቅርቦት መለኪያዎች እና መመሪያዎች በማጠናቀር ለከንቲባው ያቀርባል፣ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፭ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሀዊ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት መሰጠቱን ያረጋግጣል፤

፮ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከቱ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

፯ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከት የፖሊሲ ሀሳብ እና የህግ ረቂቅ በማመንጨት ለከንቲባው ያቀርባል፤

፰ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን በተመለከተ የነዋሪዎችን አቤቱታ ያስተናግዳል፣ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በተቻለ ፍጥነት ምላሽ ይሰጣል፤

፱ የአቤቱታ መንስኤዎች ወይም ምንጮችን ለይቶ ጥናት በማድረግ ዘላቂ መፍትሄ የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲ የከተሞች ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ መሠረት በማድረግ የአስተዳደሩን የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፩ የከተሞች የምግብ ዋስትናን በሚመለከትጥናቶችን፣ የምርምር ስራዎችንና ስትራቴጂክ ፕላኖችን እያጠና ያቀርባል፡፡ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፪ በፌደራል ደረጃ የከተሞች ምግብ ዋስትና ስራዎችን ለማስፋፋትና ለማልማት የወጡትን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መሠረት በማድረግ በከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚፈፀምበትን ስልት ይቀይሳል፤

፲፫ የከተማ ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መመሪያዎችን፣ ደንቦችንና ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፡፡ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

፲፬ በከተማ የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም በመቅረፅ ተግባራዊ ያደርጋል፤የከተማ ምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አኳያ ከመንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፲፭ ለከተማው ህብረተሰብ ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እንዲቻል ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን መረጃ በጥናት በመለየት ይሰበስባል፤እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን ለመለየት ጥናቶች እንዲከናወኑ ያደርጋል፣

፲፮ ህብረተሰቡ ያለበትን የትራንስፖርት ችግር ለማቃለል በአስተዳደሩ የተገዙ ወይም የሚገዙ የከተማ አውቶቡሶችን ያስተዳድራል ፣ ተገቢው የስምሪት ፕሮግራም መውጣቱን ይከታተላል ፣ ተገቢውን አገልግሎት መስጠታቸውን ይቆጣጠራል፤

፲፯ የማዘጋጃቤታዊ ገቢን ለማሳደግ የሚረዱ ጥናቶችን ያከናውናል፣ የህግ ማዕቀፎችን ያዘጋጃል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

፲፰ አከታተምን በሚመለከት ጥናት እንዲካሄድ ያደርጋል፣ ከተማው የአካባቢ ማዕከል እንዲሆን እና የአገልግሎት አሰጣጡም እንዲሻሻልሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፱ የከተማ እና የገጠር ትስስር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበት ሁኔታ በሚመለከት ጥናት እንዲጠና ያደርጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል ፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፳ በከተማው ያለውን የመሠረተ ልማት አገልግሎት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ በዚህ አዋጅ ለሥራ አስኪያጅ ተጠሪ እንዲሆኑ የተወሰኑ ተቋማትን ይቆጣጠራል፤ያስተባብራል፤በበላይነት ይመራል፤

፳፩ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፹፩.□<u>ጽዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ሥራዎች፣ መካነ መቃብርንና የህዝብ መፀዳጃ ቤቶችን ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፤

፪ የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ሥራዎች ለተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች እንዲያገለግሉ ያደርጋል፣ መዝናኛዎች አዘጋጅቶ ያቀርባል፤

፫ ህብረተሰቡን የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ሥራዎች ልማትና እንክብካቤ ያሳትፋል፣ መናፈሻዎችና መካነ አራዊት የሚሰሩበትን ደረጃ ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬ በከተማው ፕላን መሠረት ለመካነ መቃብርነት፣ ለአረንጓዴቦታነት፣ መንገድ አካፋዮች፣ አደባባዮችና ለመናፈሻነት የተከለሉ ቦታዎችን በባለቤትነት ያለማል፣ ያስተዳድራል፤

፭ መካነ መቃብራትን በተሻለ ሁኔታ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ስልት ይቀይሳል፤ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣ የቀብር የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ በባይተዋርነት የተቀበሩ ሰዎች ዝርዝር ለጽህፈት ቤቱ በየወቅቱ ያስተላልፋል፣ የባይተዋርነት ቀብር እንዲካሄድ ያደርጋል፣ ለመደበኛ ቀብር የአስክሬን መጓጓዣ መኪና የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ያጓጉዛል፤

፮ በአረንጓዴ መሠረተ ልማት ፣ መካነ መቃብርና በህዝብ መፀዳጃ ቤቶች ልማት እንዲሁም በደረቅ ቆሻሻ ማኔጅመንት አገልግሎት ሥራ ለመሰማራት ለሚፈልጉ አካላት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ተገቢ ድጋፍም ይሰጣል፤

፯ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ በተመለከተ የግል ባለሀብቶችንና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን የማስተባበሪያ ስልት በመቀየስ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፰ የደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ከቤት ለቤት፣ ከጉዳና እና ከንግድ ድርጅቶች የማሰባሰብ፣ የማጓጓዝ እና የማስወገድ ተግባር ያከናውናል፤

፱ ዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓትን ለመዘርጋት ጥናቶችን በማጥናትና የተለያዩ የአሰራር ስርዓቶችን በመቅረፅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ ደረጃ ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም በደረጃው መሰረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ያዘጋጃል፣ ይከታተላል፤

፲፩ደረቅ ቆሻሻ እንደገና በሥራ ላይ የሚውልበትንና ጠቃሚ ውጤት የሚያስገኝበትን ስልት በማጥናት ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፪. በጣም በተጨናነቁና የመፀዳጃ ቤት ችግር ባለባቸው አካባቢ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በማስተባበር የጋራ መፀዳጃ ቤቶች እንዲገነቡና በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

፲፫.የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ክፍያ ሥርዓት በማደራጀት ከተጠቃሚዎች የአገልግሎት ክፍያ እንዲሰበሰብ በማድረግ ገቢው አገልግሎቱን ለማስፋት እንዲውል ያደርጋል፣ አገልግሎቱን ተጠቃሚዎች በቀላሉ የሚያገኙበትን ሁኔታ ይፈጥራል።

፲፬.ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፹፪.□ቄራ አገልግሎት ድርጅት ሥልጣንና ተግባር።

፩ የድርጅቱን እቅድና ፕሮግራም ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል።

፪ በወጡ ህጎች መሠረት የእንስሳት እርድ አገልግሎት ይሰጣል፣ ተረፈ ምረት በማዘጋጀት ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት ይቀይሳል፣ ያጠናል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ህገ ወጥ እርድ ይቆጣጠራል።

፫ በየአካባቢው ህገ ወጥ እርድ እንዳይስፋፋ የህዝቡ ጤንነት እንዳይበከል በመከላከል ረገድ ህብረተሰቡን ያስተባብራል።

፬ በየጊዜው ለእርድ የሚቀርቡትን እንስሳት ምርምራ በማስደረግ እና ከድህረ እርድ በኋላ እያንዳንዱ የአካል ክፍል በማስመርመር ጤንነቱ የተረጋገጠ ሥጋ እንዲቀርብ ያደርጋል።

፭ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎችን እንዲሟሉ ያደርጋል።

፮ ጤንነቱ የተረጋገጠና ንጽህናው የተጠበቀ የእርድ አገልግሎት የሚስፋፋበትን፣ የተረፈ ምረት አጠቃቀም የሚሻሻልበትን እና ህገ ወጥ እርድ የሚወገድበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል።

፯ በየጊዜው ድርጅቱ የሚሻሻልበትን ጥናት በማድረግ የመፍትሄ ሀሳብ ያመነጫል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል።

፰ አግባብ ካላቸው አካላትና ከአስተዳደሩ ነዋሪዎች ጋር በመተባበር ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን በመከላከል ረገድ ከሚመለከተው አካል ጋር በአጋርነት ይሰራል።

፱ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፹፫.የአካባቢ ልማትና የህብረተሰብ ተሳትፎ ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩ .በህብረተሰቡ ተለይተው የሚቀርቡ የልማት ጥያቄዎችን አግባብነት በመፈተሽ ከአስተዳደሩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የልማት ዕቅድ ውስጥ መካተቱን በማገናዘብ በበጀት እንዲደገፍ ያቀርባል፤

፪ .ለአካባቢ ልማት ስራዎች ማስፈፀሚያ የሚውል ሃብት የሚገኝበትን ስልት በመቀየስ ከመንግስት፣ ከህብረተሰቡና ከሌሎች ድጋፍ ከሚያደርጉ አካላት ሀብት የማፈላለግ ስራ ያከናውናል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚመለከታቸው አካላት የሙያ፣ የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ ሊጠይቅ ይችላል፤

፫ የፕሮጀክት ሃብት ከማመንጨት እስከ አፈፃፀሙ ድረስ ባለው የስራ ሂደት ነዋሪዎችን በቀጥታ በማሳተፍ የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጥር ያደርጋል፣ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን ህዝቡ በዘላቂነት በመረከብ እንዲንከባከባቸው ሲበላሹ እንዲጠግናቸው እና በባለቤትነት ስሜት እንዲያስተዳድራቸው ያስተባብራል ፣ ይደግፋል ፤

፬ በገጠርና በከተማ ቀበሌ መካከል የሚካሄዱ የአካባቢ ልማት ስራዎች የተጣጣሙና የተደጋገፉ እንዲሆኑ ያስተባብራል፤

፭ ነዋሪዎች በሂደት በራሳቸው ሃብት ጉልበትና እውቀት የአካባቢውን የመሰረተ ልማት ችግሮች መፍታት እንዲችሉ የማስተባበር ስራ ይሰራል፤

፮ በአስተዳደሩ የሚከናወኑትን የአካባቢ ልማት ስራዎች ህብረተሰቡ በልማት ማህበራቸው የበለጠ ተደራጅተውና ተጠናክረው የሚቀጥልበትን የአሰራር ስርዓት ይቀይሳል፤

፯ በአካባቢ ልማት ጉልህ አስተዋፅኦ ሊኖራቸው የሚችሉ መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች ከህብረተሰቡ ጋር ይበልጥ ተቀራርበው ሊሰሩ የሚችሉበትን ስልት ይቀይሳል ፣ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል፤

፰ ህብረተሰቡየአካባቢውንችግርየልማትፍላጎትእንዲለይና የልማት ቀጥተኛ ተሳታፊና አንቀሳቃሽ እንዲሆን በየአካባቢው የልማት አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፤

፱ የህብረተሰቡንፍላጎትመሰረትያደረጉየአካባቢልማትግንባታስራዎችላይነዋሪውንበማስተባበርናበማሳተፍአጠናክሮማስቀጠልየሚያስችሉልዩልዩየጥናትስራዎችን በማከናወን በተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፤

፲ ህብረተሰቡለልማትበማሰለፍየልማቱምተጠቃሚናባለቤትእንዲሆንለማስቻልየተሰሩስራ ዎችክንውንሂደትይገመግማል፣የዳሰሳጥናትያከናውናል፣ይህንንበመቀመርለቀጣይልማት ግብዓትያደርጋል፤

፲፩ ለታችኛው እርከን መዋቅር ልማት ምክር ቤትናአብይ ኮሚቴዎች ድጋፍ ያደርጋል ፣ ያስተባብራል ፣ ይመራል፤

፲፪ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፹፬.<u>የውኃ እና ፍሳሽ ባለሥልጣን</u>

ባለስልጣኑ በድሬዳዋ ከተማ የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን እንደገና ለማቋቋም በወጣውአዋጅ ቁጥር ፴፯/፪ሺ፯ላይ የተገለፀው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

## ፹፭.<u>የመንገዶች ባለሥልጣን</u>

ባለሥልጣኑ በድሬዳዋ አስተዳደር የመንገዶች ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፯ ላይ የተገለፀው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

# <u>ክፍል ስድስት</u>

# <u>ስለ ቦርድ ወይም ምክር ቤት አመራር</u>

## ፹፮.<u>በቦርድ ወይም በምክር ቤት ስለሚመሩ አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት</u>

፩ በቦርድ ወይም በምክር ቤት የሚመሩ የአስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንዲሁም የቦርድ ወይም የምክር ቤት አባላት ብዛት በካቢኔው ይወሰናል፤

፪ የአስፈፃሚ አካላት ቦርድ ወይም ምክር ቤት ሰብሳቢና አባላት ከሚመለከታቸው ቢሮዎች ጋር በመመካከር በከንቲባው አቅራቢነት በካቢኔው ይሰየማሉ፤

፫ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ቦርድ ሰብሳቢና አባላት በከተማው ሥራ አስኪያጅ አቅራቢነት በካቢኔው ይሰየማሉ፤

፬ እያንዳንዱ ቦርድ ወይም ምክር ቤት የሚመራውን የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካል በሚመለከት ሥልጣንና ተግባሩ እንዲሁም የቦርዱ የአሰራር ሥነ-ሥርዓት በካቢኔው ይወሰናል፡፡

## ፹፯.<u>አስፈፃሚ አካላት እና የልማት ድርጅቶችን ስለማቋቋም</u>

ለአስተዳደሩ ምክር ቤት ተጠሪ የሆኑ እና በአስተዳደሩ ምክር ቤት በሚሾሙ ኃላፊዎች የሚመሩ አስፈፃሚ አካላትን ሳይጨምር ካቢኔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ በማውጣት ሌላ አስፈጻሚ አካል እንዲታጠፍ ከሌላ አስፈፃሚ አካል ጋር እንዲዋሀድ እንዲከፋፈል ወይም ሥልጣንና ተግባሩ እንዲለወጥ የማድረግ ወይም አዲስ አስፈፃሚ አካል የማቋቋምና የማደራጀት የአስተዳደሩን የልማት ድርጅት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የማቋቋምና እንደገና የማደራጀት የማፍረስ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፹፰.<u>የአስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀትናአሰራር ስለመወሰን</u>

ካቢኔው አስፈላጊነቱን ሲያምንበት የአስፈፃሚው አካላትን አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

# <u>ክፍል ሰባት</u>

# <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

## ፹፱.<u>መብትና ግዴታዎች ስለማስተላለፍ</u>

በነባርና በዚህ አዋጅ በተቋቋሙት አስፈፃሚ አካላት መካከል የሚኖረው የመብትና ግዴታ መተላለፍ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

፩ ፀጥታን የሚመለከቱ የፍትህ፣ ፀጥታና የህግ ጉዳዮች ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ተላልፎአል፤

፪ ፍትህና የህግ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የፍትህ፣ ፀጥታና የህግ ጉዳዮች ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የፍትህ ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፡፡

፫ ማህበራዊ ጉዳይን የሚመለከቱ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ተላልፎአል፤

፬ የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ተላልፎአል፤

፭ ወጣቶችን የሚመለከቱ የወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የወጣቶች፣ ስፖርት፣ባህል እና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ማስተባበሪያ ቢሮ ተላልፎአል፤

፮ ኮንስትራክሽንን የሚመለከቱ የኮንስትራክሽን ፣ ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ተላልፎአል፤

፯ የቤቶች ልማትን የሚመለከቱ የኮንስትራክሽን ፣ ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ለከተማው ስራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፤

፰ የደን ልማትና ጥበቃ የሚመለከቱ የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የግብርና እና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፤

፱ የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ተላልፎአል፤

፲ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ተላልፎአል፤

፲፩ የግብርና፣ ውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የግብርና ውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ተላልፎአል፤

፲፪ ቴክኒክና ሙያን የሚመለከቱ የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የሥራ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ተላልፎአል፤

፲፫ ሠራተኛን የሚመለከቱ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ለሥራ፣ ክህሎትና ቴክኖሊጂ ልማት ቢሮ ተላልፎአል፤

፲፬ ባህልና ቱሪዝምን የሚመለከቱ የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ለወጣቶች፣ ባህል፣ስፖርት እና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ማስተባበሪያ ቢሮ ተላልፎአል፤

፲፭ የስራ ዕድል ፈጠራን የሚመለከቱ የከተማ ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ለሥራ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ተላልፎአል፤

፲፮ የምግብ ዋስትናን የሚመለከቱ የከተማ ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የከተማ ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፤

፲፯ የጤና ጥበቃ ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የጤና ቢሮ ተላልፎአል፤

፲፰ የመሬት ልማት እና ማናጅመንት ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የመሬት ልማትና ማናጅመንት ቢሮ ተላልፎአል፤

፲፱ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው መንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ተላልፎአል፤

፳የፐብሊክሰርቪስናየሰውሀብትልማትቢሮመብትናግዴታዎችበዚህአዋጅለተቋቋመውየፐብሊክ ሰርቪስናየሰውሀብትልማትቢሮተላልፎአል፤

፳፩የትምህርት ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የትምህርት ቢሮ ተላልፎአል፤

፳፪የከንቲባውና ካቢኔ ጉዳዮች ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የከንቲባው እና የካቢኔ ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፤

፳፫የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብት ለውጥ ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ተላልፎአል፤

፳፬የአደጋ ክስተት ስጋት ሥራ አመራር ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የአደጋ ስጋት አመራር ከሚሽን ተላልፎአል፤

፳፭የውሃ ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፤

፳፮የንግድ ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የንግድ ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፤

፳፯የባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፤

፳፰የህብረተሰብ ተሳትፎና ልማት ኢጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው አካባቢ ልማትና ህብረተሰብ ተሳትፎ ኢጀንሲ ተላልፎአል፤

፳፱የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች የመንግስት ግዥ እና ንብረት ባለስልጣን ተላልፎአል፤

፴ የከተማው ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የከተማው ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፤

፴፩የደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት ተላልፎአል፤

፴፪የቄራ አገልግሎት ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የቄራ አገልግሎት ተላልፎአል፤

፴፫የጽዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የጽዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት ኤጀንሲ ተላልፎአል፤

## ፺.የተሻሻሉ ህጎች

፩ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ጽህፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፫ የተቋሙን ስያሜና ተግባርና ኃላፊነት የሚገልጹ አንቀፆች በዚህ አዋጅ አንቀጽ፷፺መሠረት ተሻሽለዋል፡፡

፪ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፳፺/፪ሺ፮ የተቋሙን ስያሜ የሚገልጹ አንቀፆች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፪ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡

፫ የድሬዳዋ አስተዳደር የገቢዎች ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፳፫/፪ሺ፬ ሥልጣንና ተግባሩንበሚገልፀው አንቀጽ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬ መሠረት አዲስ ተግባርና ኃላፊነት ተጨምሮለታል፡፡

፬ የድሬዳዋ አስተዳደር የአፀደ ህፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅንለማቋቋም የወጣው ደንብ ቁጥር ፲፪/፪ሺ፲ የተቋሙን ስያሜ የሚገልጹ አንቀፆች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፱ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡

## ፺፩.የተሻሩ እና ተፈፃሚ የማይሆኑ ህጎች

፩ የሚከተሉት ህጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-

ሀ.የድሬዳዋ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፷፺/፳፻፫፤

ለ.የድሬዳዋ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፷፱/፪ሺ፫፤

ሐ.የድሬደዋ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፶፯/፪ሺ፲፤

መ.የድሬዳዋ አስተዳደር የሥራ አመራርና የካይዘን ኢንስቲቲዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፵፪/፪ሺ፰፤

ሠ.የድሬዳዋ አስተዳደር የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፵፫/፲፱፻፺፰

፪ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## <u>፺፪.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

የአስተዳደሩየአስፈፃሚናማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚወሰነው መሠረት ውስጣዊ አደረጃጀታቸው ተጠይቆ ወደ ሥራ እስከሚገቡ ጊዜ ድረስበዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፁት ህጎች በስራ ላይ የሚውሉ ይሆናል፡፡

## <u>፺፫ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

፩ የድሬዳዋ አስተዳደር ካቢኔ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም አስፈላጊውን ደንብ እና መመሪያ ማውጣት ይችላል፤

፪ ለዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት ለሚወጣ ደንብ አፈፃፀም የሚመለከታቸው ቢሮዎች አስፈላጊውን ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣት ይችላሉ፡፡

## <u>፺፬.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በአስተዳደሩ ድሬ ነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ድሬዳዋ_______________ቀን፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ከድር ጁሀር**

**የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ**